ግን፡ለሌሎችም፡ማካፈልን፡አትርሱ ፤ እን
ዲህ፡ያለው፡መሥዋዕት፡እግዚአብሔርን፡
ደስ፡ያሰኘዋልና ።
፲፯፤ ስዋኖቻችሁ፡ታዘዙና፡ተገዙ፤እነርሱ፡ስሌ
ትን፡እንደሚሰጡ፡አድርገው፥ይህንኑ፡በደ
ስታ፡እንጂ፡በኃዘን፡እንዳያደርጉት፥ይህ፡
የማይጠቅማችሁ፡ነበርና፥ ስለ፡ነፍሳችሁ፡
ይተጋሉ ።
፲፰፤ ጸልዩልን፤በነገር፡ሁሉ፡በመልካም፡ እን
ድንኖር፡ወደን፥መልካም፡ሕሊና፡እንዳለን፡
፲፱፤ ተረድተናልና ። ይልቁንም፡ፈጥኜ፡እንድመ
ለስላችሁ፡ይህን፡ታደርጉ፡ዘንድ፡አጥብቄ፡
እለምናችኋለሁ ።
፳፤ በዘላለም፡ኪዳን፡ደም፡ለበጎች፡ትልቅ፡
እረኛ፡የሆነውን፡ጌታችንን፡ኢየሱስን፡ከሙ
ታን፡ያወጣው፡የሰላም፡አምላክ፥በኢየሱስ፡ ፳፩፤
ክርስቶስ፡በኩል፡በፊቱ፡ደስ፡የሚያሰኘውን፡
በእናንተ፡እያደረገ፥ፈቃዱን፡ታደርጉ፡ዘንድ፡
በመልካም፡ሥራ፡ሁሉ፡ፍጹማን፡ያድርጋ
ችሁ፤ለእርሱ፡እስከ፡ዘላለም፡ድረስ፡ክብር፡
ይሁን፤አሜን ።
ወንድሞች፡ሆይ፥የምክርን፡ቃል፡እንድ ፳፪፤
ትታገሡ፡እመክራችኋለሁ፥በጥቂት፡ቃል፡
ጽፌላችኋለሁና ። ወንድማችን፡ጢሞቴዎስ፡ ፳፫፤
እንደ፡ተፈታ፡እወቁ፥ቶሎ፡ቢመጣ፡
ከእርሱ፡ጋር፡አያችኋለሁ ። ለዋኖቻችሁ፡ ፳፬፤
ሁሉና፡ለቅዱሳን፡ሁሉ፡ሰላምታ፡አቅርቡ
ልኝ ። ከኢጣሊያ፡የሆኑት፡ሰላምታ፡ያቀር
ቡላችኋል ። ጸጋ፡ከሁላችሁ፡ጋር፡ይሁን፤ ፳፭፤
አሜን ።

# መጀመሪያይቱ፡የሐዋርያው፡የጴጥሮስ፡መልእክት ።

ምዕራፍ፡፩ ።

፩፡፪፤ የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሐዋርያ፡ጴጥሮስ፥እግ
ዚአብሔር፡አብ፡አስቀድሞ፡እንዳወቃቸው፡
በመንፈስም፡እንደሚቀደሱ፥ይታዘዙና፡በኢ
የሱስ፡ክርስቶስ፡ደም፡ይረጩ፡ዘንድ፡ለተ
መረጡት፡በጳንጦስና፡በገላትያ፡በቀጰዶቅያም፡
በእስያም፡በቢታንያም፡ለተበተኑ፡መጻተ
ኞች፤
ጸጋና፡ሰላም፡ይብዛላችሁ ።
፫፡፬፡፭፤ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ከሙታን፡በመነሣቱ፡
ለሕያው፡ተስፋና፡ስማይጠፋ፥እድፈትም፡
ለሌለበት፥ለማያልፍም፡ርስት፡እንደ፡ምሕ
ረቱ፡ብዛት፡ሁለተኛ፡የወለደን፡የጌታችን፡
የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አምላክና፡አባት፡ይባ
ረክ፤ ይህም፡ርስት፡በመጨረሻው፡ዘመን፡
ይገለጥ፡ዘንድ፡ስተዘጋጀ፡መዳን፡በእምነት፡
በእግዚአብሔር፡ኃይል፡ስተጠበቃችሁ፡ለእ
፮፡፯፤ ናንተ፡በሰማይ፡ቀርቶላችኋል ። በዚህም፡
እጅግ፡ደስ፡ይላችኋል፥ነገር፡ግን፡በእሳት፡
ምንም፡ቢፈተን፡ከሚጠፋው፡ወርቅ፡ይልቅ፡
አብልጦ፡የሚከብር፡የተፈተነ፡እምነታችሁ፥
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሲገለጥ፥ለምስጋናና፡ለክ
ብር፡ለውዳሴም፡ይገኝ፡ዘንድ፡አሁን፡ለጥቂት፡
ጊዜ፡ቢያስፈልግ፡በልዩ፡ልዩ፡ፈተና፡አዝናች
፰፡፱፤ ኋል ። እርሱንም፡ሳታዩት፡ትወዱታላችሁ፤
አሁንም፡ምንም፡ባታዩት፡በእርሱ፡አምና
ችሁ፥የእምነታችሁን፡ፍጻሜ፡እርሱም፡የነ
ፍሳችሁን፡መዳን፡እየተቀበላችሁ፥በማይነገ
ርና፡ክብር፡በሞላበት፡ሐሤት፡ደስ፡ይላች
ኋል ።
ስለእናንተም፡ስለሚሰጠው፡ጸጋ፡ትንቢት፡ ፲፤
የተናገሩት፡ነቢያት፡ስለዚህ፡መዳን፡ተግ
ተው፡እየፈለጉ፡መረመሩት ፤ በእነርሱም፡ ፲፩፤
የነበረ፡የክርስቶስ፡መንፈስ፥ስለ፡ክርስቶስ፡
መከራ፡ከእርሱም፡በኋላ፡ስለሚመጣው፡
ክብር፡አስቀድሞ፡እየመሰከረ፥በምን፡ወይም፡
እንዴት፡ባለ፡ዘመን፡እንዳመለከተ፡ይመረ
ምሩ፡ነበር ። ለእነርሱም፡ከሰማይ፡በተላከ፡ ፲፪፤
በመንፈስ፡ቅዱስ፡ወንጌልን፡የሰበኩላችሁ፡
ሰዎች፡አሁን፡በወሩላችሁ፡ነገር፡እናንተን፡
እንጂ፡ራሳቸውን፡እንዳላገለገሉ፡ተገለጠላ
ቸው ፤ ይህንም፡ነገር፡መላእክቱ፡ሊመለከቱ፡
ይመኛሉ ።
ስለዚህ፡የልቡናችሁን፡ወገብ፡ታጥቃች ፲፫፤
ሁና፡በመጠን፡ኖራችሁ፥ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ሲገለጥ፡የምታገኙትን፡ጸጋ፡ፈጽማችሁ፡
ተስፋ፡አድርጉ ። እንደሚታዘዙ፡ልጆች፡ ፲፬፤
ባለማወቃችሁ፡አስቀድሞ፡የኖራችሁበትን፡
ምኞት፡አትከተሉ ። ዳሩ፡ግን፡— እኔ፡ቅዱስ፡ ፲፭፡፲፮፤
ነኝና፡ቅዱሳን፡ሁኑ፡ተብሎ፡ስለ፡ተጻፈ፡የጠ
ራችሁ፡ቅዱስ፡እንደ፡ሆነ፡እናንተ፡ደግሞ፡
በኑሮአችሁ፡ሁሉ፡ቅዱሳን፡ሁኑ ። ስለው፡ ፲፯፤
ፊትም፡ሳያደላ፡በእያንዳንዱ፡ላይ፡እንደ፡
ሥራው፡የሚፈርደውን፡አባት፡ብላችሁ፡ብት
ጠሩ፡በእንግድነታችሁ፡ዘመን፡በፍርሃት፡

፲፫። [illegible]

፩። [illegible]

፲፰፡፲፱ ኑሩ ። ከአባቶቻችሁ፡ከወረሳችሁት፡ከከንቱ፡
ኑሮአችሁ፡በሚያልፍ፡ነገር፡በብር፡ወይም፡
በወርቅ፡ሳይሆን÷ነውርና፡እድፍ፡እንደ፡
ሌለው፡እንደ፡በግ፡ደም፡በክቡር፡የክርስ
ቶስ፡ደም፡እንደ፡ተዋጃችሁ፡ታውቃላችሁ ።
፳፡፳፩ ዓለም፡ሳይፈጠር፡እንኳ፡አስቀድሞ፡ታወቀ÷
ነገር፡ግን፡እምነታችሁና፡ተስፋችሁ፡በእግዚ
አብሔር፡ይሆን፡ዘንድ÷ከሙታን፡በስነሣው፡
ክብርንም፡በሰጠው፡በእግዚአብሔር፡በእርሱ፡
ስለምታምኑ፡ስለ፡እናንተ፡በዘመኑ፡መጨ
ረሻ፡ተገለጠ ።
፳፪ ስለእውነት፡እየታዘዛችሁ፡ግብዝነት፡ለሌለ
በት፡ለወንድማማች፡መዋደድ፡ነፍሳችሁን፡
አንጽታችሁ፡አርስ፡በርሳችሁ፡ከልባችሁ፡
፳፫ አጥብቃችሁ፡ተዋደዱ ። ዳግመኛ፡የተወለዳ
ችሁት፡ከሚጠፋ፡ዘር፡አይደለም÷በሕያውና፡
ለዘላለም፡በሚኖር፡በእግዚአብሔር፡ቃል፡
ከማይጠፋ፡ዘር፡ነው፡እንጂ ።
፳፬ ሥጋ፡ሁሉ፡እንደ፡ሣር፡ክብሩም፡ሁሉ፡
እንደ፡ሣር፡አበባ፡ነውና ፤ ሣሩ፡ይጠወ
ልጋል፡አበባውም፡ይረግፋል ፤
፳፭ የጌታ፡ቃል፡ግን፡ለዘላለም፡ይኖራል ።
በወንጌልም፡የተሰበከላችሁ፡ቃል፡ይህ፡ነው ።

## ምዕራፍ፡፪ ።

፩ እንግዲህ፡ክፋትን፡ሁሉ፡ተንኰልንም፡
ሁሉ፡ግብዝነትንም፡ቅንዓትንም፡ሐሜትንም፡
፪፡፫ ሁሉ፡አስወግዳችሁ÷ጌታ፡ቸር፡መሆኑን፡
ቀምሳችሁ፡እንደ፡ሆነ÷ለመዳን፡በእርሱ፡
እንድታድጉ፡አሁን፡እንደ፡ተወለዱ፡ሕፃናት፡
ተንኰል፡የሌለበትን፡የቃልን፡ወተት፡ተመኙ ።
፬ በሰውም፡ወደ፡ተጣለ፡በእግዚአብሔር፡
ዘንድ፡ግን፡ወደ፡ተመረጠና፡ክቡር፡ወደ፡
ሆነው፡ወደ፡ሕያው፡ድንጋይ፡ወደ፡እርሱ፡
፭ እየቀረባችሁ÷እናንተ፡ደግሞ፡እንደ፡ሕያ
ዋን፡ድንጋዮች፡ሆናችሁ÷በኢየሱስ፡ክርስ
ቶስ፡ለእግዚአብሔር፡ደስ፡የሚያሰኝ፡መንፈ
ሳዊ፡መሥዋዕትን፡ታቀርቡ፡ዘንድ፡ቅዱሳን፡
ካህናት፡እንድትሆኑ፡መንፈሳዊ፡ቤት፡ስመ
፮ ሆን፡ትሠሩ ። በመጽሐፍ፡—
እነሆ÷የተመረጠና፡የከበረን፡የማዕዘን፡
ራስ፡ድንጋይ፡በጽዮን፡አኖራለሁ፡በእ
ርሱም፡የሚያምን፡አያፍርም፡
፯ ተብሎ፡ተጽፎአልና ። እንግዲህ፡ክብሩ፡ለእ
ናንተ፡ለምታምኑት፡ነው ፤ ለማያምኑ፡ግን፡
እናጢዎች፡የጣሉት፡ድንጋይ፡እርሱ፡የማዕ
ዘን፡ራስ፡የዕንቅፋትም፡ድንጋይ፡የማሰናከ ፰
ያም፡ዓለት፡ሆነ ፤ የማያምኑ፡ስለ፡ሆኑ፡በቃሉ፡
ይሰናከሉበታልና ፤ ለዚህ፡ደግሞ፡የተመደቡ፡
ናቸው ።
እናንተ፡ግን፡ከጨለማ፡ወደሚደነቅ፡ብር ፱
ሃኑ፡የጠራችሁን፡የእርሱን፡በጎነት፡እንድት
ነግሩ፡የተመረጠ፡ትውልድ÷የንጉሥ፡ካህ
ናት÷ቅዱስ፡ሕዝብ÷ለርስቱ፡የተለየ፡ወገን፡
ናችሁ ፤ እናንተ፡ቀድሞ፡ወገን፡አልነበራች ፲
ሁም፡አሁን፡ግን፡የእግዚአብሔር፡ወገን፡
ናችሁ ፤ እናንተ፡ምሕረት፡ያገኛችሁ፡አልነበ
ራችሁም፡አሁን፡ግን፡ምሕረትን፡አግኝታ
ችኋል ።
ወዳጆች፡ሆይ÷ነፍስን፡ከሚዋጋ፡ሥጋዊ፡ ፲፩
ምኞት፡ትርቁ፡ዘንድ፡እንግዶችና፡መጻተ
ኞች፡እንደ፡መሆናችሁ፡እለምናችኋለሁ ፤
በሚመለከቱት፡ስለ፡መልካም፡ሥራችሁ÷ ፲፪
ክፉ፡እንደምታደርጉ፡በዚያ፡እናንተን፡በሚ
ያሙበት፡ነገር÷በሚጐበኝበት፡ቀን፡እግዚ
አብሔርን፡ያከብሩት፡ዘንድ፡በአሕዛብ፡መካ
ከል፡ኑሮአችሁ፡መልካም፡ይሁን ።
ስለ፡ጌታ፡ብላችሁ፡ለሰው፡ሥርዓት፡ሁሉ፡ ፲፫
ተገዙ ፤ ለንጉሥም፡ቢሆን÷ከሁሉ፡በላይ፡
ነውና ፤ ለመኳንንትም፡ቢሆን÷ክፉ፡የሚያደ ፲፬
ርጉትን፡ለመቅጣት፡በጎም፡የሚያደርጉትን፡
ለማመስገን፡ከእርሱ፡ተልከዋልና፡ተገዙ ።
በጎ፡እያደረጋችሁ÷የማያውቁትን፡ሞኞች፡ ፲፭
ዝም፡ታሰኙ፡ዘንድ፡እንዲህ፡የእግዚአብሔር፡
ፈቃድ፡ነውና ፤ አርነት፡ወጥታችሁ፡እንደ፡ ፲፮
እግዚአብሔር፡ባሪያዎች፡ሁኑ፡እንጂ፡ያ፡አር
ነት፡ለክፋት፡መሸፈኛ፡እንዲሆን፡አታድርጉ ።
ሁሉን፡አክብሩ÷ወንድሞችን፡ውደዱ÷እግ ፲፯
ዚአብሔርን፡ፍሩ÷ንጉሥን፡አክብሩ ።
ሎሌዎች፡ሆይ÷ለበጎዎችና፡ለገሮች፡ጌቶ ፲፰
ቻችሁ፡ብቻ፡ሳይሆን፡ለጠማሞች፡ደግሞ፡
በፍርሃት፡ሁሉ፡ተገዙ ። በግፍ፡መከራን፡የሚ ፲፱
ቀበል፡ሰው፡እግዚአብሔርን፡እያሰበ፡ኀዘንን፡
ቢታገሥ፡ምስጋና፡ይገባዋልና ። ኃጢአት፡ ፳
አድርጋችሁ፡ስትጐሰሙ፡ብትታገሡ÷ምን፡
ክብር፡አለበት ? ነገር፡ግን፡መልካም፡አድር
ጋችሁ፡መከራን፡ስትቀበሉ፡ብትታገሡ÷ይህ፡
ነገር፡በእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ምስጋና፡ይገባ
ዋል ። የተጠራችሁበት፡ለዚህ፡ነውና ፤ ክርስ ፳፩
ቶስ፡ደግሞ፡ፍለጋውን፡እንድትከተሉ፡ምሳሌ፡
ትቶላችሁ፡ስለ፡እናንተ፡መከራን፡ተቀብሎአ
ልና ። እርሱም፡ኃጢአት፡ሳያደርግም÷ተን ፳፪

፩። ፲፰፤ ምሳ. ፪፥፫፤ ኢሳ. ፶፪፥፫። ፲፱፤ የሐዋ. ፳፥፳፰፤ ዮሐ. ፩፥፳፱። ፳፤ ሮሜ. ፲፮፥፳፭፡፳፮። ፳፩፤ ዮሐ.
፲፱፥፴፬፤ የሐዋ. ፫፥፲፫፡፲፭። ፳፫፤ ዮሐ. ፩፥፲፫። ፳፬፡፳፭፤ ኢሳ. ፵፥፮—፰፤ ማቴ. ፳፬፥፴፭።

፪። ፩፤ ኤፌ. ፬፥፳፪። ፪፤ ፩ ቆሮ. ፫፥፪፤ ፲፬፥፳። ፫፤ መዝ. ፴፫፥፰። ፬፤ ዮሐ. ፮፥፴፯። ፭፤ ኤፌ. ፪፥፳፩፡፳፪፤
ሮሜ ፲፪፥፩። ፮፤ ኢሳ. ፳፰፥፲፮። ፯፤ መዝ. ፻፲፯፥፳፪፤ ማቴ. ፳፩፥፵፪። ፰፤ ኢሳ. ፰፥፲፬። ፱፤ ዘፀ. ፲፱፥
፭፡፮፤ ዘዳግ. ፯፥፮፤ ፲፥፲፭። ፲፤ ሆሴ. ፪፥፳፫። ፲፩፤ ዘሌዋ. ፳፭፥፳፫፤ ገላ. ፭፥፳፬። ፲፪፤ ፪ ቆሮ. ፰፥፳፩፤
ማቴ. ፭፥፲፮። ፲፫፤ ሮሜ ፲፫፥፩። ፲፬፤ ሮሜ ፲፫፥፫፡፬። ፲፭፤ ገላ. ፭፥፲፫። ፲፮፤ ሮሜ ፲፪፥፲፤ ዕብ. ፲፫፥
፩፤ ምሳ. ፳፬፥፳፩፤ ማቴ. ፳፪፥፳፩። ፲፰፤ ኤፌ. ፮፥፭። ፳፤ ማቴ. ፲፮፥፳፬፤ ዮሐ. ፲፫፥፲፭። ፳፩—፳፭፤ ኢሳ.
፶፫፥፬—፲፪። ፳፪፤ ዮሐ. ፰፥፵፮።

፳፪ ኰልም፡በአፉ፡አልተገኘበትም ፤ ሲሰድቡት፡
መልሶ፡አልተሳደበም፡ መከራንም፡ሲቀበል፡
አልዛተም፥ነገር፡ግን፡በጽድቅ፡ለሚፈርደው፡
፳፬ ራሱን፡አሳልፎ፡ሰጠ ፤ ለኃጢአት፡ ሞተን፡
ለጽድቅ፡እንድንኖር፥እርሱ፡ራሱ፡በሥጋው፡
ኃጢአታችንን፡ በእንጨት ፡ላይ፡ ተሸከመ ፤
፳፭ በመገረፉ፡ቍስል፡ተፈወሳችሁ ። እንደ፡በጎች፡
ትቅበዘበዙ፡ነበርና፥ አሁን፡ ግን፡ ወደ፡ ነፍሳ
ችሁ፡ እረኛና፡ ጠባቂ፡ ተመልሳችኋል ።

፳፬ በግዕዝ፡ እንዲህ፡ ተጽፎአል፡— ወበእንተ፡ ኃጢአትነ፡ ውእቱ፡ ተሰቅለ፡ ዲበ፡ ዕፅ፡ በሥጋሁ፡ ከመ፡ ያውፅአነ፡ እምኃጢአትነ፡ ወበጽድቁ፡ ያሕይወነ ።

## ምዕራፍ፡ ፫ ።

፩ እንዲሁም፥ እናንተ፡ ሚስቶች፡ ሆይ፥ ከባ
ሎቻችሁ፡ አንዳንዱ፡ ለትምህርት፡ የማይታ
ዘዙ፡ቢኖሩ፥በፍርሃት፡ያለውን፡ንጹሑን፡ኑሮ
አችሁን፡እየተመለከቱ፡ ያለ፡ትምህርት፡በሚ
ስቶቻቸው፡ ኑሮ፡ እንዲገኙ፡ ተገዙላቸው ።
፫ ለእናንተም፡ ጠጕርን፡ በመሸረብና፡ ወርቅን፡
በማንጠልጠል፡ወይም፡ልብስን፡በመጐናጸፍ፡
፬ በውጭ፡የሆነ፡ሽልማት፡አይሁንላችሁ፥ነገር፡
ግን፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ ዋጋው፡ እጅግ፡
የከበረ፡ የዋህና፡ ዝግተኛ፡ መንፈስ፡ ያለውን፡
የማይጠፋውን፡ልብስ፡ለብሶ፡የተሰወረ፡የልብ፡
፭ ሰው፡ይሁንላችሁ ። እንዲህ፡በቀድሞ፡ዘመን፡
በእግዚአብሔር፡ ተስፋ፡ ያደረጉት፡ ቅዱሳት፡
ሴቶች፡ ደግሞ፡ ለባሎቻቸው፡ ሲገዙ፡ ተሸል
፮ መው፡ ነበርና ፤ እንዲሁም፡ ሣራ፡ ለአብር
ሃም፡— ጌታ፡ብላ፡እየጠራችው፡ታዘዘችለት ፤
እናንተም፡ ከሚያስደነግጥ፡ ነገር፡ አንዳች፡
እንኳ፡ ሳትፈሩ፡ መልካም፡ ብታደርጉ፡ ልጆ
ችዋ፡ ናችሁ ።
፯ እንዲሁም፥ እናንተ፡ ባሎች፡ ሆይ፥ ደካማ፡
ፍጥረት፡ስለ፡ሆኑ፡ከሚስቶቻችሁ፡ጋር፡በማስ
ተዋል፡ አብራችሁ፡ ኑሩ ፤ ጸሎታችሁ፡ እንዳ
ይከለከል፥አብረው፡ደግሞ፡የሕይወትን፡ጸጋ፡
እንደሚወርሱ፡አድርጋችሁ፡አክብሩአቸው ።
፰ በመጨረሻው፡ ሁላችሁ፡ በአንድ፡ ልብ፡
ሁኑ፥የሌላው፡መከራ፡ለእናንተ፡እንደሚሆን፡
አድርጉ፥ እንደ፡ ወንድሞች፡ ተዋደዱ፥ርኅሩ
፱ ኆችና፡ትሑታን፡ሁኑ ፤ ክፉን፡ በክፉ፡ፈንታ፡
ወይም፡ ስድብን፡በስድብ፡ፈንታ፡አትመልሱ፡
በዚህ፡ ፈንታ፡ ባርኩ፡ እንጂ ፤ በረከትን፡ ልት
ወርሱ፡ ለዚህ፡ ተጠርታችኋልና ።
፲ ሕይወትን፡ ሊወድ፡ መልካሞችንም፡
ቀኖች፡ ሊያይ፡ የሚፈልግ፡ ሰው፥ መላ
ሱን፡ ከክፉ፡ ከንፈሮቹንም፡ ተንኰልን፡
ከመናገር፡ ይከልክል ፤ ከክፉ፡ ፈቀቅ፡ ፲፩
ይበል፥ መልካምንም፡ያድርግ፥ ሰላምን፡
ይሻ፡ ይከተለውም ፤ የጌታ፡ ዓይኖች፡ ፲፪
ወደ፡ ጻድቃን፡ ናቸውና፥ ጆሮዎቹም፡
ለጸሎታቸው፡ ተከፍተዋል፥የጌታ፡ፊት፡
ግን፡ ክፉ፡ ነገርን፡ በሚያደርጉ፡ ላይ፡
ነው ።
በጎንም፡ ለማድረግ፡ ብትቀኑ፡ የሚያስጨንቃ ፲፫
ችሁ፡ማን፡ነው? ነገር፡ግን፡ስለ፡ጽድቅ፡እንኳ፡ ፲፬
መከራን፡ ብትቀበሉ፡ ብፁዓን፡ ናችሁ ። ማስ
ፈራራታቸውንም፡ አትፍሩ፡ አትናወጡም፥
ዳሩ፡ ግን፡ ጌታን፡ እርሱም፡ ክርስቶስ፡ በልባ ፲፭
ችሁ፡ ቀድሱት ። በእናንተ፡ ስላለ፡ ተስፋ፡
ምክንያትን፡ ለሚጠይቁአችሁ፡ ሁሉ፡ መልስ፡
ለመስጠት፡ ዘወትር፡ የተዘጋጃችሁ፡ ሁኑ፥
ነገር፡ ግን፡ በየዋህነትና፡ በፍርሃት፡ ይሁን ።
በክርስቶስ፡ያለውን፡መልካሙን፡ኑሮአችሁን፡ ፲፮
የሚሳደቡ፡ ሰዎች፡ ክፉን፡ እንደምታደርጉ፡
በሚያሙበት፡ ነገር፡ እንዲያፍሩ፡ በጎ፡ ሕሊና፡
ይኑራችሁ ። የእግዚአብሔር፡ፈቃድ፡እንዲህ፡ ፲፯
ቢሆን፥ ክፉ፡ ስለ፡ ማድረግ፡ ሳይሆን፡ በጎ፡ ስለ፡
ማድረግ፡ መከራን፡ ብትቀበሉ፡ ይሻላችኋልና ።
ክርስቶስ፡ ደግሞ፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ እን ፲፰
ዲያቀርበን፡ እርሱ፡ ጻድቅ፡ ሆኖ፡ ስለ፡ ዓመፀ
ኞች፡ አንድ፡ ጊዜ፡ በኃጢአት፡ ምክንያት፡
ሞቶአልና ፤ በሥጋ፡ ሞተ፡ በመንፈስ፡ ግን፡
ሕያው፡ ሆነ፥ በእርሱም፡ ደግሞ፡ ሄዶ፡ በወኅኒ፡ ፲፱
ለነበሩ፡ነፍሳት፡ሰበከላቸው ፤ ጥቂቶች፡ማለት፡ ፳
ስምንት፡ ነፍስ፡ በውኃ፡ የዳኑበት፡ መርከብ፡
ሲዘጋጅ፥የእግዚአብሔር፡ ትዕግሥት፡ በኖኅ፡
ዘመን፡ በቈየ፡ ጊዜ፡ ቀድሞ፡ አልታዘዙም ።
ይህም፡ ውኃ፡ ደግሞ፡ ማለት፡ ጥምቀት፡ ምሳ ፳፩
ሌው፡ ሆኖ፡ አሁን፡ ያድነናል፥ የሰውነትን፡
እድፍ፡ ማስወገድ፡ አይደለም፥ ለእግዚአብ
ሔር፡ የበጎ፡ ሕሊና፡ ልመና፡ ነው፡ እንጂ፥
ይህም፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ትንሣኤ፡ ነው ፤
እርሱም፡ መላእክትና፡ ሥልጣናት፡ ኃይላትም፡ ፳፪
ከተገዙለት፡ በኋላ፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ሄዶ፡ በእግ
ዚአብሔር፡ ቀኝ፡ አለ ።

## ምዕራፍ፡ ፬ ።

ክርስቶስም፡በሥጋ፡ስለ፡እኛ፡መከራን፡ስለ፡ ፩
ተቀበለ፥ከእንግዲህ፡ወዲህ፡በሥጋ፡ልትኖሩ፡
በቀረላችሁ፡ ዘመን፡ እንደ፡ እግዚአብሔር፡
ፈቃድ፡ እንጂ፡ እንደ፡ ሰው፡ ምኞት፡ እንዳት
ኖሩ፥ እናንተ፡ ደግሞ፡ ያን፡ አሳብ፡ እንደ፡ ዕቃ፡
ጦር፡ አድርጋችሁ፡ ያዙት፥ በሥጋ፡ መከራን፡
የተቀበለ፡ ኃጢአትን፡ ትቶአልና ። የአሕዛብን፡ ፪

፪ ። ፳፪ ፤ ሮሜ ፰ ፥ ፱ ፡ ፲፩ ። ፳፭ ፤ ሕዝ ፴፬ ፥ ፭ ፤ ዮሐ ፲ ፥ ፲፩ ።
፫ ። ፩ ፤ ኤፌ ፭ ፥ ፳፪ ። ፫ ፡ ፬ ፤ ፩ ጢሞ ፪ ፥ ፱ ። ፮ ፤ ዘፍጥ ፲፰ ፥ ፲፪ ። ፯ ፤ ኤፌ ፭ ፥ ፳፭ ። ፰ ፤ ሮሜ ፲፪ ፥ ፲፮ ።
፱ ፤ ማቴ ፭ ፥ ፴፱ ፤ ፩ ተሰ ፭ ፥ ፲፭ ። ፲—፲፪ ፤ መዝ ፴፬ ፥ ፲፪—፲፮ ። ፲፬ ፤ ማቴ ፭ ፥ ፲ ። ፲፬ ፡ ፲፭ ፤ ኢሳ ፰ ፥ ፲፪ ፡
፲፫ ። ፲፭ ፤ ቆላ ፬ ፥ ፮ ። ፲፯ ፤ ዮሐ ፪ ፥ ፲፪ ። ፲፰ ፤ ዮሐ ፬ ፥ ፮ ። ፲፱ ፤ ዕብ ፱ ፥ ፳፰ ፤ ቆላ ፩ ፥ ፳፪ ። ፳ ፤ ዘፍጥ
፮ ፥ ፲፫ ፡ ፲፬ ፡ ፯ ፥ ፯ ፡ ፳፫ ። ፳፩ ፤ ቲቶ ፫ ፥ ፭ ። ፳፪ ፤ ኤፌ ፩ ፥ ፳ ፡ ፳፩ ።
፬ ። ፩ ፤ ሮሜ ፮ ፥ ፪ ፡ ፯ ። ፪ ፤ ፩ ዮሐ ፪ ፥ ፲፮ ፡ ፲፯ ። ፫ ፤ ኤፌ ፪ ፥ ፲፩—፲፪ ።

ፈቃድ ፡ ያደረጋችሁበት ፡ በመዳራትና ፡ በሥጋ ፡
ምኞትም ፡ በስካርም ፡ በዘፈንም ፡ ያለ ፡ ልክም ፡
በመጠጣት ፡ ነውርም ፡ ባለበት ፡ በጣዖት ፡ ማም
ለክ ፡ የተመላለሳችሁበት ፡ ያለፈው ፡ ዘመን ፡ ይበ
፬ ቃልና ። በዚህም ፡ ነገር ፡ ወደዚያ ፡ መዳራት ፡
ብዛት ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ስለማትሮጡ ፡ እየተሳ
፭ ደቡ ፡ ይደነቃሉ ፤ ግን ፡ እነርሱ ፡ በሕያዋንና ፡
በሙታን ፡ ላይ ፡ ሊፈርድ ፡ ለተዘጋጀው ፡ መልስ ፡
፮ ይሰጣሉ ። እንደ ፡ ሰዎች ፡ በሥጋ ፡ እንዲፈረ
ድባቸው ፡ በመንፈስ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ እንዲኖሩ ፡ ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ ወንጌል ፡
ለሙታን ፡ ደግሞ ፡ ተሰብኮላቸው ፡ ነበርና ።
፯ ዳሩ ፡ ግን ፡ የነገር ፡ ሁሉ ፡ መጨረሻ ፡ ቀርቦ
አል ። እንግዲህ ፡ እንደ ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ እስኩ ÷
፰ ትጸልዩም ፡ ዘንድ ፡ በመጠን ፡ ኑሩ ፤ ፍቅር ፡ የኃ
ጢአትን ፡ ብዛት ፡ ይሸፍናልና ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡
እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ አጥብቃችሁ ፡ ተዋደዱ ።
፱ ያለ ፡ ማንጐራጐር ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ እንግድ
፲ ነትን ፡ ተቀባበሉ ፤ ልዩ ፡ ልዩን ፡ የእግዚአብሔ
ርን ፡ ጸጋ ፡ ደጋግ ፡ መጋቢዎች ፡ እንደ ፡ መሆና
ችሁ ÷ እያንዳንዳችሁ ፡ የጸጋን ፡ ስጦታ ፡ እንደ ፡
ተቀበላችሁ ፡ መጠን ፡ በዚያው ፡ ጸጋ ፡ እርስ ፡ በር
፲፩ ሳችሁ ፡ አገልግሉ ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ የሚናገር ፡
ቢሆን ÷ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይናገር ፤
የሚያገለግልም ፡ ቢሆን ÷ እግዚአብሔር ፡ በሚ
ሰጠኝ ፡ ኃይል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ያገልግል ፤ ክብ
ርና ፡ ሥልጣን ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ ለእርሱ ፡
በሚሆነው ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በኩል ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ በነገር ፡ ሁሉ ፡ ይከብር ፡ ዘንድ ፤
አሜን ።
፲፪ ወዳጆች ፡ ሆይ ÷ በእናንተ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡
እሳት ፡ ሊፈትናችሁ ፡ ስለሚሆነው ፡ መከራ ፡
ድንቅ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ መጣባችሁ ፡ አትደነቁ ፤
፲፫ ነገር ፡ ግን ፡ ክብሩ ፡ ሲገለጥ ፡ ደግሞ ፡ ሐሤት ፡
እያደረጋችሁ ፡ ደስ ፡ እንዲላችሁ ÷ በክርስቶስ ፡
መከራ ፡ በምትካፈሉበት ፡ ልክ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ።
፲፬ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ብትነቀፉ ፡ የክብር ፡ መን
ፈስ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በእናንተ ፡
፲፭ ላይ ፡ ያርፋልና ፡ ብፁዓን ፡ ናችሁ ። ከእናንተ ፡
ማንም ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ወይም ፡ ሌባ ፡ ወይም ፡
ክፉ ፡ አድራጊ ፡ እንደሚሆን ፡ ወይም ፡ በሌሎች ፡
ጕዳይ ፡ እንደሚገባ ፡ ሆኖ ፡ መከራን ፡ አይቀበል ፤
፲፮ ክርስቲያን ፡ እንደሚሆን ፡ ግን ፡ መከራን ፡ ቢቀ
በል ፡ ስለዚህ ፡ ስም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመስግን ፡
፲፯ እንጂ ፡ አይፈር ። ፍርድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ቤት ፡ ተነሥቶ ፡ የሚጀመርበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሶአ
ልና ፤ አስቀድሞም ፡ በእኛ ፡ የሚጀመር ፡ ከሆነ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ወንጌል ፡ የማይታዘዙ ፡ መጨ
ረሻቸው ፡ ምን ፡ ይሆን ? ጻድቅም ፡ በጭንቅ ፡ ፲፰
የሚድን ፡ ከሆነ ፡ ዓመፀኛውና ፡ ኃጢአተኛው ፡
ወዴት ፡ ይታይ ፡ ዘንድ ፡ አለው ? ስለዚህ ፡ ፲፱
ደግሞ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ መከ
ራን ፡ የሚቀበሉ ÷ መልካምን ፡ እያደረጉ ፡ ነፍ
ሳቸውን ፡ ለታመነ ፡ ፈጣሪ ፡ አደራ ፡ ይስጡ ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

እንግዲህ ፡ እኔ ÷ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ሽማግሌ ፡ ፩
የክርስቶስም ፡ መከራ ፡ ምስክር ፡ ደግሞም ፡ ሊገ
ለጥ ፡ ካለው ፡ ክብር ፡ ተካፋይ ፡ የሆንሁ ÷ በመካ
ከላቸው ፡ ያሉትን ፡ ሽማግሌዎች ፡ እመክራቸዋ
ለሁ ፤ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ የእግዚአብ ፪
ሔርን ፡ መንጋ ፡ ጠብቁ ፤ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ፈቃድ ፡ በውድ ፡ እንጂ ፡ በግድ ፡ ሳይሆን ÷ በበጎ ፡
ፈቃድ ፡ እንጂ ፡ መጥፎውን ፡ ረብ ፡ በመመኘት ፡
ሳይሆን ፡ ጐብኙት ፤ ለመንጋው ፡ ምሳሌ ፡ ሁኑ ፡ ፫
እንጂ ፡ ማኅበሮቻችሁን ፡ በኃይል ፡ አትግዙ ፤
የእረኞችም ፡ አለቃ ፡ በሚገለጥበት ፡ ጊዜ ፡ የማ ፬
ያልፈውን ፡ የክብርን ፡ አክሊል ፡ ትቀበላላችሁ ።
እንዲሁም ÷ ጐበዞች ፡ ሆይ ÷ ለሽማግሌዎች ፡ ፭
ተገዙ ፤ ሁላችሁም ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ እየተ
ዋረዳችሁ ፡ ትሕትናን ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ታጠቁ ÷
እግዚአብሔር ፡ ትዕቢተኞችን ፡ ይቃወማልና ÷
ለትሑታን ፡ ግን ፡ ጸጋን ፡ ይሰጣል ።
እንግዲህ ፡ በጊዜው ፡ ከፍ ፡ እንዲያደርጋችሁ ፡ ፮
ከኃይለኛው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በታች ፡
ራሳችሁን ፡ አዋርዱ ፤ እርሱ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ፯
ያስባልና ፡ የሚያስጨንቃችሁን ፡ ሁሉ ፡ በእ
ርሱ ፡ ላይ ፡ ጣሉት ። በመጠን ፡ ኑሩ ፡ ንቁም ÷ ፰
ባላጋራችሁ ፡ ዲያብሎስ ፡ የሚውጠውን ፡ ፈልጎ ፡
እንደሚያገሣ ፡ አንበሳ ፡ ይዞራልና ፤ በዓለም ፡ ፱
ያሉት ፡ ወንድሞቻችሁ ፡ ያን ፡ መከራ ፡ በሙሉ ፡
እንዲቀበሉ ፡ እያወቃችሁ ፡ በእምነት ፡ ጸንታ
ችሁ ፡ ተቃወሙት ። በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ ፡ ፲
ዘላለም ፡ ክብሩ ፡ የጠራችሁ ፡ የጸጋ ፡ ሁሉ ፡ አም
ላክ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ መከራን ፡ ከተቀበላችሁ ፡
በኋላ ፡ ራሱ ፡ ፍጹማን ፡ ያደርጋችኋል ፡ ያጸናች
ሁማል ፡ ያበረታችሁማል ። ለእርሱ ፡ ክብርና ፡ ፲፩
ኃይል ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ ይሁን ፤ አሜን ።
እየመከርኋችሁና ፡ የምትቆሙበት ፡ ጸጋ ፡ ፲፪
እውነተኛ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ እንደሆነ ፡
እየመሰከርሁላችሁ ÷ የታመነ ፡ ወንድም ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ በቈጠርሁት ፡ በሲልዋኖስ ፡ እጅ ፡ በአጭሩ ፡

፬። ፭ ፡ የሐዋ. ፲ ÷ ፵፪ ። ፮ ፡ ም. ፫ ÷ ፲፰ ። ፯ ፡ ያዕ. ፭ ÷ ፰ ። ፰ ፡ ምሳ. ፲ ÷ ፲፪ ፤ ያዕ. ፭ ÷ ፳ ። ፱ ፡ ዕብ. ፲፫ ÷ ፪ ።
፲ ፡ ፲፩ ፤ ሮሜ ፲፪ ÷ ፮ ፡ ፯ ፤ ፩ ቆሮ. ፬ ÷ ፩ ፡ ፪ ፤ ፲ ÷ ፴፩ ። ፲፪ ፡ ም. ፩ ÷ ፯ ፤ ዮሐ. ፲፯ ÷ ፪ ። ፲፫ ፡ ም. ፩ ÷ ፯ ፤ የሐዋ.
፭ ÷ ፵፩ ፤ ሮሜ ፰ ÷ ፲፯ ። ፲፬ ፡ ማቴ. ፭ ÷ ፲፩ ። ፲፯ ፡ ኤር. ፳፭ ÷ ፳፱ ፤ ፪ ተሰ. ፩ ÷ ፰ ። ፲፰ ፡ ምሳ. ፲፩ ÷ ፴፩ ፤ ሉቃ.
፳፫ ÷ ፴፩ ። ፲፱ ፡ መዝ. ፴ ÷ ፭ ።

፭። ፩ ፡ ሉቃ. ፳፬ ÷ ፵፰ ፤ ሮሜ ፰ ÷ ፲፯ ። ፪ ፡ ዮሐ. ፳፩ ÷ ፲፮ ፤ የሐዋ. ፳ ÷ ፳፰ ፤ ፩ ጢሞ ፫ ÷ ፫ ። ፫ ፡ ማቴ. ፳ ÷ ፳፭ ፡ ፳፮ ፤
ቲቶ ፪ ÷ ፯ ። ፬ ፡ ዕብ. ፲፫ ÷ ፳ ፤ ፪ ጢሞ. ፬ ÷ ፰ ። ፭ ፡ ዮሐ. ፲፫ ÷ ፬ ፡ ፭ ፡ ፲፬ ፤ ምሳ. ፫ ÷ ፴፬ ። ፮ ፡ ማቴ. ፳፫ ÷ ፲፪ ፤
ያዕ. ፬ ÷ ፲ ። ፯ ፡ ማቴ. ፮ ÷ ፳፭ ፤ ፊልጵ. ፬ ÷ ፮ ። ፰ ፡ ማር. ፲፫ ÷ ፴፯ ፤ ፩ ተሰ. ፭ ÷ ፮ ። ፱ ፡ የሐዋ. ፲፬ ÷ ፳፪ ። ፲ ፡
፩ ተሰ. ፬ ÷ ፲፪ ። ፲፪ ፡ ፩ ተሰ. ፭ ÷ ፩ ።

፲፫፤ ጽፌላችኋለሁ ። ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ተመርጣ ፡
በባቢሎን ፡ ያለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ልጄም ፡
፲፬፤ ማርቆስ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ። በፍቅር ፡
አሳሳም ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ሰላምታ ፡ ተሰጣጡ ።
በክርስቶስ ፡ ላላችሁ ፡ ለሁላችሁ ፡ ሰላም ፡
ይሁን ። አሜን ።

# ሁለተኛይቱ ፡ የሐዋርያው ፡ የጴጥሮስ ፡ መልእክት ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩፤ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሪያና ፡ ሐዋርያ ፡ የሆነ ፡
ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፥
ለአምላካችንና ፡ በመድኃኒታችን ፡ በኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ጽድቅ ፡ ከገኘነው ፡ ጋር ፡ የተካከለ ፡
የክብር ፡ እምነትን ፡ ላገኙ ፤
፪፫፤ የመለኮቱ ፡ ኃይል ፥ በገዛ ፡ ክብሩና ፡ በበጎነቱ ፡
የጠራንን ፡ በማወቅ ፥ ለሕይወትና ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ ለመምሰል ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
ስለ ፡ ሰጠን ፥ በእግዚአብሔርና ፡ በጌታችን ፡ በኢ
የሱስ ፡ እውቀት ፡ ጸጋና ፡ ሰላም ፡ ይብዛላችሁ ።
፬፤ ስለ ፡ ክፉ ፡ ምኞት ፡ በዓለም ፡ ካለው ፡ ጥፋት ፡
አምልጣችሁ ፡ ከመለኮት ፡ ባሕርይ ፡ ተካፋዮች ፡
በተስፋ ፡ ቃል ፡ እንድትሆኑ ፥ በእነዚያ ፡ ክብርና ፡
በጎነት ፡ የተከበረና ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ ተስ
፭፤ ፋን ፡ ሰጠን ። ስለዚህም ፡ ምክንያት ፡ ትጋትን ፡
ሁሉ ፡ እያሳያችሁ ፡ በእምነታችሁ ፡ በጎነትን ፡
፮፤ ጨምሩ ፥ በበጎነትም ፡ እውቀትን ፥ በእውቀ
ትም ፡ ራስን ፡ መግዛት ፥ ራስንም ፡ በመግዛት ፡
መጽናትን ፥ በመጽናትም ፡ እግዚአብሔርን ፡
፯፤ መምሰል ፥ እግዚአብሔርንም ፡ በመምሰል ፡ የወ
ንድማማችን ፡ መዋደድ ፥ በወንድማማችም ፡
፰፤ መዋደድ ፡ ፍቅርን ፡ ጨምሩ ። እነዚህ ፡ ነገሮች ፡
ለእናንተ ፡ ሆነው ፡ ቢበዙ ፥ በጌታችን ፡ በኢየ
ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እውቀት ፡ ሥራ ፡ ፈቶችና ፡
ፍሬ ፡ ቢሶች ፡ እንዳትሆኑ ፡ ያደርጉአችኋልና ፤
፱፤ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ የሌሉት ፡ዕውር ፡ ነውና ፥ በቅ
ርብም ፡ ያለውን ፡ ብቻ ፡ ያያል ፥ የቀደመውንም ፡
፲፤ ኃጢአቱን ፡ መንጻት ፡ ረስቶአል ። ስለዚህ ፥
ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ መጠራታችሁንና ፡ መመረ
ጣችሁን ፡ ታጸኑ ፡ ዘንድ ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ ትጉ ፤
እነዚህን ፡ ብታደርጉ ፡ ከቶ ፡ አትሰናከሉምና ።
፲፩፤ እንዲሁ ፡ ወደ ፡ ዘላለሙ ፡ ወደ ፡ ጌታችንና ፡ መድ
ኃኒታችን ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መንግ
ሥት ፡ መግባት ፡ በሙላት ፡ ይሰጣችኋልና ።
፲፪፤ ስለዚህ ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ ምንም ፡ ብታውቁ ፡
በእናንተም ፡ ዘንድ ፡ ባለ ፡ እውነት ፡ ምንም ፡ ብት
ጸኑ ፥ ስለ ፡ እነዚህ ፡ ዘወትር ፡ እንዳሳስባችሁ ፡
፲፫፤ ቸል ፡ አልልም ። ሁልጊዜም ፡ በዚህ ፡ ማደሪያ ፡
ሳለሁ ፡ በማሳሰቤ ፡ ላነቃችሁ ፡ የሚገባኝ ፡ ይመ
፲፬፤ ስለኛል ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዳ
መለከተኝ ፡ ከዚህ ፡ ማደሪያዬ ፡ መለየቴ ፡ ፈጥኖ ፡
እንዲሆን ፡ አውቃለሁና ። ከመውጣቴም ፡ በኋላ ፡ ፲፭፤
እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ እንድታስቡ ፡ በየጊዜው ፡
ትችሉ ፡ ዘንድ ፡ እተጋለሁ ።
የእርሱን ፡ ግርማ ፡ አይተን ፡ እንጂ ፡ በብል ፲፮፤
ሃት ፡ የተፈጠረውን ፡ ተረት ፡ ሳንከተል ፡ የጌታ
ችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ኃይልና ፡ መም
ጣት ፡ አስታወቅናችሁ ። ከገናናው ፡ ክብር ፡— ፲፯፤
በእርሱ ፡ ደስ ፡ የሚለኝ ፡ የምወደው ፡ ልጄ ፡
ይህ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ያ ፡ ድምፅ ፡ በመጣለት ፡
ጊዜ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ክብርንና ፡ ምስጋ
ናን ፡ ተቀብሎአልና ፤ እኛም ፡ በቅዱሱ ፡ ተራራ ፡ ፲፰፤
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ሳለን ፡ ይህን ፡ ድምፅ ፡ ከሰማይ ፡
ሲወርድ ፡ ሰማን ። ከእርሱም ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ ፲፱፤
የጸና ፡ የትንቢት ፡ ቃል ፡ አለን ፤ ምድርም ፡ እስ
ኪጠባ ፡ ድረስ ፡ የንጋትም ፡ ኮከብ ፡ በልባችሁ ፡
እስኪወጣ ፡ ድረስ ፥ ሰው ፡ በጨለማ ፡ ስፍራ ፡
የሚበራን ፡ መብራት ፡ እንደሚጠነቀቅ ፡ ይህን ፡
ቃል ፡ እየጠነቀቃችሁ ፡ መልካም ፡ ታደርጋላ
ችሁ ። ይህን ፡ በመጀመሪያ ፡ እወቁ ፤ በመጽ ፳፤
ሐፍ ፡ ያለውን ፡ ትንቢት ፡ ሁሉ ፡ ማንም ፡ ለገዛ ፡
ራሱ ፡ ሊተረጕም ፡ አልተፈቀደም ፤ ትንቢት ፡ ፳፩፤
ከቶ ፡ በሰው ፡ ፈቃድ ፡ አልመጣምና ፥ ዳሩ ፡ግን ፡
በእግዚአብሔር ፡ ተልከው ፡ ቅዱሳን ፡ ሰዎች ፡
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተነድተው ፡ ተናገሩ ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ሐሰተኞች ፡ ነቢያት ፡ ደግሞ ፡ በሕ ፩፤
ዝቡ ፡ መካከል ፡ ነበሩ ፡ እንዲሁም ፡ በመካከላ
ችሁ ፡ ደግሞ ፡ ሐሰተኞች ፡ አስተማሪዎች ፡ ይሆ
ናሉ ፤ እነርሱም ፡ የዋጃቸውን ፡ ጌታ ፡ እንኳ ፡
ክደው ፡ የሚፈጥንን ፡ ጥፋት ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡
እየሳቡ ፡ የሚያጠፉ ፡ ኑፋቄን ፡ አሾልከው ፡ ያገ
ባሉ ፤ ብዙዎችም ፡ በመዳራታቸው ፡ ይከተሉ ፪፤
አቸዋል ፡ በእነርሱም ፡ጠንቅ ፡ የእውነት ፡ መን
ገድ ፡ ይሰደባል ። ገንዘብንም ፡ በመመኘት ፡ በተ ፫፤
ፈጠረ ፡ ነገር ፡ ይረቡባችኋል ፤ ፍርዳቸውም ፡
ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ አይዘገይም ፡ ጥፋታቸውም ፡
አያንቀላፋም ።
እግዚአብሔር ፡ ኃጢአትን ፡ላደረጉ ፡ መላእ ፬፤

፭። ፲፫፤ ቈላ. ፬፥፲። ፲፬፤ ፩ ተሰ. ፭፥፳፮።
፩። ፩፤ ቲቶ ፪፥፲፫። ፪፤ ፩ ጴጥ. ፩፥፪። ፩—፪፤ ገላ. ፩፥፳፪፤፳፫። ፬፤ ፩ ዮሐ. ፩፥፯፤፪፥፲፭። ፲፪፤፲፫፤ ሮሜ ፲፭፥፲፬፤፲፭፤ ይሁዳ ፭፤ ፪ ቆሮ. ፭፥፩። ፲፬፤ ዮሐ. ፳፩፥፲፰፤፲፱። ፲፮፤ ማር. ፱፥፪፤፫፤ ዮሐ. ፩፥፲፬። ፲፯፤፲፰፤ ማቴ. ፲፯፥፭፤፮። ፲፱፤ ፪ ቆሮ. ፬፥፯። ፳፩፤ ፩ ጴጥ. ፩፥፲፤፲፩።
፪። ፩፤ ማቴ. ፳፬፥፲፩፤ ፪ ቆሮ. ፲፩፥፲፫፤ ይሁዳ ፬። ፪፤ ፪ ጢሞ. ፪፥፫። ፫፤ ፩ ተሰ. ፪፥፭። ፬—፲፯፤ ይሁዳ ፮—፲፫።

ክት፡ሳይራራላቸው፡ወደ፡ገሃነም፡ጥሎ፡በጨ
ለማ፡ጕድጓድ፡ለፍርድ፡ሊጠበቁ፡አሳልፎ፡
፭ ከሰጣቸው÷ለቀደመውም፡ዓለም፡ሳይራራ፡
ከሌሎች፡ሰባት፡ጋር፡ጽድቅን፡የሚሰብከውን፡
ኖኅን፡አድኖ፡በኃጢአተኞች፡ዓለም፡ላይ፡
፮ የጥፋትን፡ውኃ፡ካወረደ÷ኃጢአትንም፡ያደ
ርጉ፡ዘንድ፡ላሉት፡ምሳሌ፡አድርጎ፡ከተማዎ
ችን፡ሰዶምንና፡ገሞራን፡አመድ፡አስኪሆኑ፡
ድረስ፡አቃጥሎና፡ገልብጦ፡ከፈረደባቸው÷
፯፡፰ ጻድቅ፡ሎጥም፡በመካከላቸው፡ሲኖር፡እያየና፡
እየሰማ፡ዕለት፡ዕለት፡በዓመፀኛ፡ሥራቸው፡
ጻድቅ፡ነፍሱን፡አስጨንቆ፡ነበርና፡በዓመፀ
ኞች፡ሴሰኛ፡ኑሮ፡የተገፋውን፡ያን፡ጻድቅ፡
፱፡፲ ከዳነ÷ጌታ፡እግዚአብሔርን፡የሚያመልኩ
ትን፡ከፈተና፡እንዴት፡እንዲያድን÷በደለኞ
ችንም፡ይልቁንም፡በርኵስ፡ምኞት፡የሥጋን፡
ፍትወት፡እየተከተሉ፡የሚመላለሱትን፡ጌት
ነትንም፡የሚንቁትን፡እየቀጣቸው፡ለፍርድ፡
ቀን፡እንዴት፡እንዲጠብቅ፡ያውቃል ።
ደፋሮችና፡ኵሩዎች፡ሆነው፡ሥልጣን፡ያላ
፲፩ ቸውን፡ሲሰድቡ፡አይንቀጠቀጡም ፤ ዳሩ፡ግን፡
መላእክት፡በኀይልና፡በብርታት፡ከእነርሱ፡
ይልቅ፡ምንም፡ቢበልጡ፡በጌታ፡ፊት፡በእነ
ርሱ፡ላይ፡የስድብን፡ፍርድ፡አያመጡም ።
፲፪ እነዚህ፡ግን፡ለመጠመድና፡ለመጥፋት፡በፍ
ጥረታቸው፡እንደ፡ተወለዱ፡እእምሮ፡እንደ
ሌላቸው፡እንስሶች፡ሆነው÷በማያውቁት፡
ነገር፡እየተሰደቡ፡በጥፋታቸው፡ይጠፋሉ ፤
፲፫ የዓመፃቸውን፡ደመወዝ፡ይቀበላሉ ። በቀን፡
ሲዘፍኑ፡እንደ፡ተድላ፡ይቈጥሩታል ፤ ነውረ
ኞችና፡ርኵሰን፡ሆነው፡ከእናንተ፡ጋር፡ሲጋ
፲፬ በዙ፡በፍቅር፡ግብዣ፡ይዘፍናሉ ፤ ምንዝር፡
የሞላባቸው፡ኃጢአትንም፡የማይተዉ፡ዓይ
ኖች፡አሉአቸው ፤ የማይጸኑትን፡ነፍሶች፡
ያታልላሉ ፤ መመኘትን፡የስመደ፡ልብ፡አላ
፲፭ ቸው ፤ የተረገሙ፡ናቸው ። ቅንን፡መንገድ፡
ትተው፡ተስተዋል ፤ የባሶርን፡ልጅ፡የበለዓምን፡
መንገድ፡ተከተሉ ፤ እርሱ፡የዓመፃን፡ደመ
፲፮ ወዝ፡ወደደ÷ነገር፡ግን፡ስለ፡መተላለፉ፡
ተዘለፈ ፤ ቃል፡የሌለው፡አህያ፡በሰው፡ቃል፡
ተናግሮ፡የነቢዩን፡እብድነት፡አገደ ።
፲፯ ድቅድቅ፡ጨለማ፡ለዘላለም፡የተጠበቀላቸው፡
እነዚህ፡ውኃ፡የሌለባቸው፡ምንጮች፡በዐ
ውሎ፡ነፋስም፡የተነዱ፡ደመናዎች፡ናቸው ።
፲፰ ከንቱና፡ከመጠን፡ይልቅ፡ታላቅ፡የሆነውን፡
ቃል፡ይናገራሉና÷በስሕተትም፡ከሚኖሩት፡
አሁን፡የሚያመልጡትን፡በሥጋ፡ሴሰኛ፡ምኞት፡
ያታልላሉ ። ራሳቸው፡የጥፋት፡ባሪያዎች፡ ፲፱
ሆነው፦አርነት፡ትወጣላችሁ፡እያሉ፡ተስፋ፡
ይሰጡአቸዋል ፤ ሰው፡ለተሸነፈበት፡ለእርሱ፡
ተገዝቶ፡ባሪያ፡ነውና ። በጌታችንና፡በመድኃ ፳
ኒታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እውቀት፡ከዓ
ለም፡ርኵሰት፡ካመለጡ፡በኋላ፡ዳግመኛ፡በእ
ርስዋ፡ተጠላልፈው፡የተሸነፉ፡ቢሆኑ÷ከፊ
ተኛው፡ኑሮአቸው፡ይልቅ፡የኋለኛው፡የበሰ፡
ሆኖባቸዋል ። አውቀዋት፡ከተሰጣቸው፡ከቅ ፳፩
ድስት፡ትእዛዝ፡ኪመለሱ፡የጽድቅን፡መንገድ፡
ባላወቋት፡በተሻላቸው፡ነበርና ። ውሻ፡ወደ፡ ፳፪
ትፋቱ፡ይመለሳል÷ደግሞ፦የታጠበች፡
እርያ፡በጭቃ፡ለመንከባለል፡ትመለሳለች፡
እንደሚባል፡እውነተኞች፡ምስሌዎች፡ሆኖባ
ቸዋል ።

## ምዕራፍ፡፫ ።

ወዳጆች፡ሆይ÷አሁን፡የምጽፍላችሁ፡መል ፩፡፪
እክት፡ይህች፡ሁለተኛይቱ፡ናት ። በቅዱሳን፡
ነቢያትም፡ቀድሞ፡የተባለውን፡ቃል፡በሐዋ
ርያቶቻችሁም፡ያገኛችኋትን፡የጌታንና፡የመ
ድኃኒትን፡ትእዛዝ፡እንድታስቡ፡በሁለቱ፡እያ
ሰሰብኋችሁ፡ቅን፡ልቡናችሁን፡አነቃቃለሁ ።
በመጨረሻው፡ዘመን፡እንደ፡ራሳቸው፡ምኞት፡ ፫
የሚመላለሱ፡ዘባቾች፡በመዘበት፡እንዲመጡ፡
ይህን፡በፊት፡እወቁ ፤ እነርሱም፦የመም ፬
ጣቱ፡የተስፋ፡ቃል፡ወዴት፡ነው ? አባቶች፡
ከሞቱበት፡ጊዜ÷እፍጥረት፡መጀመሪያ፡ይፀ፡
ሁሉ፡እንዳለ፡ይኖራልና፡ይላሉ ። ሰማያት፡ ፭
ከጥንት፡ጀምረው፡ምድርም፡በእግዚአብሔር፡
ቃል፡ከውኃ፡ተጋጥማ፡በውኃ፡መካከል፡
እንደ፡ነበሩ፡ወደው፡አያበተውሉምና ፤ በዚ ፮
ህም፡ምክንያት፡ያን፡ጊዜ፡የነበረ፡ዓለም፡
በውኃ፡ሰጥሞ፡ጠፋ ፤ አሁን፡ያሉ፡ሰማያ ፯
ትና፡ምድር፡ግን፡እግዚአብሔርን፡የማያመ
ልኩት፡ሰዎች፡እስከሚጠፉበት፡እስከ፡ፍርድ፡
ቀን፡ድረስ፡ተጠብቀው፡በዚያ፡ቃል፡ለእ
ሳት፡ቀርተዋል ።
እናንተ፡ግን÷ወዳጆች፡ሆይ÷በጌታ፡ዘንድ፡ ፰
አንድ፡ቀን፡እንደ፡ሺህ፡ዓመት÷ሺህ፡ዓመ
ትም፡እንደ፡አንድ፡ቀን፡እንደ፡ሆነ፡ይህን፡
አንድ፡ነገር፡አትርሱ ። ለአንዳንዶች፡የሚዘ ፱
ገይ፡እንደሚመስላቸው፡ጌታ፡ስለ፡ተስፋ፡
ቃሉ፡አይዘገይም÷ነገር፡ግን፡ሁሉ፡ወደ፡
ንስሐ፡እንዲደርሱ፡እንጂ፡ማንም፡እንዳይ
ጠፋ፡ወዶ፡ስለ፡እናንተ፡ይታገሣል ። የጌ ፲
ታው፡ቀን፡ግን፡እንደ፡ሌባ፡ሆኖ፡ይመጣል ፤

፪። ፭ ፩ጴጥ. ፫÷፳ ። ፮ ዘፍጥ. ፲፱÷፳፬ ። ፯ ዘፍጥ. ፲፱÷፲፮፡፳፱ ። ፱ ፩ቆሮ. ፲÷፲፫ ። ፲ ፊልጵ. ፫÷፲፱ ። ፲፩ ዘኍል. ፳፪÷፳—፳ ፤ ራእ. ፪÷፲፬ ። ፲፭ ዘኍል. ፳፪÷፳፪—፳፰ ። ፲፯ ይሁዳ ፲፪ ። ፲፱ ዮሐ. ፰÷፴፬ ። ፳ ማቴ. ፲፪÷፵፭ ፤ ዕብ. ፮÷፬—፮ ። ፳፩ ሉቃ. ፲፪÷፵፯፡፵፰ ፤ ዕብ. ፲÷፳፮፡፳፯ ። ፳፪ ምሳ. ፳፮÷፲፩ ።

፫። ፩፡፫ ይሁዳ ፲፯፡፲፰ ። ፬ ኢሳ. ፭÷፲፱ ፤ ሕዝ. ፲፪÷፳፪ ፤ ማቴ. ፳፬÷፵፰ ። ፭ ዘፍጥ. ፩÷፮—፲ ፤ መዝ. ፳፬÷፪ ። ፮ ዘፍጥ. ፯÷፳፩ ። ፰ መዝ. ፺፱÷፬ ። ፱ ኢሳ. ፴÷፲፰ ፤ እንባ. ፪÷፫ ፤ ፩ጢሞ. ፪÷፬ ። ፲ ፩ተሰ. ፭÷፪ ፤ ማቴ. ፳፬÷፵፫ ፤ ራእ. ፫÷፫ ።

በዚያም፡ቀን፡ሰማያት፡በታላቅ፡ድምፅ፡ያል
ፉሉ ፥ የሰማይም ፡ ፍጥረት ፡ በትልቅ ፡ ትኩ
ሳት፡ይቀልጣል፥ምድርም፡በእርስዋም፡ላይ፡
የተደረገው፡ሁሉ፡ይቃጠላል ።
፲፩፡፲፪ ይህ፡ሁሉ፡እንዲህ፡የሚቀልጥ፡እሆን፥
የእግዚአብሔርን፡ቀን፡መምጣት፡አየጠበቃ
ችሁና፡እያስቸኰላችሁ፥ለቅዱስ፡ኑሮ፡እግ
ዚአብሔርንም፡በመምሰል፡እንደ፡ምን፡ልት
ሆኑ፡ይገባችኋል ? ስለዚያ፡ቀን፡ሰማያት፡ተቃ
ጥለው፡ይቀልጣሉ፡የሰማይም፡ፍጥረት፡በት
፲፫ ልቅ፡ትኩሳት፡ይፈታል ፤ ነገር፡ግን፡ጽድቅ፡
የሚኖርባትን፡አዲስ፡ሰማይና፡አዲስ፡ምድር፡
እንደ፡ተስፋ፡ቃሉ፡እንጠብቃለን ።
፲፬ ስለዚህ፥ወዳጆች፡ሆይ፥ይህን፡እየጠበቃ
ችሁ፡ያለ፡ነውርና፡ያለ፡ነቀፋ፡ሆናችሁ፡በሰ
፲፭ ላም፡በእርሱ፡እንድትገኙ፡ትጉ፥የጌታችንም፡
ትዕግሥት፡መዳናችሁ፡እንደ፡ሆነ፡ቍጠሩ ።
እንዲህም፡የተወደደው፡ወንድማችን፡ጳው
ሎስ፡ደግሞ፡እንደ፡ተሰጠው፡ጥበብ፡መጠን፡
ጳፈላችሁ ፥ በመልእክቱም ፡ ሁሉ ፡ ደግሞ ፡ ፲፮
እንደ፡ነገረ፡ስለዚህ፡ነገር፡ተናገረ ። በእነዚያ፡
ዘንድ፡ለማስተዋል፡የሚያስቸግር፡ነገር፡አለ፥
ያልተማሩትና፡የማይጸኑትም፡ሰዎች፡ሌሎ
ችን፡መጻሕፍት፡እንደሚያጣምሙ፡እነዚህን፡
ደግሞ፡ለገዛ፡ጥፋታቸው፡ያጣምማሉ ። እን ፲፯
ግዲህ፡እናንተ፥ወዳጆች፡ሆይ፥ይህን፡አስቀ
ድማችሁ፡ስለምታውቁ፥በዓመፀኞች፡ስሕ
ተት፡ተስበችሁ፡ከራሳችሁ፡ጽናት፡እንዳት
ወድቁ፡ተጠንቀቁ ፤ ነገር፡ግን፡በጌታችንና፡ ፲፰
በመድኃኒታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጸጋና፡
እውቀት፡እደጉ ። ለእርሱ፡አሁንም፡እስከ፡
ዘላለምም፡ቀን፡ድረስ፡ክብር፡ይሁን ፤ አሜን ።

# መጀመሪያይቱ ፡ የሐዋርያው ፡ የዮሐንስ ፡ መልእክት ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ ስለ፡ሕይወት፡ቃል፡እመጀመሪያው፡የነበ
ረውንና፡የሰማነውን፡በዓይኖቻችንም፡ያየን
ውን፡የተመለከትነውንም፡እጆቻችንም፡የዳሰ
፪ ሱትን፡እናወራለን ፤ ሕይወትም፡ተገለጠ፡አይ
ተንማል፡እንመሰክርማለን፥እአብ፡ዘንድ፡የነበ
ረውንም፡ለእኛም፡የተገለጠውን፡የዘላለምን፡
፫ ሕይወት፡እናወራላችኋለን ፤ እናንተ፡ደግሞ፡
ከእኛ፡ጋር፡ኅብረት፡እንዲኖራችሁ፡ያየነው
ንና፡የሰማነውን፡ለእናንተ፡ደግሞ፡እናወራላ
ችኋለን ። ኅብረታችንም፡ከአባት፡ጋር፡ከል
፬ ጁም፡ከኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጋር፡ነው ። ደስታ
ችሁም፡እንዲፈጸም፡ይህን፡እንጽፍላችኋለን ።
፭ ከእርሱም፡የሰማናት፡ለእናንተም፡የምና
ወራላችሁ፡መልእክት፡—እግዚአብሔር፡ብር
ሃን፡ነው፡ጨለማም፡በእርሱ፡ዘንድ፡ከቶ፡
፮ የለም፡የምትል፡ይህች፡ናት ። ከእርሱ፡ጋር፡
ኅብረት፡አለን፡ብንል፡በጨለማም፡ብንመላ
ለስ፡እንዋሻለን፡እውነትንም፡አናደርግም ፤
፯ ነገር፡ግን፡እርሱ፡በብርሃን፡እንዳለ፡በብርሃን፡
ብንመላለስ፡ለእያንዳንዳችን፡ኅብረት፡አለን፥
የልጁም፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ደም፡ከኃጢ
፰ አት፡ሁሉ፡ያነጻናል ። ኃጢአት፡የለብንም፡
ብንል፡ራሳችንን፡እናስታለን፥እውነትም፡
፱ በእኛ፡ውስጥ፡የለም ። በኃጢአታችን፡ብን
ናዘዝ፡ኃጢአታችንን፡ይቅር፡ሊለን፡እዓመ
ፃም፡ሁሉ፡ሊያነጻን፡የታመነና፡ጻድቅ፡ነው ።
ኃጢአትን፡አላደረግንም፡ብንል፡ሐሰተኛ፡ ፲
እናደርገዋለን፡ቃሉም፡በእኛ፡ውስጥ፡የለም ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ልጆቼ፡ሆይ፥ኃጢአትን፡እንዳታደርጉ፡ ፩
ይህን፡እጽፍላችኋለሁ ። ማንም፡ኃጢአትን፡
ቢያደርግ፡ከአብ፡ዘንድ፡ጠበቃ፡አለን፡እር
ሱም፡ጻድቅ፡የሆነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ነው ።
እርሱም፡የኃጢአታችን፡ማስተስሪያ፡ነው፥ ፪
ስኃጢአታችንም፡ብቻ፡አይደለም፥ነገር፡ግን፡
ለዓለሙ፡ሁሉ፡ኃጢአት፡እንጂ ። ትእዛዛቱ ፫
ንም፡ብንጠብቅ፡በዚህ፡እንዳወቅነው፡እናው
ቃለን ። አውቄዋለሁ፡የሚል፡ትእዛዛቱንም፡ ፬
የማይጠብቅ፡ውሸተኛ፡ነው፡እውነትም፡በእ
ርሱ፡ውስጥ፡የለም ። ቃሉን፡ግን፡የሚጠ ፭
ብቅ፡ሁሉ፡በእርሱ፡የእግዚአብሔር፡ፍቅር፡
በእውነት፡ተፈጽሞአል ። በእርሱ፡እንዳለን፡
በዚህ፡እናውቃለን፤በእርሱ፡እኖራለሁ፡የሚል፡ ፮
እርሱ፡እንደ፡ተመላለሰ፡ራሱ፡ደግሞ፡ሊመ
ላለስ፡ይገባዋል ።
ወንድሞች፡ሆይ፥ከመጀመሪያ፡የነበረቻ ፯
ችሁ፡አሮጌ፡ትእዛዝ፡እንጂ፡የምጽፍላችሁ፡
አዲስ፡ትእዛዝ፡አይደለችም ፤ አሮጌይቱ፡ትእ
ዛዝ፡የሰማችኋት፡ቃል፡ናት ። ዳግመኛ፡አዲስ፡ ፰

፫። ፲፩ ኢሳ ፷፮፥፪። ፲፫ ኢሳ ፷፭፥፲፯ ፤ ፷፮፥፳፪ ፤ ራእ ፳፩፥፩፡፳፯። ፲፭ ሮሜ ፪፥፬። ፲፯ ማር ፲፫፥፳፫። ፲፰ ሮሜ ፲፩፥፴፮።

፩። ፩ ዮሐ ፩፥፩ ፤ ፲፬ ፤ ፲፱፥፴፭ ፤ ሉቃ ፳፬፥፴፱። ፪ ዮሐ ፩፥፬ ፤ ፲፬፥፮። ፫ የሐዋ ፬፥፳ ፤ ዮሐ ፲፯፥፳፩። ፬ ዮሐ ፲፭፥፲፩። ፭ ዮሐ ፰፥፲፪። ፮ ዮሐ ፫፥፳፩። ፯ ዕብ ፱፥፲፬። ፰ ፤ ፲ ምሳ ፳፰፥፲፫። ፲ ምሳ ፳፥፱ ፤ ዮሐ ፭፥፴፰።

፪። ፩ ሮሜ ፰፥፴፬ ፤ ዕብ ፯፥፳፭። ፪ ሮሜ ፫፥፳፭ ፤ ዮሐ ፩፥፳፱። ፫ ዮሐ ፭፥፵፪። ፬ ዮሐ ፲፬፥፳፩። ፭ ዮሐ ፲፬፥፳፫። ፮ ዮሐ ፲፭፥፬ ፤ ፲፪ ዘሌዋ ፲፱፥፲፰። ፯ ዮሐ ፲፫፥፴፬ ፤ ፩፥፪።

ትእዛዝን ፡ እጽፍላችኋለሁ ፥ ይህም ፡ ነገር ፡
በእርሱ ፡ በእናንተም ፡ እውነተኛ ፡ ነው ፤ ጨለ
ማው ፡ ያልፋልና ፡ እውነተኛውም ፡ ብርሃን ፡
፱፤ አሁን ፡ ይበራል ። በብርሃን ፡ እስሁ ፡ የሚል ፡
ወንድሙንም ፡ የሚጠላ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ በጨ
፲፤ ለማ ፡ አለ ። ወንድሙን ፡ የሚወድ ፡ በብርሃን ፡
፲፩፤ ይኖራል ፡ ማሰናከያም ፡ የለበትም ፤ ወንድሙን ፡
የሚጠላ ፡ ግን ፡ በጨለማ ፡ አለ ፥ በጨለማም ፡
ይመላለሳል ፥ የሚሄድበትንም ፡ አያውቅም ፥
ጨለማው ፡ ዓይኖቹን ፡ አሳውሮታልና ።
፲፪፤ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ኃጢአታችሁ ፡ ስለ ፡ ስሙ ፡
፲፫፤ ተሰርዮላችኋልና ፡ እጽፍላችኋለሁ ። አባቶች ፡
ሆይ ፥ ከመጀመሪያ ፡ የነበረውን ፡ አውቃች
ኋልና ፡ እጽፍላችኋለሁ ። ጐበዞች ፡ ሆይ ፥
ክፉውን ፡ አሸንፋችኋልና ፡ እጽፍላችኋለሁ ።
ልጆች ፡ ሆይ ፥ አብን ፡ አውቃችኋልና ፡ እጽፍ
፲፬፤ ላችኋለሁ ። አባቶች ፡ ሆይ ፥ ከመጀመሪያ ፡ የነ
በረውን ፡ አውቃችኋልና ፡ እጽፍላችኋለሁ ።
ጐበዞች ፡ ሆይ ፥ ብርቱዎች ፡ ስለ ፡ ሆናችሁ ፡ የእ
ግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በእናንተ ፡ ስለሚኖር ፡
ክፉውንም ፡ ስለ ፡ አሸንፋችሁ ፡ እጽፍላችኋለሁ ።
፲፭፤፲፮፤ ዓለምን ፡ ወይም ፡ በዓለም ፡ ያሉትን ፡ አትው
ደዱ ፤ በዓለም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ እርሱም ፡ የሥጋ ፡
ምኞትና ፡ የዓይን ፡ አምሮት ፡ ስለ ፡ ገንዘብም ፡
መመካት ፡ ከዓለም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንጂ ፡ ከአባት ፡
ስላልሆነ ፥ ማንም ፡ ዓለምን ፡ ቢወድ ፡ የአባት ፡
፲፯፤ ፍቅር ፡ በእርሱ ፡ ውስጥ ፡ የለም ። ዓለሙም ፡
ምኞቱም ፡ ያልፋሉ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡
የሚያደርግ ፡ ግን ፡ ለዘላለም ፡ ይኖራል ።
፲፰፤ ልጆች ፡ ሆይ ፥ መጨረሻው ፡ ሰዓት ፡ ነው ፥
የክርስቶስም ፡ ተቃዋሚ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡
ሰማችሁ ፡ አሁን ፡ እንኳ ፡ ብዙዎች ፡ የክርስቶስ ፡
ተቃዋሚዎች ፡ ተነሥተዋል ፤ ስለዚህም ፡ መጨ
ረሻው ፡ ሰዓት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እናውቃለን ።
፲፱፤ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ወጡ ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ ከእኛ ፡ ወገን ፡
አልነበሩም ፤ ከእኛ ፡ ወገንስ ፡ ቢሆኑ ፡ ከእኛ ፡
ጋር ፡ጸንተው ፡ በኖሩ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡
ከእኛ ፡ ወገን ፡ እንዳልሆኑ ፡ ይገለጡ ፡ ዘንድ ፡
፳፤ ወጡ ። እናንተም ፡ ከቅዱሱ ፡ ቅባት ፡ ተቀብላ
፳፩፤ ችኋል ፥ ሁሉንም ፡ ታውቃላችሁ ። እውነትን ፡
የምታውቁ ፡ ስለ ፡ ሆናችሁ ፥ ውሸትም ፡ ሁሉ ፡
ከእውነት ፡ እንዳልሆነ ፡ ስለምታውቁ ፡ እንጂ ፡
እውነትን ፡ ስለማታውቁ ፡ አልጽፍላችሁም ።
፳፪፤ ክርስቶስ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ኢየሱስን ፡ ከሚ
ክድ ፡ በቀር ፡ ውሸተኛው ፡ ማን ፡ ነው ? አብንና ፡
ወልድን ፡ የሚክድ ፡ ይህ ፡ የክርስቶስ ፡ ተቃዋሚ ፡
፳፫፤ ነው ። ወልድን ፡ የሚክድ ፡ ሁሉ ፡ አብ ፡ እንኳ ፡
የለውም ፤ በወልድ ፡ የሚታመን ፡ አብ ፡ ደግሞ ፡
፳፬፤ አለው ። እናንተስ ፡ ከመጀመሪያ ፡ የሰማችሁት ፡
በእናንተ ፡ጸንቶ ፡ ይኑር ። ከመጀመሪያ ፡ የሰማ
ችሁት ፡ በእናንተ ፡ ቢኖር ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡
በወልድና ፡ በአብ ፡ ትኖራላችሁ ። እርሱም ፡ ፳፭፤
የሰጠን ፡ ተስፋ ፡ ይህ ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ ነው ።
ስለሚያስቱአችሁ ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ጽፌላች ፳፮፤
ኋለሁ ። እናንተስ ፡ ከእርሱ ፡ የተቀበላችሁት ፡ ፳፯፤
ቅባት ፡ በእናንተ ፡ ይኖራል ፥ ማንም ፡ ሊያስተ
ምራችሁ ፡ አያስፈልጋችሁም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የእ
ርሱ ፡ ቅባት ፡ ስለ ፡ ሁሉ ፡ እንደሚያስተምራ
ችሁ ፥ እውነተኛም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሸትም ፡
እንዳልሆነ ፥ እናንተንም ፡ እንዳስተማራችሁ ፥
በእርሱ ፡ ኑሩ ።
አሁንም ፥ ልጆች ፡ ሆይ ፥ በሚገለጥበት ፡ ጊዜ ፡ ፳፰፤
እምነት ፡ እንዲሆንልን ፡ በመምጣቱም ፡ በእርሱ ፡
ፊት ፡ እንዳናፍር ፡ በእርሱ ፡ ኑሩ ። ጻድቅ ፡ ፳፱፤
እንደ ፡ ሆነ ፡ ካወቃችሁ ፡ጽድቅን ፡ የሚያደርግ ፡
ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ እንደ ፡ ተወለደ ፡ እወቁ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ተብለን ፡ ልንጠራ ፡ ፩፤
አብ ፡ እንዴት ፡ ያለውን ፡ ፍቅር ፡ እንደ ፡ ሰጠን ፡
እዩ ፥ እንዲሁም ፡ ነን ። ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡
ዓለም ፡ እርሱን ፡ ስላላወቀው ፡ እኛን ፡ አያውቀ
ንም ። ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ አሁን ፡ የእግዚአብ ፪፤
ሔር ፡ ልጆች ፡ ነን ፥ ምንም ፡ እንደምንሆን ፡ ገና ፡
አልተገለጠም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ቢገለጥ ፡ እርሱ ፡
እንዳለ ፡ እናየዋለንና ፡ እርሱን ፡ እንድንመስል ፡
እናውቃለን ። በእርሱም ፡ ይህን ፡ ተስፋ ፡ የሚ ፫፤
ያደርግ ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ ንጹሕ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ራሱን ፡ ያነጻል ።
ኃጢአትን ፡ የሚያደርግ ፡ ሁሉ ፡ ዓመፅን ፡ ፬፤
ደግሞ ፡ ያደርጋል ፥ ኃጢአትም ፡ ዓመፅ ፡ ነው ።
እርሱም ፡ ኃጢአትን ፡ ሊያስወግድ ፡ እንደ ፡ ፭፤
ተገለጠ ፡ ታውቃላችሁ ፥ በእርሱም ፡ ኃጢአት ፡
የለም ። በእርሱ ፡ የሚኖር ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአትን ፡ ፮፤
አያደርግም ፤ ኃጢአትን ፡ የሚያደርግ ፡ ሁሉ ፡
አላየውም ፡ አላወቀውምም ። ልጆች ፡ ሆይ ፥ ፯፤
ማንም ፡ አያስታችሁ ፤ እርሱ ፡ ጻድቅ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ጽድቅን ፡ የሚያደርግ ፡ ጻድቅ ፡ ነው ።
ኃጢአትን ፡ የሚያደርግ ፡ ከዲያብሎስ ፡ ነው ፥ ፰፤
ዲያብሎስ ፡ ከመጀመሪያ ፡ ኃጢአትን ፡ ያደርጋ
ልና ። ስለዚህ ፡ የዲያብሎስን ፡ ሥራ ፡ እንዲያ
ፈርስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ተገለጠ ። ከእ ፱፤
ግዚአብሔር ፡ የተወለደ ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአትን ፡
አያደርግም ፥ ዘሩ ፡ በእርሱ ፡ ይኖራልና ፤ ከእግዚ
አብሔርም ፡ ተወልዶአልና ፡ ኃጢአትን ፡ ሊያደ
ርግ ፡ አይችልም ። የእግዚአብሔር ፡ ልጆችና ፡ ፲፤
የዲያብሎስ ፡ ልጆች ፡ በዚህ ፡ የተገለጡ ፡ ናቸው ፤
ጽድቅን ፡ የማያደርግና ፡ ወንድሙን ፡ የማይ

፪። ፲፤ ዮሐ. ፲፩÷፱ ። ፲፩፤ ዮሐ. ፲፪÷፴፭ ። ፲፪፤ ፩ ቆሮ. ፮÷፲፩ ። ፲፬፤ ኤፌ. ፮÷፲ ። ፲፭፤ ያዕ. ፬÷፬ ። ፲፯፤ ማቴ. ፳፬÷፭፤፩ ጢሞ. ፬÷፩ ። ፲፱፤ የሐዋ. ፳÷፴ ። ፳፤ ዮሐ. ፲፬÷፳፮ ። ፳፫፤ ዮሐ. ፭÷፳፫፤፲፭÷፳፫ ። ፳፬፤ ዮሐ. ፩፤ ዮሐ. ፲፬÷፳፫ ። ፳፯፤ ዮሐ. ፲፬÷፳፮፤ኤር. ፴፩÷፴፬፤ዮሐ. ፲፬÷፳፮ ። ፳፰፤ ቆላ. ፫÷፬ ። ፳፱፤ ፫ ዮሐ. ፲፩ ።
፫። ፩፤ ዮሐ. ፩÷፲፪፤፲፯÷፳፭ ። ፪፤ ሮሜ ፰÷፲፯፤ፊልጵ. ፫÷፳፩፤፩ ቆሮ. ፲፫÷፲፪ ። ፫፤ ፪ ቆሮ. ፯÷፩ ። ፭፤ ዕብ. ፱÷፳፰፤ዮሐ. ፰÷፵፮ ። ፯፤ ፫ ዮሐ. ፲፩ ። ፰፤ ዮሐ. ፰÷፵፬፤ዕብ. ፪÷፲፬ ። ፱፤ ሮሜ. ፭÷፲፰ ።

ወድ፡ሁሉ፡ከእግዚአብሔር፡አይደለም ።
፲፩ ከመጀመሪያ፡የሰማችኋት፡መልእክት፡—
እርስ፡በርሳችን፡እንዋደድ፡የምትል፡ይህች፡
፲፪ ናትና ፤ ከክፉው፡እንደ፡ነበረ፡ወንድሙንም፡
እንደ፡ገደለ፡እንደ፡ቃየል፡አይደለም ፤ ስለ፡
ምንስ፡ገደለው ? የገዛ፡ሥራው፡ክፉ፥የወንድ
፲፫ ሙም፡ሥራ፡ጽድቅ፡ስለ፡ነበረ፡ነው ። ወንድ
ሞች፡ሆይ ፥ ዓለም፡ቢጠላችሁ፡አትደነቁ ።
፲፬ እኛ፡ወንድሞችን፡የምንወድ፡ስለ፡ሆንን፡
ከሞት፡ወደ፡ሕይወት፡እንደ፡ተሻገርን፡እናው
ቃለን ፤ ወንድሙን፡የማይወድ፡በሞት፡ይኖ
፲፭ ራል ። ወንድሙን፡የሚጠላ፡ሁሉ፡ነፍሰ፡ገዳይ፡
ነው ፥ ነፍሰ፡ገዳይም፡የሆነ፡ሁሉ፡የዘላለም፡
ሕይወት፡በእርሱ፡እንዳይኖር፡ታውቃላችሁ ።
፲፮ እርሱ፡ስለ፡እኛ፡ነፍሱን፡አሳልፎ፡ሰጥቶአ
ልና፡በዚህ፡ፍቅርን፡አውቀናል ፤ እኛም፡ስለ፡
ወንድሞቻችን፡ነፍሳችንን፡አሳልፈን፡እን
፲፯ ድንሰጥ፡ይገባናል ። ነገር፡ግን፡የዚህ፡ዓለም፡
ገንዘብ፡ያለው ፥ ወንድሙም፡የሚያስፈልገው፡
ሲያጣ፡አይቶ፡ያልራራለት፡ማንም፡ቢሆን ፥
የእግዚአብሔር፡ፍቅር፡በእርሱ፡እንዴት፡ይኖ
፲፰ ራል ? ልጆቼ፡ሆይ ፥ በሥራና፡በእውነት፡
እንጂ፡በቃልና፡በአንደበት፡አንዋደድ ።
፲፱ ልባችንም፡በእኛ፡ላይ፡በሚፈርድበት፡
ሁሉ ፥ ከእውነት፡እንደ፡ሆንን፡በዚህ፡እናው
ቃለን፡በፊቱም፡ልባችንን፡እናሳርፋለን ፥ እግ
ዚአብሔር፡ከልባችን፡ይልቅ፡ታላቅ፡ነውና፡
፳ ሁሉንም፡ያውቃል ። ወዳጆች፡ሆይ ፥ ልባች
ንስ፡ባይፈርድብን፡ለእግዚአብሔር፡ዘንድ፡
፳፩ ድፍረት፡አለን ፥ ትእዛዙንም፡የምንጠብቅና፡
በፊቱ፡ደስ፡የሚያሰኘውን፡የምናደርግ፡ስለ፡
ሆንን፡የምንለምነውን፡ሁሉ፡ከእርሱ፡እናገ
፳፪ ኛለን ። ትእዛዚቱም፡ይህች፡ናት ፥ በልጁ፡
በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡እናምን፡ዘንድ ፥
ትእዛዝንም፡እንደ፡ሰጠን፡እርስ፡በርሳችን፡
፳፫ እንዋደድ፡ዘንድ ። ትእዛዙንም፡የሚጠብቅ፡
በእርሱ፡ይኖራል፡እርሱም፡ይኖርበታል ፤
በዚህም፡በእኛ፡እንዲኖር፡ከሰጠን፡ከመን
ፈሱ፡እናውቃለን ።

## ምዕራፍ፡፬ ።

፩ ወዳጆች፡ሆይ ፥ መንፈስን፡ሁሉ፡አትመኑ ፥
ነገር፡ግን፡መናፍስት፡ከእግዚአብሔር፡ሆነው፡
እንደ፡ሆነ፡መርምሩ ፤ ብዙዎች፡ሐሰተኞች፡
፪ ነቢያት፡ወደ፡ዓለም፡ወጥተዋልና ። የእግዚአ
ብሔርን፡መንፈስ፡በዚህ፡ታውቃላችሁ ፤ ኢየ
ሱስ፡ክርስቶስ፡በሥጋ፡እንደ፡መጣ፡የሚታ
መን፡መንፈስ፡ሁሉ፡ከእግዚአብሔር፡ነው ፥
ኢየሱስ፡ክርስቶስም፡በሥጋ፡እንደ፡መጣ፡ ፫
የማይታመን፡መንፈስ፡ሁሉ፡ከእግዚአብሔር፡
አይደለም ፤ ይህም፡የክርስቶስ፡ተቃዋሚው፡
መንፈስ፡ነው ፤ ይህም፡እንዲመጣ፡ሰምታች
ኋል ፥ አሁንም፡እንኳ፡በዓለም፡አለ ። ልጆች፡ ፬
ሆይ ፥ እናንተ፡ከእግዚአብሔር፡ናችሁ፡አሸ
ንፋችኋቸውማል ፥ በዓለም፡ካለው፡ይልቅ፡
በእናንተ፡ያለው፡ታላቅ፡ነውና ። እነርሱ፡ ፭
ከዓለም፡ናቸው ፤ ስለዚህ፡ከዓለም፡የሆነውን፡
ይናገራሉ፡ዓለሙም፡ይሰማቸዋል ። እኛ፡ከእ ፮
ግዚአብሔር፡ነን ፤ እግዚአብሔርን፡የሚያ
ውቅ፡ይሰማናል ፤ ከእግዚአብሔር፡ያልሆነ፡
አይሰማንም ። የእውነትን፡መንፈስና፡የስሕ
ተትን፡መንፈስ፡በዚህ፡እናውቃለን ።
ወዳጆች፡ሆይ ፥ ፍቅር፡ከእግዚአብሔር፡ ፯
ስለ፡ሆነ ፥ የሚወደውም፡ሁሉ፡ከእግዚአብ
ሔር፡ስለ፡ተወለደ፡እግዚአብሔርንም፡ስለ
ሚያውቅ ፥ እርስ፡በርሳችን፡እንዋደድ ።
ፍቅር፡የሌለው፡እግዚአብሔርን፡አያውቅም ፥ ፰
እግዚአብሔር፡ፍቅር፡ነውና ። በዚህ፡የእግ ፱
ዚአብሔር፡ፍቅር፡በእኛ፡ዘንድ፡ተገለጠ ፥
በእርሱ፡በኩል፡በሕይወት፡እንኖር፡ዘንድ፡
እግዚአብሔር፡አንድ፡ልጁን፡ወደ፡ዓለም፡
ልኮታልና ። ፍቅርም፡እንደዚህ፡ነው ፤ እግ ፲
ዚአብሔር፡እርሱ፡ራሱ፡እንደ፡ወደደን፡ስለ፡
ኃጢአታችንም፡ማስተስሪያ፡ይሆን፡ዘንድ፡
ልጁን፡እንደ፡ላከ፡እንጂ፡እኛ፡እግዚአብሔ
ርን፡እንደ፡ወደድነው፡አይደለም ። ወዳጆች፡ ፲፩
ሆይ ፥ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አድርጎ፡ከወ
ደደን፡እኛ፡ደግሞ፡እርስ፡በርሳችን፡ልን
ዋደድ፡ይገባናል ። እግዚአብሔርን፡ማንም፡ ፲፪
ከቶ፡አላየውም ፤ እርስ፡በርሳችን፡ብንዋደድ፡
እግዚአብሔር፡በእኛ፡ይኖራል፡ፍቅሩም፡
በእኛ፡ፍጹም፡ሆኖአል ።
ከመንፈሱ፡ስለ፡ሰጠን ፥ በእርሱ፡እንድን ፲፫
ኖር፡እርሱም፡በእኛ፡እንዲኖር፡በዚህ፡እና
ውቃለን ። እኛም፡አይተናል፡አብትም፡ልጁን፡ ፲፬
የዓለም፡መድኃኒት፡ሊሆን፡እንደ፡ላከው፡
እንመሰክራለን ። ኢየሱስ፡የእግዚአብሔር፡ ፲፭
ልጅ፡እንደ፡ሆነ፡በሚታመን፡ሁሉ፡እግዚአ
ብሔር፡በእርሱ፡ይኖራል፡እርሱም፡በእግዚ
አብሔር፡ይኖራል ። እኛም፡እግዚአብሔር፡ ፲፮
ለእኛ፡ያለውን፡ፍቅር፡አውቀናል፡አምነን
ማል ። እግዚአብሔር፡ፍቅር፡ነው ፥ በፍቅ
ርም፡የሚኖር፡በእግዚአብሔር፡ይኖራል፡እግ
ዚአብሔርም፡በእርሱ፡ይኖራል ። በፍርድ፡ ፲፯
ቀን፡ድፍረት፡ይሆንልን፡ዘንድ፡ፍቅር፡በዚህ፡
ከእኛ፡ጋር፡ተፈጽሞአል ፤ እርሱ፡እንዳለ፡

፫። ፲፩፤ ምዕ. ፩ ፥ ፭፤ ዮሐ. ፲፫ ፥ ፴፬። ፲፪፤ ዘፍጥ. ፬ ፥ ፰—፰። ፲፫፤ ዮሐ. ፲፭ ፥ ፲፰ ፡ ፲፱ ። ፲፬፤ ዮሐ. ፭ ፥ ፳፬። ፲፭፤ ማቴ. ፭ ፥ ፳፩ ፡ ፳፪። ፲፮፤ ዮሐ. ፲፭ ፥ ፲፫። ፲፯፤ ዘዳግ. ፲፭ ፥ ፯። ፲፰፤ ያዕ. ፪ ፥ ፲፭ ፡ ፲፯። ፳፩፤ ዕብ. ፬ ፥ ፲፮። ፳፪፤ ማቴ. ፯ ፥ ፯። ፳፫፤ ምዕ. ፪ ፥ ፰፤ ዮሐ. ፯ ፥ ፳፱። ፳፬፤ ዮሐ. ፲፬ ፥ ፳፫ ፡ ፳፫፤ ሮሜ ፰ ፥ ፱።

፬። ፩፤ ማቴ. ፯ ፥ ፲፭። ፪፤ ፩ ቆሮ. ፲፪ ፥ ፫። ፫፤ ምዕ. ፪ ፥ ፲፰፤ ፪ ዮሐ. ፯። ፬፤ ሮሜ. ፰ ፥ ፴፩። ፭፤ ዮሐ. ፲፭ ፥ ፲፱። ፯፤ ዮሐ. ፰ ፥ ፵፯። ፰፤ ምዕ. ፪ ፥ ፴፬። ፱፤ ዮሐ. ፫ ፥ ፲፮። ፲፤ ምዕ. ፪ ፥ ፪። ፲፩፤ ዮሐ. ፲፭ ፥ ፴፪። ፲፪ ዮሐ. ፩ ፥ ፲፰። ፲፫፤ ምዕ. ፫ ፥ ፳፬። ፲፬፤ ዮሐ. ፫ ፥ ፲፯። ፲፭፤ ምዕ. ፬ ፥ ፴፩።

እኛ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ነንና ።
፲፰ ፍጹም ፡ ፍቅር ፡ ፍርሃትን ፡ አውጥቶ ፡ ይጥላል ፡
እንጂ ፡ በፍቅር ፡ ፍርሃት ፡ የለም ÷ ፍርሃት ፡
ቅጣት ፡ አለውና ፤ የሚፈራም ፡ ሰው ፡ ፍቅሩ ፡
፲፱ ፍጹም ፡ አይደለም ። እርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ወዶ
፳ ናልና ፡ እኛ ፡ እንወደዋለን ። ማንም ፡— እግዚ
አብሔርን ፡ እወዳለሁ ፡ እያለ ፡ ወንድሙን ፡
ቢጠላ ፡ ሐሰተኛ ፡ ነው ፤ ያየውን ፡ ወንድሙን ፡
የማይወድ ፡ ያላየውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሊወ
፳፩ ደው ፡ እንዴት ፡ ይችላል ? እግዚአብሔርንም ፡
የሚወድ ፡ ወንድሙን ፡ ደግሞ ፡ እንዲወድ ፡
ይህች ፡ ትእዛዝ ፡ ከእርሱ ፡ አለችን ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በኢየሱስ ፡ የሚያ
ምን ፡ ሁሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተወልዶአል ÷
ወላጁንም ፡ የሚወድ ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ የተወለ
፪ ደውን ፡ ደግሞ ፡ ይወዳል ። እግዚአብሔርን ፡
ስንወድ ፡ ትእዛዛቱንም ፡ ስናደርግ ፡ የእግዚአ
ብሔርን ፡ ልጆች ፡ እንድንወድ ፡ በዚህ ፡ እናው
፫ ቃለን ። ትእዛዛቱን ፡ ልንጠብቅ ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ ፍቅር ፡ ይህ ፡ ነውና ፤ ትእዛዛቱም ፡ ከባ
፬ ዶች ፡ አይደሉም ። ከእግዚአብሔር ፡ የተወለደ ፡
ሁሉ ፡ ዓለምን ፡ ያሸንፋልና ፤ ዓለምንም ፡ የሚ
፭ ያሸንፈው ፡ እምነታችን ፡ ነው ። ኢየሱስም ፡
የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሚያምን ፡
በቀር ፡ ዓለምን ፡ የሚያሸንፍ ፡ ማን ፡ ነው ?
፮ በውኃና ፡ በደም ፡ የመጣ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እር
ሱም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ በውኃውና ፡ በደሙ ፡
፯ እንጂ ፡ በውኃው ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። መንፈ
ስም ፡ እውነት ፡ ነውና ፡ የሚመሰክረው ፡ መንፈስ ፡
፰ ነው ። የሚመሰክሩት ፡ መንፈሱና ፡ ውኃው ፡
ደሙም ፡ ሦስት ፡ ናቸውና ፤ ሦስቱም ፡ በአንድ ፡
፱ ይስማማሉ ። የሰውን ፡ ምስክር ፡ ብንቀበል ፡
የእግዚአብሔር ፡ ምስክር ፡ ከእርሱ ፡ ይልቅ ፡
ይበልጣል ፤ ስለ ፡ ልጁ ፡ የመሰከረው ፡ የእግዚአ
፲ ብሔር ፡ ምስክር ፡ ይህ ፡ ነውና ። በእግዚአብ
ሔር ፡ ልጅ ፡ የሚያምን ፡ በነፍሱ ፡ ምስክር ፡
አለው ፤ በእግዚአብሔር ፡ የማያምን ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ስለ ፡ ልጁ ፡ የመሰከረውን ፡ ምስክር ፡
ስላላመነ ፡ ሐሰተኛ ፡ አድርጎታል ። እግዚአብ ፲፩
ሔርም ፡ የዘላለምን ፡ ሕይወት ፡ እንደ ፡ ሰጠን ፡
ይህም ፡ ሕይወት ፡ በልጁ ፡ እንዳለ ፡ ምስክሩ ፡
ይህ ፡ ነው ። ልጁ ፡ ያለው ፡ ሕይወት ፡ አለው ፤ ፲፪
የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የሌለው ፡ ሕይወት ፡
የለውም ።
የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ እንዳላችሁ ፡ ታውቁ ፡ ፲፫
ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ስም ፡ ለምታ
ምኑ ፡ ይህን ፡ ጽፌላችኋለሁ ። በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ፲፬
ያለን ፡ ድፍረት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡
እንዳች ፡ ብንለምን ፡ ይሰማናል ። የምንለም ፲፭
ነውንም ፡ ሁሉ ፡ እንዲሰማልን ፡ ብናውቅ ፡ ከእ
ርሱ ፡ የለመነውን ፡ ልመና ፡ እንደ ፡ ተቀበልን ፡
እናውቃለን ። ማንም ፡ ወንድሙን ፡ ሞት ፡ የማ ፲፮
ይገባውን ፡ ኃጢአት ፡ ሲያደርግ ፡ ቢያየው ፡ ይለ
ምን ÷ ሞትም ፡ የማይገባውን ፡ ኃጢአት ፡ ላደ
ረጉት ፡ ሕይወት ፡ ይሰጥለታል ። ሞት ፡ የሚገ
ባው ፡ ኃጢአት ፡ አለ ፤ ስለዚያ ፡ እንዲጠይቅ ፡
አልልም ። ዓመፃ ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ÷ ፲፯
ሞትም ፡ የማይገባው ፡ ኃጢአት ፡ አለ ።
ከእግዚአብሔር ፡ የተወለደ ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአ ፲፰
ትን ፡ እንዳያደርግ ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡
የተወለደው ፡ ራሱን ፡ እንዲጠብቅ ፡ ክፉውም ፡
እንዳይነካው ፡ እናውቃለን ።
ከእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆንን ፡ ዓለምም ፡ ፲፱
በሞላው ፡ በክፉው ፡ እንደ ፡ ተያዘ ፡ እናውቃ
ለን ።
የእግዚአብሔርም ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ መጣ ÷ እው ፳
ነተኛም ፡ የሆነውን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ልቡናን ፡
እንደ ፡ ሰጠን ፡ እናውቃለን ፤ እውነተኛም ፡ በሆ
ነው ፡ በእርሱ ፡ አለን ÷ እርሱም ፡ ልጁ ፡ ኢየ
ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። እርሱ ፡ እውነተኛ ፡
አምላክና ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ ነው ። ልጆች ፡ ፳፩
ሆይ ÷ ከጣዖታት ፡ ራሳችሁን ፡ ጠብቁ ።

# ሁለተኛይቱ ፡ የሐዋርያው ፡ የዮሐንስ ፡ መልእክት ።

፩፡፪ በእኛ ፡ ስለሚኖርና ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ስዘላለም ፡
ስለሚሆን ፡ እውነት ÷ እኔ ፡ ሽማግሌው ፡ በእው
ነት ፡ ለምወዳቸውና ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ ሳልሆን ፡ እው
ነትን ፡ የሚያውቁ ፡ ሁሉ ፡ ደግሞ ፡ ለሚወዱአ
ቸው ፡ ለተመረጠች ፡ እመቤትና ፡ ለልጆችዋ ፤
ከእግዚአብሔር ፡ አብና ፡ ከአብ ፡ ልጅ ፡ ከኢየ ፫
ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ምሕረት ፡ ሰላምም ፡ በእ
ውነትና ፡ በፍቅር ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ይሆናሉ ።
ትእዛዝን ፡ ከአብ ፡ እንደ ፡ ተቀበልን ፡ ከልጆ ፬
ችሽ ፡ በእውነት ፡ የሚሄዱ ፡ እንዳንዶችን ፡ ስለ ፡

፬። ፳፡ ም. ፪ ÷ ፱ ። ፳፩፡ ማር. ፲፪ ÷ ፳፱—፴፩ ።
፭። ፩፡ ዮሐ. ፩ ÷ ፲፪ ፡ ፲፫ ፡ ፰ ÷ ፵፪ ። ፫፡ ዮሐ. ፲፬ ÷ ፲፭ ። ፬፡ ዮሐ. ፲፮ ÷ ፴፫ ። ፮፡ ዮሐ. ፲፱ ÷ ፴፬ ። ፯፡ ዮሐ. ፲፭ ÷ ፳፮ ። ፱፡ ዮሐ. ፰ ÷ ፲፯ ፡ ፲፰ ፤ ማቴ. ፫ ÷ ፲፯ ። ፲፡ ሮሜ ፰ ÷ ፲፮ ። ፲፩፡ ዮሐ. ፩ ÷ ፬ ። ፲፪፡ ዮሐ. ፫ ÷ ፴፮ ። ፲፫፡ ዮሐ. ፳ ÷ ፴፩ ። ፲፬፡ ም. ፫ ÷ ፳፪ ፤ ፳፪ ። ፲፮፡ ማቴ. ፲፪ ÷ ፴፩ ። ፲፰፡ ም. ፫ ÷ ፱ ፤ ዮሐ. ፲፯ ÷ ፲፭ ። ፲፱፡ ሉቃ. ፬ ÷ ፭ ፡ ፮ ። ፳፡ ዮሐ. ፲፯ ÷ ፫ ። ፳፩፡ ፩ ቆሮ. ፲ ÷ ፲፬ ።
፩፡ ፫ ዮሐ. ፩ ። ፫፡ ፩ ጢሞ. ፩ ÷ ፪ ። ፬፡ ፫ ዮሐ. ፫ ።

፬፤ አገኘኋቸው ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ። አሁንም ፥
እመቤት ፡ ሆይ ፥ አርስ ፡ በርሳችን ፡ እንድንዋ
ደድ ፡ እለምንሻለሁ ፤ ይህች ፡ ከመጀመሪያ ፡
በእኛ ፡ ዘንድ ፡ የነበረች ፡ ትእዛዝ ፡ ናት ፡ እንጂ ፡
አዲስ ፡ ትእዛዝን ፡ እንደምጽፍልሽ ፡ አይደለም ።
፭፤ እንደ ፡ ትእዛዛቱም ፡ እንሄድ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ፍቅር ፡
ነው ፤ ከመጀመሪያ ፡ እንደ ፡ ሰማችሁ ፥ በእርስዋ ፡
፮፤ ትሄዱ ፡ ዘንድ ፡ ትእዛዙ ፡ ይህች ፡ ናት ። ብዙ ፡
አሳቾች ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ገብተዋልና ፡ እነርሱም ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡
የማያምኑ ፡ ናቸው ፤ ይህ ፡ አሳቹና ፡ የክርስቶስ ፡
፯፤ ተቃዋሚው ፡ ነው ። ሙሉ ፡ ደመወዝን ፡ እን
ድትቀበሉ ፡ እንጂ ፡ የሠራችሁትን ፡ እንዳታ
፰፤ ጠፉ ፡ ስራሳችሁ ፡ ተጠንቀቁ ። ለሚወጣ ፡ ሁሉ ፡
በክርስቶስም ፡ ትምህርት ፡ ለማይኖር ፡ ሰው ፡
አምላክ ፡ የለውም ፤ በክርስቶስ ፡ ትምህርት ፡ ለሚ
ኖር ፡ አብና ፡ ወልድ ፡ አሉት ። ማንም ፡ ወደ ፡ ፲፤
እናንተ ፡ ቢመጣ ፡ ይህንም ፡ ትምህርት ፡ ባያ
መጣ ፡ በቤታችሁ ፡ አትቀበሉት ፡ ሰላምም ፡
አትበሉት ፤ ሰላም ፡ የሚለው ፡ ሰው ፡ በክፉ ፡ ፲፩፤
ሥራው ፡ ይካፈላልና ።
እንድጽፍላችሁ ፡ የምፈልገው ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ፲፪፤
ሳለኝ ፡ በወረቀትና ፡ በቀለም ፡ ልጽፈው ፡ አል
ወድም ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ ደስታችሁ ፡ ፍጹም ፡ እንዲ
ሆን ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ልመጣ ፡ አፍ ፡ ለአፍም ፡
ልናገራችሁ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።
የተመረጠችው ፡ የእኅትሽ ፡ ልጆች ፡ ሰላምታ ፡ ፲፫፤
ያቀርቡልሻል ።

# ሦስተኛይቱ ፡ የሐዋርያው ፡ የዮሐንስ ፡ መልእክት ።

፩፤ ሽማግሌው ፡ በእውነት ፡ እኔ ፡ ለምወደው ፡
ለተወደደው ፡ ለጋይዮስ ።
፪፤ ወዳጅ ፡ ሆይ ፥ ነፍስህ ፡ እንደሚከናወን ፥ በነ
ገር ፡ ሁሉ ፡ እንዲከናወንልህና ፡ ጤና ፡ እንዲኖ
፫፤ ርህ ፡ እጸልያለሁ ። ወንድሞች ፡ መጥተው ፡
አንተ ፡ ለእውነት ፡ እንደምትሄድ ፡ ስለ ፡ እውነ
ትህ ፡ ሲመሰክሩ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎኛልና ።
፬፤ ልጆቼ ፡ በእውነት ፡ እንዲሄዱ ፡ ከመስማት ፡
ይልቅ ፡ የሚበልጥ ፡ ደስታ ፡ የለኝም ።
፭፤ ወዳጅ ፡ ሆይ ፥ ምንም ፡ እንግዶች ፡ ቢሆኑ ፥
ለወንድሞች ፡ በምታደርገው ፡ ሁሉ ፡ የታመነ ፡
፮፤ ሥራ ፡ ትሠራለህ ፥ እነርሱም ፡ በማኅበር ፡ ፊት ፡
ስለ ፡ ፍቅርህ ፡ መሰከረዋል ፤ ለእግዚአብሔር ፡
እንደሚገባ ፡ አድርገህ ፡ በጕዞአቸው ፡ ብትረዳ ፡
፯፤ መልካም ፡ ታደርጋለህ ፤ ከአሕዛብ ፡ አንዳች ፡
፰፤ ሳይቀበሉ ፡ ስለ ፡ ስሙ ፡ ወጥተዋልና ። እንግ
ዲህ ፡ ከእውነት ፡ ጋር ፡ አብረን ፡ እንድንሠራ ፡
እኛ ፡ እንዲህ ፡ ያሉትን ፡ በእንግድነት ፡ ልንቀ
በል ፡ ይገባናል ።
፱፤ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ጻፍሁ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡
ዋናቸው ፡ ሊሆን ፡ የሚወድ ፡ ዲዮጥራጢስ ፡
፲፤ አይቀበለንም ። ስለዚህ ፥ እኔ ፥ ብመጣ ፥ በእኛ ፡
ላይ ፡ በክፉ ፡ ቃል ፡ እየለፈለፈ ፡ የሚያደርገውን ፡
ሥራውን ፡ አሳስበለሁ ፤ ይህም ፡ ሳይበቃው ፡
እርሱ ፡ ራሱ ፡ ወንድሞችን ፡ አይቀበልም ፥ ሊቀ
በሉአቸውም ፡ የሚወዱትን ፡ ከልክሎ ፡ ከቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ያወጣቸዋል ።
ወዳጅ ፡ ሆይ ፥ በጎ ፡ የሆነውን ፡ እንጂ ፡ ክፉን ፡ ፲፩፤
አትምሰል ። በጎ ፡ የሚያደርግ ፡ ከእግዚአብ
ሔር ፡ ነው ፤ ክፉን ፡ የሚያደርግ ፡ ግን ፡ እግዚ
አብሔርን ፡ አላየውም ። ለድሜጥሮስ ፡ ሁሉ ፡ ፲፪፤
ይመሰክሩለታል ፥ እውነት ፡ ራስዋም ፡ ትመሰክ
ርለታለች ፤ እኛም ፡ ደግሞ ፡ እንመሰክርለታለን ፥
ምስክርነታችንም ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታው
ቃላችሁ ።
ልጽፍልህ ፡ የምፈልገው ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ነበ ፲፫፤
ረኝ ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ በቀለምና ፡ በብርዕ ፡ ልጽፍልህ ፡
አልወድም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ወዲያው ፡ ላይህ ፡ ፲፬፤
ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ፥ አፍ ፡ ለአፍም ፡ እንነጋገ
ራለን ።
ሰላም ፡ ለአንተ ፡ ይሁን ። ወዳጆች ፡ ሰላምታ ፡ ፲፭፤
ያቀርቡልሃል ። ወዳጆችን ፡ በየስማቸው ፡ እየ
ጠራህ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርብልኝ ።

# የሐዋርያው ፡ የያዕቆብ ፡ መልእክት ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩፤ የእግዚአብሔርና ፡ የጌታ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስ
ቶስ ፡ ባሪያ ፡ ያዕቆብ ፡ ለተበተኑ ፡ ለአሥራ ፡
ሁለቱ ፡ ወገኖች ፤ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይሁን ።
ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ የእምነታችሁ ፡ መፈተን ፡ ፪፤
ትዕግሥትን ፡ እንዲያደርግላችሁ ፡ አውቃችሁ ፥
ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተና ፡ ሲደርስባችሁ ፡ እንደ ፡ ሙሉ ፡

፬፤ ፩ ዮሐ ፪ ፥ ፯ ። ፭፤ ፩ ዮሐ ፭ ፥ ፫ ። ፯፤ ፩ ዮሐ ፬ ፥ ፩–፫ ። ፱፤ ፩ ዮሐ ፪ ፥ ፳፫ ። ፲፤ ፪ ተሰ ፫ ፥ ፮ ።
፲፪፤ ፫ ዮሐ ፲፫ ፡ ፲፬ ።

፩፤ ፪ ዮሐ ፩ ። ፫፤ ፪ ዮሐ ፬ ። ፭፤ ማቴ ፳፭ ፥ ፴፭ ፤ ገላ ፮ ፥ ፲ ፤ ዕብ ፲፫ ፥ ፪ ። ፯፤ ቲቶ ፫ ፥ ፲፫ ። ፰፤ ፩ ቆሮ
፱ ፥ ፲፪ ፡ ፲፭ ። ፲፩፤ ፩ ዮሐ ፪ ፥ ፳፱ ፤ ፫ ፥ ፮ ። ፲፪፤ ዮሐ ፳፩ ፥ ፳፬ ። ፲፫ ፡ ፲፬፤ ፪ ዮሐ ፲፪ ።

፩፡ ፩፤ የሐዋ ፲፪ ፥ ፲፯ ፤ ገላ ፩ ፥ ፲፱ ፤ ሐዋ ፩ ፥ ፩ ። ፪፤ ሮሜ ፭ ፥ ፫ ።

፬፤ ደስታ፡ ቍጠሩት ። ትዕግሥትም፡ ምንም፡
የሚጐድላችሁ፡ ሳይኖር፡ ፍጹማንና፡ ምሉዓን፡
ትሆኑ፡ ዘንድ፡ ሥራውን፡ ይፈጽም ።
፭፤ ከእናንተ፡ ግን፡ ማንም፡ ጥበብ፡ ቢጐድለው፡÷
ሳይነቅፍ፡ በልግስና፡ ለሁሉ፡ የሚሰጠውን፡
እግዚአብሔርን፡ ይለምን÷ ለእርሱም፡ ይሰጠ
፮፤ ዋል ። ነገር፡ ግን፡ በምንም፡ ሳይጠራጠር፡
በእምነት፡ ይለምን ፤ የሚጠራጠር፡ ሰው፡ በነ
ፋስ፡ የተገፋና፡ የተነቃነቀ፡ የባሕርን፡ ማዕበል፡
፯፰፤ ይመስላልና ። ሁለት፡ አሳብ፡ ላለው፡ በመን
ገዱም፡ ሁሉ፡ ለሚወላውል፡ ለዚያ፡ ሰው፡
ከጌታ፡ ዘንድ፡ አንዳች፡ እንዲያገኝ፡ አይምሰ
ለው ።
፱፤ የተዋረደው፡ ወንድም፡ ግን፡ በከፍታው÷
ባለ፡ ጠጋም፡ በውርደቱ፡ ይመካ ፤ እንደ፡ ሣር፡
፲፩፤ አበባ፡ ያልፋልና ። ፀሐይ፡ ከትኵሳት፡ ጋር፡
ይወጣልና÷ ሣርንም፡ ያጠወልጋልና÷ አበባ
ውም፡ ይረግፋልና÷የመልኩም፡ ውበት፡ ይጠ
ፋልና ፤ እንዲሁ፡ ደግሞ፡ ባለ፡ ጠጋው፡ በመ
ንገዱ፡ ይዝላል ።
፲፪፤ በፈተና፡ የሚጸና፡ ሰው፡ የተባረከ፡ ነው ፤
ከተፈተነ፡ በኋላ፡ ለሚወዱት፡ ተስፋ፡ ስለ፡
እርሱ፡ የሰጣቸውን፡ የሕይወትን፡ አክሊል፡
፲፫፤ ይቀበላልና ። ማንም፡ ሲፈተን፡— በእግዚአብ
ሔር፡ እፈተናለሁ፡ አይበል ፤ እግዚአብሔር፡
በክፉ፡ አይፈተንምና ፤ እርሱ፡ ራሱስ፡ ማን
፲፬፤ ንም፡ አይፈትንም ። ነገር፡ ግን፡ እያንዳንዱ፡
በራሱ፡ ምኞት፡ ሲሳብና፡ ሲታለል፡ ይፈተናል ።
፲፭፤ ከዚህ፡ በኋላ፡ ምኞት፡ ፀንሳ፡ ኃጢአትን፡ ትወ
ልዳለች ፤ ኃጢአትም፡ ካደገች፡ በኋላ፡ ሞትን፡
ትወልዳለች ።
፲፮፤ የተወደዳችሁ፡ ወንድሞቼ፡ ሆይ÷ አትሳቱ ።
፲፯፤ በጎ፡ ስጦታ፡ ሁሉ፡ ፍጹምም፡ በረከት፡ ሁሉ፡
ከላይ፡ ናቸው÷ መለወጥም፡ በእርሱ፡ ዘንድ፡
ከሌለ፡ በመዞርም፡ የተደረገ፡ ጥላ፡ በእርሱ፡
ዘንድ፡ ከሌለ፡ ከብርሃናት፡ አባት፡ ይወርዳሉ ።
፲፰፤ ለፍጥረቱ፡ የበኵራት፡ ዓይነት፡ እንድንሆን፡
በእውነት፡ ቃል፡ አስቦ፡ ወለደን ።
፲፱፤ ስለዚህ÷ የተወደዳችሁ፡ ወንድሞቼ፡ ሆይ÷
ሰው፡ ሁሉ፡ ለመስማት፡ የፈጠነ፡ ለመናገርም፡
፳፤ የዘገየ፡ ለቍጣም፡ የዘገየ፡ ይሁን ፤ የሰው፡
ቍጣ፡ የእግዚአብሔርን፡ ጽድቅ፡ አይሠራ
፳፩፤ ምና ። ስለዚህ፡ ርኵሰትን፡ ሁሉ፡ የክፋትንም፡
ትርፍ፡ አስወግዳችሁ÷ ነፍሳችሁን፡ ማዳን፡
የሚችለውን፡ በውስጣችሁም፡ የተተከለውን፡
ቃል፡ በየዋህነት፡ ተቀበሉ ።
፳፪፤ ቃሉን፡ የምታደርጉ፡ ሁኑ፡ እንጂ፡ ራሳች
ሁን፡ እያሳታችሁ፡ የምትሰሙ፡ ብቻ፡ አትሁኑ ።

ቃሉን፡ የሚሰማ፡ የማያደርገውም፡ ቢኖር፡ የተ ፳፫፤
ፈጥሮ፡ ፊቱን፡ በመስተዋት፡ የሚያይን፡ ሰው፡
ይመስላል ፤ ራሱን፡ አይቶ፡ ይሄዳልና÷ ወዲያ ፳፬፤
ውም፡ እንደ፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ ይረሳል ። ነገር፡ ፳፭፤
ግን፡ ነጻ፡ የሚያወጣውን፡ ፍጹሙን፡ ሕግ፡
ተመልክቶ፡ የሚጸናበት÷ ሥራንም፡ የሚሠራ፡
እንጂ፡ ሰምቶ፡ የሚረሳ፡ ያልሆነው÷ በሥራው፡
የተባረከ፡ ይሆናል ።
እንደበቱን፡ ሳይገታ፡ ልቡን፡ እያሳተ፡ እግዚአ ፳፮፤
ብሔርን፡ የሚያመልክ፡ የሚመስለው፡ ማንም፡
ቢኖር፡ የእርሱ፡ አምልኮ፡ ከንቱ፡ ነው ። ንጹሕ፡ ፳፯፤
የሆነ፡ ነውርም፡ የሌለበት፡ አምልኮ፡ በእግዚ
አብሔር፡ አብ፡ ዘንድ፡ ይህ፡ ነው ፤ ወላጆች፡
የሌላቸውን፡ ልጆች፡ ባልቴቶችንም፡ በመከራ
ቸው፡ መጠየቅ÷ በዓለምም፡ ከሚገኝ፡ እድፍ፡
ሰውነቱን፡ መጠበቅ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ወንድሞቼ፡ ሆይ÷ በክብር፡ ጌታ፡ በጌታችን፡ ፩፤
በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ያለውን፡ እምነት፡ ለሰው፡
ፊት፡ በማድላት፡ አትያዙ ። የወርቅ፡ ቀለበት፡ ፪፤
ያደረገና፡ የጌጥ፡ ልብስ፡ የለበሰ፡ ሰው፡ ወደ፡
ጉባኤአችሁ፡ ቢገባ÷ እድፍ፡ ልብስም፡ የለበሰ፡
ድሀ፡ ሰው፡ ደግሞ፡ ቢገባ÷ የጌጥ፡ ልብስም፡ ፫፤
የለበሰውን፡ ተመልክታችሁ፡— አንተስ፡ በዚህ፡
በመልካም፡ ስፍራ፡ ተቀመጥ፡ ብትሉት÷ ድሀ
ውንም፡— አንተስ፡ ወደዚያ፡ ቁም፡ ወይም፡
ከእግሬ፡ መረገጫ፡ በታች፡ ተቀመጥ፡ ብትሉት÷
ራሳችሁን፡ መለያየታችሁ፡ አይደለምን ? ክፉ፡ ፬፤
አሳብ፡ ያላቸውም፡ ዳኞች፡ መሆናችሁ፡ አይ
ደለምን ? የተወደዳችሁ፡ ወንድሞቼ፡ ሆይ÷ ፭፤
ስሙ ፤ እግዚአብሔር፡ በእምነት፡ ባለ፡ ጠጎች፡
እንዲሆኑ፡ ለሚወዱትም፡ ተስፋ፡ ስለ፡ እርሱ፡
የሰጣቸውን፡ መንግሥት፡ እንዲወርሱ፡ የዚ
ህን፡ ዓለም፡ ድሆች፡ አልመረጠምን ? እናንተ፡ ፮፤
ግን፡ ድሆችን፡ አዋረዳችሁ ። ባለ፡ ጠጎቹ፡ የሚ
ያስጨንቁአችሁ፡ አይደሉምን ? ወደ፡ ፍርድ፡
ቤትም፡ የሚጐትቱአችሁ፡ እነርሱ፡ አይደሉ
ምን ? የተጠራችሁበትን፡ መልካሙን፡ ስም፡ ፯፤
የሚሰድቡ፡ እነርሱ፡ አይደሉምን ?
ነገር፡ ግን፡ መጽሐፍ፡— ባልንጀራህን፡ እንደ፡ ፰፤
ራስህ፡ ውደድ፡ እንደሚል፡ የንጉሥን፡ ሕግ፡
ብትፈጽሙ፡ መልካም፡ ታደርጋላችሁ ፤ ለሰው፡ ፱፤
ፊት፡ ግን፡ ብታደሉ፡ ኃጢአትን፡ ትሠራላችሁ÷
ሕግም፡ እንደ፡ ተላላፊዎች፡ ይወቅሳችኋል ።
ሕግን፡ ሁሉ፡ የሚጠብቅ÷ ነገር፡ ግን፡ በአንዱ፡ ፲፤
የሚሰናከል፡ ማንም፡ ቢኖር፡ በሁሉ፡ በደለኛ፡
ይሆናል ፤ አታመንዝር፡ ያለው፡ ደግሞ፡— አት ፲፩፤

፩። ፭፤ ምሳ. ፪÷፫—፮ ። ፮፤ ማር. ፲፩÷፳፬፤ሉቃ. ፰÷፲፱ ። ፱፤ ም. ፪÷፭ ። ፲፤ ፩ ጴጥ. ፩÷፳፬ ። ፲፪፤ ኢዮ.
፭÷፲፯ ። ፲፫፤ ማቴ. ፲÷፳፪፤፩ ጢሞ. ፩÷፲፪ ። ፲፭፤ ሮሜ. ፮÷፳፫ ። ፲፯፤ ዮሐ. ፫÷፳፯፤መዝ. ፻፴፮÷፯፤ሚል.
፫÷፮ ። ፲፰፤ ዮሐ. ፩÷፲፫፤ሮሜ. ፰÷፲፱—፳፫ ። ፲፱፤ ምሳ. ፲÷፲፱፤፲፱÷፳፱ ። ፳፩፤ ቆላ. ፫÷፰ ። ፳፪፤ ማቴ.
፯÷፳፮፤ሮሜ. ፪÷፲፫ ። ፳፭፤ ሮሜ. ፰÷፪፤ሉቃ. ፲፩÷፳፰ ። ፳፯፤ መዝ. ፷፰÷፭ ።
፪። ፩፤ ዘዳግ. ፩÷፲፯ ። ፪፤ ዮሐ. ፯÷፳፬ ። ፭፤ ፩ ቆሮ. ፩÷፳፯—፳፰፤ሉቃ. ፲፪÷፳፩ ። ፰፤ ዘሌዋ. ፲፱÷፲፰፤ማር.
፲፪÷፴፩ ። ፱፤ ሥራ. ፩ ። ፲፤ ማቴ. ፭÷፲፱ ። ፲፩፤ ዘፀአ. ፳÷፲፫፤፲፬ ።

ግደል፡ብሎአልና ፤ ባታመነዝርም ፥ ነገር፡ግን፡
፲፪፤ ብትገድል ፥ ሕግን፡ተላላፊ፡ሆነሃል ። በነጻነት፡
ሕግ፡ፍርድን፡ይቀበሉ፡ዘንድ፡እንዳላቸው፡
ሰዎች፡እንዲሁ፡ተናገሩ ፥ እንዲሁም፡አድርጉ ።
፲፫፤ ምሕረትን፡ለማያደርግ፡ ምሕረት፡የሌለበት፡
ፍርድ፡ይሆናልና ፤ ምሕረትም፡በፍርድ፡ላይ፡
ይመካል ።
፲፬፤ ወንድሞቼ፡ሆይ ፥ እምነት፡አለኝ፡የሚል ፥
ሥራ፡ግን፡የሌለው፡ሰው፡ቢኖር፡ምን፡
ይጠቅመዋል ? እምነቱስ፡ሊያድነው፡ይችላ
፲፭፤ ልን ? ወንድም፡ወይም፡እኅት፡ራቁታቸውን፡
፲፮፤ ቢሆኑ፡የዕለት፡ምግብንም፡ቢያጡ ፥ ከእናንተ፡
አንዱም ፦ በደኅና፡ሂዱ ፥ እሳት፡ሙቁ ፥ ጥገ
ቡም፡ቢላቸው፡ለሰውነት፡ግን፡የሚያስፈል
ጉትን፡በትሰጡአቸው፡ምን፡ይጠቅማቸዋል ?
፲፯፤ እንደዚሁም፡ሥራ፡የሌለው፡እምነት፡ቢኖር፡
በራሱ፡የሞተ፡ነው ።
፲፰፤ ነገር፡ግን፡አንድ፡ሰው ፦ አንተ፡እምነት፡
አለህ፡እኔም፡ሥራ፡አለኝ ፤ እምነትህን፡ከሥ
ራህ፡ለይተህ፡አሳየኝ ፥ እኔም፡እምነቴን፡በሥ
፲፱፤ ራዬ፡አሳይሃለሁ፡ይላል ። እግዚአብሔር፡
አንድ፡እንደ፡ሆነ፡አንተ፡ታምናለህ ፤ መል
ካም፡ታደርጋለህ ፤ አጋንንት፡ደግሞ፡ያምናሉ፡
፳፤ ይንቀጠቀጡማል ። አንተ፡ከንቱ፡ሰው ፥ እም
ነት፡ከሥራ፡ተለይቶ፡የሞተ፡መሆኑን፡ልታ
፳፩፤ ውቅ፡ትወዳለህን ? አበታችን፡አብርሃም፡
ልጁን፡ይስሐቅን፡በመሠዊያው፡ባቀረበ፡
፳፪፤ ጊዜ፡በሥራ፡የጸደቀ፡አልነበረምን ? እምነት፡
ከሥራው፡ጋር፡አብሮ፡ያደርግ፡እንደ፡ነበረ ፥
በሥራም፡እምነት፡እንደ፡ተፈጸመ፡ትመለከ
፳፫፤ ታለህን ? መጽሐፍም ፦ አብርሃምም፡እግዚ
አብሔርን፡አመነ፡ጽድቅም፡ሆኖ፡ተቈጠረ
ለት፡ያለው፡ተፈጸመ ፤ የእግዚአብሔርም፡
፳፬፤ ወዳጅ፡ተባለ ። ሰው፡በእምነት፡ብቻ፡ሳይ
፳፭፤ ሆን፡በሥራ፡እንዲጸድቅ፡ታያላችሁ ። እንደ
ዚሁም፡ጋለሞታይቱ፡ረዓብ፡ደግሞ፡መልእ
ክተኞቹን፡ተቀብላ፡በሌላ፡መንገድ፡በሰደደ
፳፮፤ ቻቸው፡ጊዜ፡በሥራ፡አልጸደቀችምን ? ከነ
ፍስ፡የተለየ፡ሥጋ፡የሞተ፡እንደ፡ሆነ፡እን
ዲሁ፡ደግሞ፡ከሥራ፡የተለየ፡እምነት፡የሞተ፡
ነው ።

## ምዕራፍ፡፫ ።

፩፤ ወንድሞቼ፡ሆይ ፥ እናንተ፡ብዙዎች፡አስ
ተማሪዎች፡አይሁኑ ፥ የበለጠን፡ፍርድ፡እን
፪፤ ድንቀበል፡ታውቃላችሁና ። ሁላችን፡በብዙ፡
ነገር፡እንሰናከላለንና ፤ በቃል፡የማይሰናከል፡
ማንም፡ቢኖር፡እርሱ፡ሥጋውን፡ሁሉ፡ደግሞ፡
ሊገታ፡የሚችል፡ፍጹም፡ሰው፡ነው ። እነሆ ፥ ፫፤
ፈረሶች፡ይታዘዙልን፡ዘንድ፡ልጓም፡በአፋ
ቸው፡ውስጥ፡እናገባለን ፥ ሥጋቸውንም፡ሁሉ፡
እንመራለን ። እነሆ ፥ መርከቦች፡ደግሞ፡ ፬፤
ይህን፡ያህል፡ታላቅ፡ቢሆኑ፡በሀውሉ፡ነፋ
ስም፡ቢነዱ ፥ የመሪ፡ፈቃድ፡ወደሚወደው፡
ስፍራ፡እጅግ፡ታናሽ፡በሆነ፡መቅዘፊያ፡ይመ
ራሉ ። እንዲሁም፡አንደበት፡ደግሞ፡ትንሽ፡ ፭፤
ብልት፡ሆኖ፡በታላላቅ፡ነገር፡ይመካል ።
እነሆ ፥ ትንሽ፡እሳት፡እንዴት፡ያለ፡ትልቅ፡
ጫካ፡ያቃጥላል ።
አንደበትም፡እሳት፡ነው ። አንደበት፡በብ ፮፤
ልቶቻችን፡መካከል፡ዓመፀኛ፡ዓለም፡ሆኖ
አል ፤ ሥጋን፡ሁሉ፡ያሳድፋልና ፥ የፍጥረት
ንም፡ሩጫ፡ያቃጥላል ፥ በገሃነምም፡ይቃጠ
ላል ። የአራዊትና፡የወፎች፡የተንቀሳቃሾ ፯፤
ችና፡በባሕር፡ያለ፡የፍጥረት፡ወገን፡ሁሉ፡
በሰው፡ይገራል ፥ ደግሞ፡ተገርቶአል ፤ ነገር፡ ፰፤
ግን፡አንደበትን፡ሊገራ፡ማንም፡ሰው፡አይ
ችልም ፤ የሚገድል፡መርዝ፡የሞላበት፡ወላ
ዋይ፡ክፉት፡ነው ። በእርሱ፡ጌታንና፡አብን፡ ፱፤
እንባርካለን ፤ በእርሱም፡እንደ፡እግዚአብ
ሔር፡ምሳሌ፡የተፈጠሩትን፡ሰዎች፡እንረግ
ማለን ፤ ከአንድ፡አፍ፡በረከትና፡መርገም፡ ፲፤
ይወጣሉ ። ወንድሞቼ፡ሆይ ፥ ይህ፡እንዲሁ፡
ሊሆን፡አይገባም ። ምንጭስ፡ከአንድ፡አፍ፡ ፲፩፤
የሚጣፍጥንና፡የሚመርን፡ውኃ፡ያመነጫ
ልን ? ወንድሞቼ፡ሆይ ፥ በለስ፡ወይራን፡ ፲፪፤
ወይስ፡ወይን፡በለስን፡ልታፈራ፡ትችላለችን ?
ከጨው፡ውኃም፡ጣፋጭ፡ውኃ፡አይወጣም ።
ከእናንተ፡ጥበበኛና፡አስተዋይ፡ማን፡ነው ? ፲፫፤
በመልካም፡አንዋዋሩ፡ሥራውን፡በጥበብ፡
የዋህነት፡ያሳይ ። ነገር፡ግን፡መራራ፡ቅንዓ ፲፬፤
ትና፡አድመኛነት፡በልባችሁ፡ቢኖርባችሁ ፥
አትመኩ፡በእውነትም፡ላይ፡አትዋሹ ። ይህ፡ ፲፭፤
ጥበብ፡ከላይ፡የሚወርድ፡አይደለም ፤ ነገር፡
ግን፡የምድር፡ነው ፥ የሥጋም፡ነው ፥ የአጋንን
ትም፡ነው ፤ ቅንዓትና፡አድመኛነት፡ባሉበት፡ ፲፮፤
ስፍራ፡በዚያ፡ሁከትና፡ክፉ፡ሥራ፡ሁሉ፡
አሉና ። ላይኛይቱ፡ጥበብ፡ግን፡በመጀመሪያ፡ ፲፯፤
ንጽሕት፡ናት ፥ በኋላም፡ታራቂ ፥ ገር ፥ እሺ፡
ባይ - ምሕረትና፡በጎ፡ፍሬ፡የሞላባት ፥ ጥር
ጥርና፡ግብዝነት፡የሌለባት፡ናት ። የጽድቅም፡ ፲፰፤
ፍሬ፡ሰላምን፡ለሚያደርጉት፡ሰዎች፡በሰላም፡
ይዘራል ።

## ምዕራፍ፡፬ ።

በእናንተ፡ዘንድ፡ጦርና፡ጠብ፡ከወዴት፡ ፩፤

፪። ፲፪፤ ምዕ. ፩፥፳፭ ። ፲፫፤ ማቴ. ፭፥፯፤፳፭፥፵፩ ። ፲፬፤ ማቴ. ፯፥፳፩ ። ፲፭፤ ሉቃ. ፫፥፲፩ ። ፲፮፤ ፩ ዮሐ. ፫፥፲፯ ። ፲፰፤ ማቴ. ፯፥፲፮፡፲፯፤ገላ. ፭፥፮ ። ፲፱፤ ማር. ፩፥፳፬ ። ፳፩፤ ዘፍጥ. ፳፪፥፱—፲፪ ። ፳፪፤ ዕብ. ፲፩፥፲፯ ። ፳፫፤ ዘፍጥ. ፲፭፥፮፤ኢሳ. ፵፩፥፰ ። ፳፭፤ ኢያ. ፪፥፩—፳፩፤ዕብ. ፲፩፥፴፩ ። ፳፮፤ ጥ. ፲፮ ።
፫። ፩፤ መዝ. ፲፩፥፫፡፬ ። ፪፤ ማቴ. ፲፪፥፴፯ ። ፮፤ መዝ. ፻፳፥፫ ። ፱፤ ዘፍጥ. ፩፥፳፮ ። ፲፩፤ ምዕ. ፩፥፳፮ ። ፲፫፤ ሉቃ. ፮፥፵፭ ። ፲፰፤ ኢሳ. ፴፪፥፲፯፤ማቴ. ፭፥፱ ።
፬። ፩፤ ሮሜ ፯፥፳፫ ።

ይመጣሉ ? በብልቶቻችሁ፡ውስጥ፡ከሚዋጉ፡
፪፤ ከእነዚህ፡ከምኞቶቻችሁ፡አይደሉምን ? ትመ
ኛላችሁ፡ለእናንተም፡አይሆንም፤ ትገድላላ
ችሁ፡በብርቱም፡ትፈልጋላችሁ፣ልታገኙም፡
አትችሉም፤ ትጣላላችሁ፡ትዋጋላችሁ፡
ነገር፡ግን፡አትለምኑምና፡ለእናንተ፡አይሆ
፫፤ ንም፤ ትለምናላችሁ፣በምኞቶቻችሁም፡ትከ
ፍሉ፡ዘንድ፡በክፉ፡ትለምናላችሁና፡አትቀበ
፬፤ ሉም። አመንዝሮች፡ሆይ፣ዓለምን፡መው
ደድ፡ለእግዚአብሔር፡ጥል፡እንዲሆን፡አታ
ውቁምን ? እንግዲህ፡የዓለም፡ወዳጅ፡ሊሆን፡
የሚፈቅድ፡ሁሉ፡የእግዚአብሔር፡ጠላት፡ሆኖ
፭፤ አል። ወይስ፡መጽሐፍ፡— በእኛ፡ዘንድ፡ያሳ
ደረው፡መንፈስ፡በቅንዓት፡ይመኛል፡ያለው፡
፮፤ በከንቱ፡እንደ፡ተናገረ፡ይመስላችኋልን ? ነገር፡
ግን፡ጸጋን፡አብልጦ፡ይሰጣል፤ ስለዚህ፡— እግ
ዚአብሔር፡ትዕቢተኞችን፣ይቃወማል፣ለት
፯፤ ሑታን፡ግን፡ጸጋን፡ይሰጣል፡ይላል። እን
ግዲህ፡ለእግዚአብሔር፡ተገዙ፤ ዲያብሎስን፡
፰፤ ግን፡ተቃወሙ፡ከእናንተም፡ይሸሻል፤ ወደ፡
እግዚአብሔር፡ቅረቡ፡ወደ፡እናንተም፡ይቀር
ባል። እናንተ፡ኃጢአተኞች፣እጆቻችሁን፡
አንጹ፤ ሁለት፡አሳብም፡ያላችሁ፡እናንተ፣
፱፤ ልባችሁን፡አጥሩ። ተጨነቁና፡አዘኑ፡አልቅ
ሱም፤ ሳቃችሁ፡ወደ፡ኀዘን፡ደስታችሁም፡
፲፤ ወደ፡ትካዜ፡ይለወጥ። በጌታ፡ፊት፡ራሳች
ሁን፡አዋርዱ፡ከፍ፡ከፍም፡ያደርጋችኋል።
፲፩፤ ወንድሞች፡ሆይ፣እርስ፡በርሳችሁ፡አትተ
ማሙ። ወንድሙን፡የሚያማ፡በወንድሙም፡
የሚፈርድ፡ሕግን፡ያማል፡በሕግም፡ይፈር
ዳል፤ በሕግም፡ብትፈርድ፡ፈራጅ፡ነህ፡እንጂ፡
፲፪፤ ሕግን፡አድራጊ፡አይደለህም። ሕግን፡የሚ
ሰጥና፡የሚፈርድ፡አንድ፡ነው፤ እርሱም፡
ሊያድን፡ሊያጠፋም፡የሚችል፡ነው፤ በሌ
ላው፡ግን፡የምትፈርድ፡አንተ፡ማን፡ነህ ?
፲፫፤ አሁንም፡— ዛሬ፡ወይም፡ነገ፡ወደዚህ፡
ከተማ፡እንሄዳለን፡በዚያም፡ዓመት፡እንኖራ
ለን፡እንነግድማለን፡እናተርፍማለን፡የምትሉ፡
፲፬፤ እናንተ፣ተመልከቱ፣ነገ፡የሚሆነውን፡አታ
ውቁምና። ሕይወታችሁ፡ምንድር፡ነው ?
ጥቂት፡ጊዜ፡ታይቶ፡ኋላ፡እንደሚጠፋ፡እንፋ
፲፭፤ ሎት፡ናችሁና። በዚህ፡ፈንታ፡— ጌታ፡ቢፈ
ቅድ፡ብንኖርም፡ይህን፡ወይም፡ያን፡እናደርጋ
፲፮፤ ለን፡ማለት፡ይገባችኋል። አሁን፡ግን፡በትዕ
ቢታችሁ፡ትመካላችሁ፤ እንደዚህ፡ያለ፡ትም
፲፯፤ ክህት፡ሁሉ፡ክፉ፡ነው። እንግዲህ፡በጎ፡ለማ
ድረግ፡አውቆ፡ለማይሠራው፡ኃጢአት፡ነው።

ምዕራፍ፡፭።

አሁንም፡እናንተ፡ባለ፡ጠጎች፣ስለሚደር ፩፤
ስባችሁ፡ጭንቅ፡ዋይ፡ዋይ፡እያላችሁ፡አል
ቅሱ። ሀብታችሁ፡ተበላሽቶአል፣ልብሳች ፪፤
ሁም፡በብል፡ተበልቶአል። ወርቃችሁም፡ ፫፤
ብራችሁም፡ዝጎአል፣ዝገቱም፡ምስክር፡ይሆ
ንባችኋል፡ሥጋችሁንም፡እንደ፡እሳት፡ይበ
ላል። ለኋለኛው፡ቀን፡መዝገብን፡አከማችታ
ችኋል። እነሆ፣እርሻችሁን፡ያጨዱት፡የሠ ፬፤
ራተኞች፡ደመወዝ፡በእናንተ፡ተቀምቶ፡ይጮ
ኻል፣የአጫጆችም፡ድምፅ፡ወደ፡ጌታ፡ፀባ
ዖት፡ጆሮ፡ገብቶአል። በምድር፡ላይ፡ተቀ ፭፤
ማጥላችኋል፡በሴሰኝነትም፡ኖራችኋል፤ ለእ
ርድ፡ቀን፡እንደሚያወፍር፡ልባችሁን፡አወ
ፍራችኋል። ጻድቁን፡ኰንናችሁታል፡ገድላ ፮፤
ችሁትማል፤ እናንተን፡አይቃወምም።
እንግዲህ፣ወንድሞች፡ሆይ፣ጌታ፡እስኪ ፯፤
መጣ፡ድረስ፡ታገሡ። እነሆ፣ገበሬው፡የፊ
ተኛውንና፡የኋለኛውን፡ዝናብ፡እስኪቀበል፡
ድረስ፡እርሱን፡እየታገሠ፡የከበረውን፡የመ
ሬት፡ፍሬ፡ይጠብቃል። እናንተ፡ደግሞ፡ ፰፤
ታገሡ፣ልባችሁንም፡አጽኑ፤ የጌታ፡መም
ጣት፡ቀርቦአልና። ወንድሞች፡ሆይ፣እንዳ ፱፤
ይፈረድባችሁ፡እርስ፡በርሳችሁ፡አታጕረም
ርሙ፤ እነሆ፣ፈራጅ፡በደጅ፡ፊት፡ቆሞአል።
ወንድሞች፡ሆይ፣የመከራና፡የትዕግሥት፡ ፲፤
ምሳሌ፡የሆኑትን፡በጌታ፡ስም፡የተናገሩትን፡
ነቢያትን፡ተመልከቱ። እነሆ፣በትዕግሥት፡ ፲፩፤
የጸኑትን፡ብፁዓን፡እንላቸዋለን፤ ኢዮብ፡
እንደ፡ታገሠ፡ሰምታችኋል፣ጌታም፡እንደ፡
ፈጸመለት፡አይታችኋል፤ ጌታ፡እጅግ፡የሚ
ምር፡የሚራራም፡ነውና።
ከሁሉም፡በፊት፣ወንድሞቼ፡ሆይ፣በሰ ፲፪፤
ማይ፡ቢሆን፡በምድርም፡ቢሆን፡በሌላ፡መሐ
ላም፡ቢሆን፡በምንም፡አትማሉ፤ ነገር፡ግን፡
ከፍርድ፡በታች፡እንዳትወድቁ፡ነገራችሁ፡
አዎን፡ቢሆን፡አዎን፡ይሁን፣አይደለምም፡
ቢሆን፡አይደለም፡ይሁን።
ከእናንተ፡መከራን፡የሚቀበል፡ማንም፡ ፲፫፤
ቢኖር፡እርሱ፡ይጸልይ፤ ደስ፡የሚለውም፡
ማንም፡ቢኖር፡እርሱ፡ይዘምር። ከእናንተ፡ ፲፬፤
የታመመ፡ማንም፡ቢኖር፡የቤተ፡ክርስቲያንን፡
ሽማግሌዎች፡ወደ፡እርሱ፡ይጥራ፤ በጌታም፡
ስም፡እርሱን፡ዘይት፡ቀብተው፡ይጸልዩለት።
የእምነትም፡ጸሎት፡ድውዩን፡ያድናል፡ጌታም፡ ፲፭፤
ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም፡ሠርቶ፡እንደ፡ሆነ፡
ይሰረይለታል። እርስ፡በርሳችሁ፡በኃጢአታ ፲፮፤

፬። ፩፤ ማቴ. ፳፮÷፵፩ ፤ ሮሜ ፯÷፳፫ ፤ ፩ ጴጥ. ፪÷፲፩ ። ፫፤ ፩ ቆሮ. ፮÷፲፱ ፤ ገላ. ፭÷፲፯ ። ፮፤ ምሳ. ፫÷፴፬ ፤ ማቴ. ፳፫÷፲፪ ። ፯፤ ፩ ጴጥ. ፭÷፮ ፤ ፱ ። ፰፤ ዘካ. ፩÷፫ ፤ ኢሳ. ፩÷፲፮ ። ፱፤ ማቴ. ፭÷፬ ። ፲፤ ማቴ. ፳፫÷፲፪ ፤ ፩ ጴጥ. ፭÷፮ ። ፲፩፤ ማቴ. ፯÷፩ ። ፲፪፤ ኢሳ. ፴፫÷፳፪ ፤ ሮሜ ፲፬÷፬ ። ፲፫፤ ፲፬፤ ምሳ. ፳፯÷፩ ፤ ሉቃ. ፲፪÷፲፰—፳፤ መዝ. ፻፩÷፫ ። ፲፯፤ ሉቃ. ፲፪÷፵፯ ፤ ዮሐ. ፱÷፵፩ ፤ ፲፭÷፳፪ ።

፭። ፩፤ ሉቃ. ፮÷፳፬ ። ፪፤ ማቴ. ፮÷፲፱ ። ፬፤ ዘሌዋ. ፲፱÷፲፫ ፤ ፲፭ ። ፭፤ ሉቃ. ፲፮÷፲፱ ፤ ኤር. ፲፪÷፫ ። ፯፤ ሉቃ. ፳፩÷፲፱ ፤ ዘዳግ. ፲፩÷፲፬ ። ፰፤ ፩ ተሰ. ፫÷፲፫ ። ፲፤ ማቴ. ፭÷፲፪ ። ፲፩፤ ኢዮብ ፩÷፳፩ ፤ ፵፪ ፤ ፶፪÷፲ ፤ ፲፪ ፤ ዘፀአ. ፴፬÷፮ ። ፲፪፤ ማቴ. ፭÷፴፬—፴፯ ። ፲፫፤ መዝ. ፶፱÷፲፭ ። ፲፬፤ ማር. ፮÷፲፫ ። ፲፮፤ ምሳ. ፲፭÷፳፱ ።

ችሁ፡ ተናዘዙ ÷ ትፈወሱም ፡ ዘንድ ፡ እያንዳ
ንዱ፡ለለ፡ሌላው፡ይጸልይ ፤ የጻድቅ፡ለው፡
ጸሎት፡በሥራዋ፡እጅግ፡ኃይል፡ታደርጋለች።
፲፯፤ ኤልያስ፡እንደ፡እኛ፡የሆነ፡ሰው፡ነበረ÷ ዝና
ብም፡ እንዳይዘንብ፡ አጥብቆ፡ ጸለየ÷ በምድ
ርም፡ላይ፡ሦስት፡ዓመት፡ ከስድስት፡ ወር፡
፲፰፤ አልዘነበም ፤ ሁለተኛም፡ጸለየ÷ሰማዩም፡ዝና
ብን፡ሰጠ፡ምድሪቱም፡ፍሬዋን፡አበቀለች ።
ወንድሞቼ፡ሆይ÷ከእናንተ፡ማንም፡ከእው ፲፱፤
ነት፡ቢስት፡አንዱም፡ቢመልሰው÷ኃጢአተ ፳፤
ኛን፡ከተሳሳተበት፡መንገድ፡የሚመልሰው፡
ነፍሱን፡ከሞት፡እንዲያድን÷የኃጢአትንም፡
ብዛት፡እንዲሸፍን፡ይወቅ ።

# የያዕቆብ ፡ ወንድም ፡ የይሁዳ ፡ መልእክት ።

፩፤ የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ባሪያ፡የያዕቆብም፡
ወንድም፡የሆነ፡ይሁዳ÷በእግዚአብሔር፡አብ፡
ተወደው፡ለኢየሱስ፡ክርስቶስም፡ተጠብቀው፡
ለተጠሩ ፤
፪፤ ምሕረትና፡ሰላም፡ፍቅርም፡ይብዛላችሁ ።
፫፤ ወዳጆች፡ሆይ÷ስለምንካፈለው፡ስለ፡መዳ
ናችን፡ልጽፍላችሁ፡እጅግ፡ተግቼ፡ሳለሁ÷
ለቅዱሳን፡አንድ፡ጊዜ፡ፈጽሞ፡ስለ፡ተሰጠ፡
ሃይማኖት፡ እንድትጋደሉ፡ እየመከርኋችሁ፡
፬፤ እጽፍላችሁ፡ዘንድ፡ግድ፡ሆነብኝ ። ከብዙ፡
ጊዜ፡በፊት፡ለዚህ፡ፍርድ፡የተጻፉ፡ አንዳን
ዶች፡ሰዎች፡ሾልከው፡ገብተዋልና ፤ ኃጢአ
ተኞች፡ሆነው፡የአምላካችንን፡ጸጋ፡በሴሰኝ
ነት፡ይለውጣሉ፡ንጉሣችንንና፡ጌታችንንም፡
ብቻውን፡ያለውን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ይክ
ዳሉ ።
፭፤ ዳሩ፡ግን፡ሁሉን፡አንድ፡ጊዜ፡ፈጽሞ፡
ምንም፡የተማራችሁ፡ብትሆኑ፡ጌታ፡ከግብፅ፡
አገር፡ሕዝቡን፡አድኖ፡የማያምኑትን፡በኋላ፡
፮፤ እንዳጠፋቸው፡ላሳስባችሁ፡እወዳለሁ ። መና
ሪያቸውንም፡የተዉትን፡እንጂ፡የራሳቸውን፡
አለቅነት፡ያልጠበቁትን፡መላእክት፡በዘላለም፡
እስራት፡ከጨለማ፡በታች፡እስከ፡ታላቁ፡ቀን፡
፯፤ ፍርድ፡ድረስ፡ጠብቆአቸዋል ። እንዲሁም፡
እንደ፡እነርሱ፡ዝሙትን፡ያደረጉና፡ሌላን፡
ሥጋ፡የተከተሉ፡ሰዶምና፡ገሞራ፡በዙሪያቸ
ውም፡የነበሩ፡ከተማዎች፡በዘላለም፡እሳት፡
እየተቀጡ፡ምሳሌ፡ሆነዋል ።
፰፤ እንዲሁም፡እነዚህ፡ሰዎች፡ደግሞ፡እያ
ለሙ፡ሥጋቸውን፡ያረክሳሉ፡ጌትነትንም፡
ይጥላሉ፡ሥልጣን፡ያላቸውንም፡ይሳደባሉ ።
፱፤ የመላእክት፡አለቃ፡ሚካኤል፡ግን፡ከዲያብ
ሎስ፡ጋር፡በተከራከረ፡ጊዜ፡ስለ፡ሙሴ፡ሥጋ፡
ሲነጋገር ―ጌታ፡ይገሥጽህ፡አለው፡እንጂ፡
የስድብን፡ፍርድ፡ሊናገረው፡አልደፈረም ።
፲፤ እነዚህ፡ግን፡የማያውቁትን፡ሁሉ፡ይሳደባሉ÷
እእምሮም፡እንደሌላቸው፡እንስሶች፡በፍጥ
ረታቸው፡በሚያውቁት፡ሁሉ፡በእርሱ፡ይጠ
ፋሉ ። ወዮላቸው÷በቃየል፡መንገድ፡ሄደዋ ፲፩፤
ልና፡ስለ፡ደመወዝም፡በበለዓም፡ስሕተት፡
ራሳቸውን፡አሳልፈው፡ሰጥተዋል፡በቆሬም፡
መቃወም፡ ጠፍተዋል ። እነዚህ፡ከእናንተ፡ ፲፪፤
ጋር፡ሲጋበዙ፡በፍቅር፡ግብዣችሁ፡እንደ፡
እድፍ፡ናቸው ፤ እንደ፡እረኞች፡ያለ፡ፍርሃት፡
ራሳቸውን፡ይጠብቃሉ ፤ በነፋስ፡የተወሰዱ፡
ውኃ፡የሌለባቸው፡ደመናዎች÷ፍሬ፡የማያ
ፈሩ፡ሁለት፡ጊዜ፡የሞቱ፡ከነሥራቸው፡የተ
ነቀሉ፡በበጋ፡የደረቁ፡ዛፎች÷የገዛ፡ነውራ ፲፫፤
ቸውን፡አረፋ፡አየደፈቁ፡ጨካኝ፡የባሕር፡
ማዕበል÷ድቅድቅ፡ጨለማ፡ለዘላለም፡የተጠ
በቀላቸው፡የሚንከራተቱ፡ከዋክብት፡ናቸው ።
ከአዳም፡ጀምሮ፡ሰባተኛ፡የሆነ፡ሄኖክ ― ፲፬፡፲፭፤
እነሆ÷ጌታ፡በሁሉ፡ላይ፡እንዲፈርድ÷በኃ
ጢአተኝነትም፡ስላደረጉት፡ስለ፡ኃጢአተኛ፡
ሥራቸው፡ሁሉ፡ዓመፀኞችም፡ኃጢአተኞች፡
በእርሱ፡ላይ፡ስለ፡ተናገሩ፡ስለ፡ጭከና፡ነገር፡
ሁሉ፡ኃጢአተኞችን፡ሁሉ፡እንዲወቅስ፡ከአእ
ላፋት፡ቅዱሳኑ፡ጋር፡መጥቶአል፡ብሎ፡ለእነ
ዚህ፡ደግሞ፡ትንቢት፡ተናገረ ። እነዚህ፡እንደ፡ ፲፮፤
ምኞታቸው፡እየሄዱ፡የሚያንጐራጕሩና፡ስለ፡
ዕድላቸው፡የሚያጕረመርሙ፡ናቸው÷እንዲ
ረባቸውም፡ለሰው፡ፊት፡እያደሉ፡አፋቸው፡
ከመጠን፡ይልቅ፡ታላቅ፡ቃል፡ይናገራል ።
እናንተ፡ግን÷ወዳጆች፡ሆይ÷በጌታችን፡ ፲፯፤
በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሐዋርያት፡ቀድሞ፡የተ
ነገረውን፡ቃል፡አስቡ ፤ እነርሱ ―በመጨረ ፲፰፤
ሻው፡ዘመን፡በኃጢአተኝነት፡እንደ፡ገዛ፡
ምኞታቸው፡ እየሄዱ፡ ዘባቾች፡ ይሆናሉ፡
ብለዋችኋልና ። እነዚህ፡የሚያለያዩ፡ሥጋው ፲፱፤
ያንም፡የሆኑ፡መንፈስም፡የሌላቸው፡ሰዎች፡
ናቸው ። እናንተ፡ግን÷ወዳጆች፡ሆይ÷ከሁሉ፡ ፳፤
ይልቅ፡በተቀደሰ፡ሃይማኖታችሁ፡ራሳችሁን፡

፭። ፲፯፤ ፩ ነገሥ. ፲፯ ÷ ፩፤ ሉቃ. ፬ ÷ ፳፭። ፲፰፤ ፩ ነገሥ. ፲፰ ÷ ፵፪፤ ፵፭። ፲፱፤ ማቴ. ፲፰ ÷ ፲፭። ፳፤ መዝ. ፴፭ ÷ ፩፤ ፩ ጴጥ. ፬ ÷ ፰።
፩፤ ማቴ. ፲፫ ÷ ፶፭። ፪፤ ፪ ጴጥ. ፩ ÷ ፪። ፬፤ ፪ ጴጥ. ፩ ÷ ፲፩፤ ገላ. ፲፬ ÷ ፵፭። ፭፤ ፪ ጴጥ. ፪ ÷ ፪። ፮፤ ዘኁ. ፲፬ ÷ ፳፱፤ ፪ ጴጥ. ፪ ÷ ፲፩። ፯፤ ፪ ጴጥ. ፪ ÷ ፲፬።
፲፩ ÷ ፴፪፤ ፪ ጴጥ. ፪ ÷ ፮። ፰፤ ፪ ጴጥ. ፪ ÷ ፲። ፱፤ ዘፍ. ፫ ÷ ፪፤ ዳን. ፲ ÷ ፲፫፤ ፪ ጴጥ. ፪ ÷ ፲፩። ፲፤ ፪ ጴጥ. ፪ ÷ ፲፪።
፲፩፤ ዘፍ. ፬ ÷ ፰፤ ፪ ጴጥ. ፪ ÷ ፲፭፤ ዘኁ. ፲፮ ÷ ፩–፫፤ ፴፩—፴፭። ፲፪፡፲፫፤ ኢሳ. ፶፯ ÷ ፳፤ ፪ ጴጥ. ፪ ÷ ፲፫፡፲፯።
፲፬፤ ዘፍ. ፭ ÷ ፲፰። ፲፮፤ ፪ ጴጥ. ፪ ÷ ፲፰፤ ዘሌዋ. ፲፱ ÷ ፲፭። ፲፯፤ ፪ ጴጥ. ፫ ÷ ፪። ፲፰፤ ፪ ጴጥ. ፫ ÷ ፫። ፲፱፤
፩ ቆሮ. ፪ ÷ ፲፬። ፳፤ ቆላ. ፪ ÷ ፯፤ ኤፌ. ፮ ÷ ፲፰።

ሰማነጽ፡እየተጋችሁ፡በመንፈስ፡ቅዱስም፡እየ
፳፩ ጸለያችሁ÷ወደ፡ዘላለም፡ሕይወት፡የሚወስደ
ውን፡የጌታችንን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ምሕ
ረት፡ስትጠባበቁ፡በእግዚአብሔር፡ፍቅር፡ራስ
፳፪ ችሁን፡ጠብቁ ። አንዳንዶች፡ተከራከሪዎች
፳፫ ንም፡ውቀሱ÷አንዳንዶችንም፡ከእሳት፡ነጥቃ
ችሁ፡አድኑ÷አንዳንዶችንም፡በሥጋ፡የረከ
ሰውን፡ልብስ፡እንኳ፡እየጠላችሁ፡በፍርሃት፡
ማሩ ።

ሳትሰናከሉም፡እንዲጠብቃችሁ÷በክብሩም፡ ፳፬
ፊት፡በደስታ፡ነውር፡የሌላችሁ፡አድርጎ፡
እንዲያቆማችሁ፡ለሚችለው፡ብቻውን፡ለሆነ፡ ፳፭
አምላክና፡መድኃኒታችን፡ከዘመን፡ሁሉ፡
በፊት፡አሁንም፡እስከ፡ዘላለምም፡ድረስ፡በጌ
ታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ክብርና፡ግርማ፡
ኃይልም፡ሥልጣንም፡ይሁን፤አሜን ።

# የዮሐንስ፡ራእይ ።

## ምዕራፍ፡፩ ።

፩ ቶሎ፡ይሆን፡ዘንድ፡የሚገባውን፡ነገር፡
ለባሪያዎቹ፡ያሳይ፡ዘንድ፡እግዚአብሔር፡ለኢ
የሱስ፡ክርስቶስ፡የሰጠው፡በእርሱም፡የተገ
ለጠው፡ይህ፡ነው÷ኢየሱስም፡በመልአኩ፡
፪ ልኮ፡ለባሪያው፡ለዮሐንስ፡አመለከተ÷እር
ሱም፡ለእግዚአብሔር፡ቃልና፡ለኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ምስክር፡ላየውም፡ሁሉ፡መሰ
፫ ከረ ። ዘመኑ፡ቀርቦአልና፡የሚያነበው÷የትን
ቢቱን፡ቃል፡የሚሰሙትና፡በውስጡ፡የተጻ
ፈውን፡የሚጠብቁት፡ብፁዓን፡ናቸው ።

፬ ዮሐንስ፡በእስያ፡ላሉት፡ለሰባቱ፡አብያተ፡
ክርስቲያናት ፤

ካለውና፡ከነበረው፡ከሚመጣውም÷በዙፋ
ኑም፡ፊት፡ካሉት፡ከሰባቱ፡መናፍስት፡÷ከታ
መነውም፡ምስክር፡ከሙታንም፡በኵር፡የምድ
ርም፡ነገሥታት፡ገዥ፡ከሆነ፡ከኢየሱስ፡ክር
ስቶስ፡ጸጋና፡ሰላም፡ለእናንተ፡ይሁን ።

ለወደደን፡ከኃጢአታችንም፡በደሙ፡
፮ ላጠበን÷መንግሥትም፡ለአምላኩና፡ለአባ
ቱም፡ካህናት፡እንድንሆን፡ላደረገ÷ለእርሱ፡
ከዘላለም፡እስከ፡ዘላለም፡ድረስ፡ክብርና፡
፯ ኃይል፡ይሁን፤አሜን ። እነሆ÷ከደመና፡
ጋር፡ይመጣል፤ዓይንም፡ሁሉ፡የወጉትም፡
ያዩታል÷የምድርም፡ወገኖች፡ሁሉ፡ስለ፡
እርሱ፡ዋይ፡ዋይ፡ይላሉ ። አዎን÷አሜን ።

፰ ያለውና፡የነበረው፡የሚመጣውም፡ሁሉ
ንም፡የሚገዛ፡ጌታ፡አምላክ፡— አልፋና፡
ዖሜጋ፡እኔ፡ነኝ፡ይላል ።

፱ እኔ፡ወንድማችሁ፡የሆንሁ፡ከእናንተም፡
ጋር፡አብሬ፡መከራውንና፡መንግሥቱን፡የኢ
የሱስ፡ክርስቶስንም፡ትዕግሥት፡የምካፈል፡
ዮሐንስ፡ስለ፡እግዚአብሔር፡ቃልና፡ስለ፡
ኢየሱስ፡ምስክር፡ፍጥሞ፡በምትባል፡ደሴት፡
፲ ነበርሁ ። በጌታ፡ቀን፡በመንፈስ፡ነበርሁ÷
በኋላዬም፡የመለከትን፡ድምፅ፡የሚመስል፡
ታላቅ፡ድምፅ፡ሰማሁ÷እንዲሁም፡— የምታየ ፲፩
ውን፡በመጽሐፍ፡ጽፈህ፡ወደ፡ኤፌሶንና፡
ወደ፡ሰምርኔስ፡ወደ፡ጴርጋሞንም፡ወደ፡ትያ
ጥሮንም፡ወደ፡ሰርዴስም፡ወደ፡ፊልድልፍ
ያም፡ወደ፡ሎዶቅያም፡በእስያ፡ወዳሉት፡ወደ፡
ሰባቱ፡አብያተ፡ክርስቲያናት፡ላክ፡አለኝ ።

የሚናገረኝንም፡ድምፅ፡ለማየት፡ዘወር፡ ፲፪
አልሁ፤ዘወርም፡ብዬ፡ሰባት፡የወርቅ፡መቅ
ረዞች፡አየሁ÷በመቅረዞቹም፡መካከል፡የሰው፡ ፲፫
ልጅ፡የሚመስለውን፡አየሁ÷እርሱም፡እስከ፡
እግሩ፡ድረስ፡ልብስ፡የለበሰው፡ደረቱንም፡
በወርቅ፡መታጠቂያ፡የታጠቀ፡ነበር ። ራሱና፡ ፲፬
የራሱ፡ጠጕርም፡እንደ፡ነጭ፡የበግ፡ጠጕር፡
እንደ፡በረዶም፡ነጭ፡ነበሩ÷ዓይኖቹም፡እንደ፡
እሳት፡ነበልባል፡ነበሩ፤እግሮቹም፡በእቶን፡ ፲፭
የነጠረ፡የጋስ፡ናስ፡ይመስሉ፡ነበር÷ድምፁም፡
እንደ፡ብዙ፡ውኆዎች፡ድምፅ፡ነበረ ። በቀኝ፡ ፲፮
እጁም፡ሰባት፡ከዋክብት፡ነበሩት÷ከአፉም፡
በሁለት፡ወገን፡የተሳለ፡ስለታም፡ሰይፍ፡ወጣ፤
ፊቱም፡በኃይል፡እንደሚበራ፡እንደ፡ፀሐይ፡
ነበረ ።

ባየሁትም፡ጊዜ፡እንደ፡ሞተ፡ሰው፡ሆኜ፡ ፲፯
ከእግሩ፡በታች፡ወደቅሁ ። ቀኝ፡እጁንም፡
ጫነብኝ፡እንዲህም፡አለኝ፡— አትፍራ፤ፊተ
ኛውና፡መጨረሻው፡ሕያውም፡እኔ፡ነኝ÷ ፲፰
ሞቼም፡ነበርሁ፡እነሆም÷ከዘላለም፡እስከ፡
ዘላለም፡ድረስ፡ሕያው፡ነኝ÷የሞትና፡የሲኦ
ልም፡መክፈቻ፡አለኝ ። እንግዲህ፡ያየኸውን፡ ፲፱
አሁንም፡ያለውን፡ከዚህም፡በኋላ፡ይሆን፡
ዘንድ፡ያለውን፡ጻፍ ። በቀኝ፡እጄ፡ያየሃቸው፡ ፳
የሰባት፡ከዋክብትና፡የሰባቱ፡የወርቅ፡መቅ
ረዞች፡ምሥጢር፡ይህ፡ነው፤ሰባቱ፡ከዋክ
ብት፡የሰባቱ፡አብያተ፡ክርስቲያናት፡መላእ
ክት፡ናቸው÷ሰባቱም፡መቅረዞች፡ሰባቱ፡አብ
ያተ፡ክርስቲያናት፡ናቸው ።

፳፫፤ ዓሞ. ፬ ÷ ፲፩ ፤ ዘካ. ፫ ÷ ፪ ፣ ፬ ፤ ራእ. ፫ ÷ ፬ ። ፳፬፤ ፩ ተሰ. ፭ ÷ ፳፫ ፤ ፩ ጴጥ. ፬ ÷ ፲፫ ። ፳፭፤ ሮሜ ፲፮ ÷ ፳፯ ።

፩። ፩፤ ዮሐ. ፲፯ ÷ ፯ ፣ ፰ ። ፪፤ ዘፀአ. ፫ ÷ ፲፬ ፤ ኢሳ. ፵፩ ÷ ፬ ፣ ፫ ። ፫፤ ዮሐ. ፲፭ ÷ ፱ ፤ ፲፭ ÷ ፳፮ ፤ ቈላ. ፩ ÷ ፲፰ ፤ [illegible] [illegible] ፩ ጴጥ. ፩ ÷ ፲፱ ። ፮፤ ዘፀአ. ፲፱ ÷ ፮ ፤ ፩ ጴጥ. ፪ ÷ ፱ ፤ ሮሜ ፲፭ ÷ [illegible] ። ፯፤ ማቴ. [illegible] ፤ ዘካ. ፲፪ ÷ ፲ ፤ ዮሐ. ፲፱ ÷ [illegible] ። ፰፤ ዮሐ. ፱ ። ፲፤ ፪ ቆሮ. ፲፪ ÷ ፪ ፤ ዘፀአ. ፲፱ ÷ ፲፮ ። ፲፩፤ የሐዋ. ፲፱ ÷ ፩ ፣ ፰ ፣ ፲ ። ፲፪፤ ዘፀአ. [illegible] ። ፲፫፤ ዳን. ፯ ÷ ፲፫ ። ፲፬፤ ዳን. ፯ ÷ ፱ ። ፲፭፤ ሕዝ. ፩ ÷ [illegible] ። ፲፮፤ ኢሳ. [illegible] ፤ ማቴ. ፲፯ ÷ ፪ ። ፲፯፤ ዳን. ፰ ÷ ፲፯ ፤ ፲፰ ፤ ኢሳ. ፵፬ ÷ ፮ ። ፲፰፤ ሮሜ ፮ ÷ ፱ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩፤ በኤፌሶን ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፤— በቀኝ ፡
እጁ ፡ ሰባቱን ፡ ከዋክብት ፡ የያዘው ፡ በሰባቱም ፡
የወርቅ ፡ መቅረዞች ፡ መካከል ፡ የሚሄደው ፡ እን
ዲህ ፡ ይላል ፤—
፪፤ ሥራህንና ፡ድካምህን ፡ ትዕግሥትህንም ፡ አው
ቃለሁ ፤ ክፉዎችንም ፡ ልትታገሥ ፡ እንዳትችል ÷
እንዲሁም ፡ ሳይሆኑ ፤— ሐዋርያት ፡ ነን ፡ የሚ
ሉቱን ፡ መርምረህ ፡ ሐሰተኞች ፡ ሆነው ፡ እንዳ
፫፤ ገኘሃቸው ፡ አውቃለሁ ፤ ታግሥህማል ÷ ስለ ፡
፬፤ ስሜም ፡ ብለህ ፡ ጸንተህ ፡ አልደከምህም ። ዳሩ ፡
ግን ፡ የምነቅፍብህ ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ የቀደመውን ፡
፭፤ ፍቅርህን ፡ ትተሃልና ። እንግዲህ ፡ ከወዴት ፡
እንደ ፡ ወደቅህ ፡ አስብ ፡ ንስሐም ፡ ግባ ፡ የቀደ
መውንም ፡ ሥራህን ፡ አድርግ ፤ አለዚያ ፡ እመ
ጣብሃለሁ ፡ ንስሐም ፡ ባትገባ ፡ መቅረዝህን ፡ ከስ
፮፤ ፍራው ፡ እወስዳለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አለህ ፤
እኔ ፡ ደግሞ ፡ የምጠላውን ፡ የኒቆላውያንን ፡
፯፤ ሥራ ፡ ጠልተሃልና ። መንፈስ ፡ ለአብያተ ፡ ክር
ስቲያናት ፡ የሚለውን ፡ ጆሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።
ድል ፡ ለነሣው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ገነት ፡ ካለው ፡
ከሕይወት ፡ ዛፍ ፡ እንዲበላ ፡ እሰጠዋለሁ ።
፰፤ በሰምርኔስም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፤— ሞቶ ፡
የነበረው ፡ ሕያውም ፡ የሆነው ፡ ፊተኛውና ፡
መጨረሻው ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤—
፱፤ መከራህንና ፡ ድህነትህን ፡ አውቃለሁ ÷ ነገር ፡
ግን ፡ ባለ ፡ ጠጋ ፡ ነህ ፤ የሰይጣንም ፡ ማኅበር ፡
ናቸው ፡ እንጂ ፡ አይሁድ ፡ ሳይሆኑ ፤— አይሁድ ፡
ነን ፡ የሚሉት ፡ የሚሳደቡትን ፡ ስድብ ፡ አው
፲፤ ቃለሁ ። ልትቀበለው ፡ ያለህን ፡ መከራ ፡ አት
ፍራ ። እነሆ ÷ እንድትፈተኑ ፡ ዲያብሎስ ፡ ከእ
ናንተ ፡ አንዳንዶቻችሁን ፡ በወኅኒ ፡ ሊያገባችሁ ፡
አለው ÷ አሥር ፡ ቀንም ፡ መከራን ፡ ትቀበላላ
ችሁ ። እስከ ፡ሞት ፡ ድረስ ፡ የታመንህ ፡ ሁን ፡
፲፩፤ የሕይወትንም ፡ አክሊል ፡ እሰጥሃለሁ ። መን
ፈስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚለውን ፡ ጆሮ ፡
ያለው ፡ ይስማ ። ድል ፡ የነሣው ፡ በሁለተኛው ፡
ሞት ፡ አይጐዳም ።
፲፪፤ በጴርጋሞንም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፤— በሁ
ለት ፡ ወገን ፡ የተሳለ ፡ ስለታም ፡ ሰይፍ ፡ ያለው ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፤—
፲፫፤ የሰይጣን ፡ ዙፋን ፡ ባለበት ፡ የምትኖርበትን ፡
አውቃለሁ ፤ ስሜንም ፡ ትጠብቃለህ ÷ ሰይጣ
ንም ፡ ለሚኖርበት ÷ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የተገደ
ለው ፡ የታመነው ፡ ምስክሬ ፡ አንቲጳስ ፡ በነበረ
በት ፡ ዘመን ፡ እንኳ ፡ ሃይማኖቴን ፡ አልካድህም ።
ዳሩ ፡ ግን ፡ ለጣዖት ፡ የታረደውን ፡ እንዲበሉና ፡ ፲፬፤
እንዲሴስኑ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ማሰ
ናከያን ፡ ሊያኖርባቸው ፡ ባላቅን ፡ ያስተማረ ፡ የበ
ለዓምን ፡ ትምህርት ፡ የሚጠብቁ ፡ በዚያ ፡ ከአ
ንተ ፡ ጋር ፡ ስላሉ ÷ የምነቅፍብህ ፡ ጥቂት ፡ ነገር ፡
አለኝ ። እንዲሁ ፡ የኒቆላውያንን ፡ ትምህርት ፡ ፲፭፤
እንደ ፡ እነዚህ ፡ የሚጠብቁ ፡ ሰዎች ፡ ከአንተ ፡
ጋር ፡ ደግሞ ፡ አሉ ። እንግዲህ ፡ ንስሐ ፡ ግባ ፤ አለ ፲፮፤
ዚያ ፡ ፈጥኜ ፡ እመጣብሃለሁ ÷ በአፌም ፡ ሰይፍ ፡
እዋጋቸዋለሁ ። መንፈስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስ ፲፯፤
ቲያናት ፡ የሚለውን ፡ ጆሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።
ድል ፡ ለነሣው ፡ ከተሰወረ ፡ መና ፡ እሰጠዋለሁ ÷
ነጭ ፡ ድንጋይንም ፡ እሰጠዋለሁ ÷ በድንጋዩም ፡
ላይ ፡ ከተቀበለው ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የሚ
ያውቀው ፡ የሌለ ፡ አዲስ ፡ ስም ፡ ተጽፎአል ።
በትያጥሮንም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ፲፰፤
ቲያን ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፤— እንደ ፡
እሳት ፡ ነበልባል ፡ የሆኑ ፡ ዓይኖች ፡ ያሉት ፡ ለእ
ግሮቹም ፡ የነጠረ ፡ የጋለ ፡ ናስ ፡ የሚመስሉ ፡ እግ
ሮች ፡ ያሉት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፤—
ሥራህንና ፡ ፍቅርህን ፡ እምነትህንም ፡ አገል ፲፱፤
ግሎትህንም ፡ ትዕግሥትህንም ፡ ከፊተኛውም ፡
ሥራህ ፡ ይልቅ ፡ የኋለኛው ፡ እንዲበዛ ፡ አውቃ
ለሁ ። ዳሩ ፡ ግን ፤— ነቢይ ፡ ነኝ ፡ የምትለውን ፡ ፳፤
ባሪያዎቼንም ፡ እንዲሴስኑና ፡ ለጣዖት ፡ የታረደ
ውን ፡ እንዲበሉ ፡ የምታስተምረውንና ፡ የምታ
ስተውን ፡ ያችን ፡ ሴት ፡ ኤልዛቤልን ፡ ስለምት
ተዋት ፡ የምነቅፍብህ ፡ ነገር ፡ አለኝ ፤ ንስሐም ፡ ፳፩፤
እንድትገባ ፡ ጊዜ ፡ ሰጠኋት ፡ ከዝሙትዋም ፡
ንስሐ ፡ እንድትገባ ፡ አልወደደችም ። እነሆ ÷ ፳፪፤
ለአልጋ ፡ ላይ ፡ እጥላታለሁ ÷ ከእርስዋም ፡ ጋር ፡
የሚያመነዝሩትን ፡ ከሥራዋ ፡ ንስሐ ፡ ባይገቡ ፡
በታላቅ ፡ መከራ ፡ እጥላቸዋለሁ ፤ ልጆችዋንም ፡ ፳፫፤
በሞት ፡ እገድላቸዋለሁ ፤ አብያተ ፡ ክርስቲያና
ትም ፡ ሁሉ ፡ ኵላሊትንና ፡ ልብን ፡ የምመረምር ፡
እኔ ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ያውቃሉ ÷ ለእያንዳንዳች
ሁም ፡ እንደ ፡ ሥራችሁ ፡ እሰጣችኋለሁ ። ዳሩ ፡ ፳፬፤
ግን ፡ ይህን ፡ ትምህርት ፡ ለማትይዙ ፡ ሁሉ ፡ የሰ
ይጣንንም ፡ ጥልቅ ፡ ነገር ፡ እነርሱ ፡ እንደሚሉት ፡
ለማታውቁ ፡ ለእናንተ ፡ በትያጥሮን ፡ ለቀራች
ሁት ፡ እላለሁ ፤ ሌላ ፡ ሸክም ፡ አልጭንባች
ሁም ÷ ነገር ፡ ግን ፡ እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ ያላች ፳፭፤
ሁን ፡ ጠብቁ ። ድል ፡ ለነሣውና ፡ እስከ ፡ መጨ ፳፮፳፯፤
ረሻም ፡ ሥራዬን ፡ ለጠበቀው ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡
ከአባቴ ፡ እንደ ፡ ተቀበልሁ ፡ በአሕዛብ ፡ ላይ ፡
ሥልጣንን ፡ እሰጠዋለሁ ÷ በብረትም ፡ በትር ፡
ይገዛቸዋል ÷ እንደ ፡ ሸክላ ፡ ዕቃም ፡ ይቀጠ
ቀጣሉ ፤ የንጋትንም ፡ ኮከብ ፡ እሰጠዋለሁ ። ፳፰፤

፳፱ መንፈስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚለውን ፡
ጆሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ በሰርዴስም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፤— ሰባቱ ፡
የእግዚአብሔር ፡ መናፍስትና ፡ ሰባቱ ፡ ከዋክ
ብት ፡ ያሉት ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤—
ሥራህን ፡ አውቃለሁ ፤ ሕያው ፡ እንደ ፡ መሆ
፪ ንህ ፡ ስም ፡ አለህ ፡ ሞተሃማል ። ሥራህን ፡ በአም
ላኬ ፡ ፊት ፡ ፍጹም ፡ ሆኖ ፡ አላገኘሁትምና ፡ የነ
ቃህ ፡ ሁን ፥ ሊሞቱም ፡ ያላቸውን ፡ የቀሩትን ፡
፫ ነገሮች ፡ አጽና ። እንግዲህ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡
ተቀበልህና ፡ እንደ ፡ ሰማህ ፡ አስብ ፥ ጠብቀውም ፡
ንስሐም ፡ ግባ ። እንግዲያስ ፡ ባትነቃ ፡ እንደ ፡
ሌባ ፡ እመጣብሃለሁ ፡ በማናቸውም ፡ ሰዓት ፡ እን
፬ ድመጣብህ ፡ ከቶ ፡ አታውቅም ። ነገር ፡ ግን ፡
ልብሳቸውን ፡ ያላረከሱ ፡ በሰርዴስ ፡ ጥቂት ፡
ሰዎች ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ አሉ ፥ የተገባቸውም ፡
ስለ ፡ ሆኑ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡
፭ ይሄዳሉ ። ድል ፡ የነሣው ፡ እንዲሁ ፡ በነጭ ፡
ልብስ ፡ ይጐናጸፋል ፥ ስሙንም ፡ ከሕይወት ፡
መጽሐፍ ፡ አልደመስስም ፥ በአባቴና ፡ በመላእ
፮ ክቱም ፡ ፊት ፡ ለስሙ ፡ እመሰክርለታለሁ ። መን
ፈስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚለውን ፡
ጆሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።
፯ በፊልድልፍያም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፤— የዳ
ዊት ፡ መክፈቻ ፡ ያለው ፤ የሚከፍት ፥ የሚዘጋም ፡
የሌለ ፤ የሚዘጋ ፥ የሚከፍትም ፡ የሌለ ፤ ቅዱስና ፡
እውነተኛ ፡ የሆነው ፡ እርሱ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤—
፰ ሥራህን ፡ አውቃለሁ ፤ እነሆ ፥ በአንተ ፡ ፊት ፡
የተከፈተ ፡ በር ፡ ሰጥቼአለሁ ፡ ማንም ፡ ሊዘ
ጋው ፡ አይችልም ፤ ኃይልህ ፡ ምንም ፡ ትንሽ ፡
ቢሆን ፡ ቃሌን ፡ ጠብቀሃልና ፥ ስሜንም ፡ አልካድህ
፱ ምና ። እነሆ ፥ አይሁድ ፡ ሳይሆኑ ፤— አይሁድ ፡
ነን ፡ ከሚሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከሚዋሹ ፡ ከሰይጣን ፡
ማኅበር ፡ እንዳንዶችን ፡ እሰጥሃለሁ ፤ እነሆ ፥
መጥተው ፡ በእግሮችህ ፡ ፊት ፡ ይሰግዱ ፡ ዘንድ ፡
እኔም ፡ እንደ ፡ ወደድሁህ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ አደ
፲ ርጋቸዋለሁ ። የትዕግሥቴን ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ ጠበ
ቅህ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በምድር ፡ የሚኖሩትን ፡ ይፈ
ትናቸው ፡ ዘንድ ፡ በዓለም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሊመጣ ፡
ካለው ፡ ከፈተናው ፡ ሰዓት ፡ እጠብቅሃለሁ ።
፲፩ እነሆ ፥ ቶሎ ፡ ብዬ ፡ እመጣለሁ ፤ ማንም ፡ አክሊ
ልህን ፡ እንዳይወስድብህ ፡ ያለህን ፡ አጽንተህ ፡
፲፪ ያዝ ። ድል ፡ የነሣው ፡ በአምላኬ ፡ መቅደስ ፡
ዓምድ ፡ እንዲሆን ፡ አደርገዋለሁ ፥ ወደ ፡ ፊትም ፡
ከዚያ ፡ ከቶ ፡ አይወጣም ፤ የአምላኬን ፡ ስምና ፡
የአምላኬን ፡ ከተማ ፡ ስም ፥ ማለት ፡ ከሰማይ ፡
ከአምላኬ ፡ ዘንድ ፡ የምትወርደውን ፡ አዲሲቱን ፡
ኢየሩሳሌምን ፥ አዲሱንም ፡ ስሜን ፡ በእርሱ ፡
ላይ ፡ እጽፋለሁ ። መንፈስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስ ፲፫
ቲያናት ፡ የሚለውን ፡ ጆሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።
በሎዶቅያም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ፲፬
ያን ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፤— አሜን ፡
የሆነው ፤ የታመነውና ፡ እውነተኛው ፡ ምስክር ፥
በእግዚአብሔርም ፡ ፍጥረት ፡ መጀመሪያ ፡ የነ
በረው ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤—
በራድ ፡ ወይም ፡ ትኩስ ፡ እንዳይደለህ ፡ ሥራ ፲፭
ህን ፡ አውቃለሁ ። በራድ ፡ ወይም ፡ ትኩስ ፡ ብት
ሆንስ ፡ መልካም ፡ በሆነ ፡ ነበር ። እንዲሁ ፡ ለብ ፡ ፲፮
ስላልህ ፡ በራድም ፡ ወይም ፡ ትኩስ ፡ ስላልሆንህ ፡
ከአፌ ፡ ልተፋህ ፡ ነው ። ሀብታም ፡ ነኝና ፡ ባለ ፡ ፲፯
ጠጋ ፡ ሆኜአለሁ ፡ አንድም ፡ ስንኳ ፡ አያስፈልገ
ኝም ፡ የምትል ፡ ስለ ፡ ሆንህ ፥ ጐስቋላና ፡ ምስ
ኪንም ፡ ድሀም ፡ ዕውርም ፡ የተራቆትህም ፡ መሆ
ንህን ፡ ስለማታውቅ ፥ ባለ ፡ ጠጋ ፡ እንድትሆን ፡ ፲፰
በእሳት ፡ የነጠረውን ፡ ወርቅ ፥ ተጐናጽፈህም ፡
የራቁትነትህ ፡ ኃፍረት ፡ እንዳይገለጥ ፡ ነጭ ፡
ልብስን ፥ እንድታይም ፡ ዓይኖችህን ፡ የምትኳ
ለውን ፡ ኵል ፡ ከእኔ ፡ ትገዛ ፡ ዘንድ ፡ እመክርሃ
ለሁ ። እኔ ፡ የምወዳቸውን ፡ ሁሉ ፡ እገሥጻቸ ፲፱
ዋለሁ ፡ እቀጣቸውማለሁ ፤ እንግዲህ ፡ ቅና ፡
ንስሐም ፡ ግባ ። እነሆ ፡ በደጅ ፡ ቆሜ ፡ እንኳኳ ፳
ለሁ ፤ ማንም ፡ ድምፄን ፡ ቢሰማ ፡ ደጁንም ፡
ቢከፍትልኝ ፥ ወደ ፡ እርሱ ፡ እገባለሁ ፡ ከእር
ሱም ፡ ጋር ፡ እራት ፡ እበላለሁ ፡ እርሱም ፡ ከእኔ ፡
ጋር ፡ ይበላል ። እኔ ፡ ደግሞ ፡ ድል ፡ እንደ ፡ ፳፩
ነሣሁ ፡ ከአባቴም ፡ ጋር ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡
ተቀመጥሁ ፥ ድል ፡ ለነሣው ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ በዙ
ፋኔ ፡ ላይ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ እሰጠዋለሁ ። መን ፳፪
ፈስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚለውን ፡
ጆሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

ከዚያ ፡ በኋላም ፡ አየሁ ፥ እነሆም ፡ በሰማይ ፡ ፩
የተከፈተ ፡ ደጅ ፥ እንደ ፡ መለከትም ፡ ሆኖ ፡ ሲና
ገረኝ ፡ የሰማሁት ፡ ፊተኛው ፡ ድምፅ ፤— ወደዚህ ፡
ውጣና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሊሆን ፡ የሚያስፈልገ
ውን ፡ ነገር ፡ አሳይሃለሁ ፡ አለ ። ወዲያው ፡ በመ ፪
ንፈስ ፡ ነበርሁ ፤ እነሆም ፥ ዙፋን ፡ በሰማይ ፡
ቆሞአል ፡ በዙፋኑም ፡ ላይ ፡ ተቀማጭ ፡ ነበረ ፤
ተቀምጦም ፡ የነበረው ፡ በመልኩ ፡ የኢያስጲ ፫
ድንና ፡ የሰርዲኖን ፡ ዕንቍ ፡ ይመስል ፡ ነበር ።
በመልኩም ፡ መረግድን ፡ የመሰለ ፡ ቀስተ ፡
ደመና ፡ በዙፋኑ ፡ ዙሪያ ፡ ነበረ ። በዙፋኑ ፡ ዙሪ ፬
ያም ፡ ሀያ ፡ አራት ፡ ዙፋኖች ፡ ነበሩ ፥ በዙፋኖ

፫። ፩፤ ም. ፩፥፬፤ ፲፮፤ ፩ ጢሞ. ፭፥፮ ። ፫፤ ማቴ. ፳፬፥፵፪፤ ፵፫፤ ፩ ተሰ. ፭፥፪ ። ፬፤ ይሁዳ ፳፫ ። ፭፤ ዘፀአ. ፴፪፥፴፪፤ ማቴ. ፲፥፴፪፤ ሉቃ. ፲፪፥፰ ። ፯፤ ፩ ዮሐ. ፭፥፳፤ ኢሳ. ፳፪፥፳፪ ። ፱፤ ም. ፪፥፱፤ ኢሳ. ፷፥፲፬፤ ፵፫፥፬ ። ፲፩፤ ም. ፪፥፲፮፤ ኢሳ. ፶፪፥፪፤ ሕዝ. ፵፰፥፴፭ ። ፲፬፤ ም. ፩፥፭፤ ፪ ቆሮ. ፩፥፳፤ ዮሐ. ፩፥፫ ። ፲፯፤ ሆሴ. ፲፪፥፰ ። ፲፰፤ ቀሎ. ፪ ። ፲፱፤ ምሳ. ፫፥፲፪ ። ፳፤ ሉቃ. ፲፪፥፴፯፤ ዮሐ. ፲፬፥፳፫ ። ፳፩፤ ማቴ. ፲፱፥፳፰ ።

፬። ፩፤ ም. ፩፥፲፤ ፲፱ ። ፪፤ ፫፤ መዝ. ፲፥፬፤ ሕዝ. ፩፥፳፮፤ ፳፰ ። ፬፤ ኢሳ. ፳፬፥፳፫ ።

ቹም ፡ ላይ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ በራሳቸ
ውም ፡ የወርቅ ፡ አክሊል ፡ ደፍተው ፡ ሀያ ፡ አራት ፡
፭፤ ሽማግሌዎች ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ። ከዙፋኑም ፡
መብረቅና ፡ ድምፅ ፡ ነጐድጓድም ፡ ይወጣል ፤
በዙፋኑም ፡ ፊት ፡ ሰባት ፡ የእሳት ፡ መብራቶች ፡
ይበሩ ፡ ነበር ÷ እነርሱም ፡ ሰባቱ ፡ የእግዚአብ
፮፤ ሔር ፡ መናፍስት ፡ ናቸው ። በዙፋኑም ፡ ፊት ፡
ብርሌ ፡ የሚመስል ፡ የብርጭቆ ፡ ባሕር ፡ ነበረ ።
በዙፋኑም ፡ መካከል ፡ በዙፋኑም ፡ ዙሪያ ÷
በፊትና ፡ በኋላ ፡ ዓይኖች ፡ የሞሉአቸው ፡ አራት ፡
፯፤ እንስሶች ፡ ነበሩ ። ፊተኛውም ፡ እንስሳ ፡ አን
በሳን ፡ ይመስላል ÷ ሁለተኛውም ፡ እንስሳ ፡
ጥጃን ፡ ይመስላል ÷ ሦስተኛውም ፡ እንስሳ ፡ እንደ ፡
ሰው ፡ ፊት ፡ ነበረው ÷ አራተኛውም ፡ እንስሳ ፡
፰፤ የሚበረውን ፡ ንስር ፡ ይመስላል ። አራቱም ፡
እንስሶች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በድስት ፡ ክንፎች ፡
አሉአቸው ÷ በዙሪያቸውና ፡ በውስጣቸውም ፡
ዓይኖች ፡ ሞልተውባቸዋል ፤

ቅዱስ ÷ ቅዱስ ÷ ቅዱስ ÷ የነበረውና ፡
ያለው ፡ የሚመጣውም ፡ ሁሉንም ፡ የሚገዛ ፡
ጌታ ፡ አምላክ ፡

፱፤ እያሉ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ አያርፉም ። እንስሶ
ቹም ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ለተቀመጠው ፡ ከዘላለ
ምም ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ በሕይወት ፡ ለሚኖረው ፡
ለእርሱ ፡ ክብርና ፡ ውዳሴ ፡ ምስጋናም ፡ በሰጡት ፡
፲፤ ጊዜ ÷ ሀያ ፡ አራቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡
በተቀመጠው ፡ ፊት ፡ ወድቀው ÷ ከዘላለም ፡
እስከ ፡ ዘላለም ፡ በሕይወት ፡ ለሚኖረው ፡ እየ
ሰገዱ ፡—

ጌታችንና ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ÷ አንተ ፡
ሁሉን ፡ ፈጥረሃልና ፡ ስለ ፡ ፈቃድህም ፡ ሆነ
ዋልና ፡ ተፈጥረውማልና ፡ ክብር ፡ ውዳሴ ፡
ኃይልም ፡ ልትቀበል ፡ ይገባሃል ፡

እያሉ ፡ በዙፋኑ ፡ ፊት ፡ አክሊላቸውን ፡ ያኖ
ራሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩፤ በዙፋኑ ፡ ላይም ፡ በተቀመጠው ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡
ላይ ፡ በውስጥና ፡ በኋላ ፡ የተጻፈበት ፡ በሰባትም ፡
፪፤ ማኅተም ፡ የተዘጋ ፡ መጽሐፍን ፡ አየሁ ። ብር
ቱም ፡ መልአክ ፡— መጽሐፉን ፡ ይዘረጋ ፡ ዘንድ ፡
ማኅተሞቹንም ፡ ይፈታ ፡ ዘንድ ፡ የሚገባው ፡
ማን ፡ ነው ? ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ሲያውጅ ፡
፫፤ አየሁ ። በሰማይም ፡ ቢሆን ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡
ቢሆን ፡ ከምድርም ፡ በታች ፡ ቢሆን ፡ መጽሐፉን ፡
ሊዘረጋ ፡ ወይም ፡ ሊመለከተው ፡ ማንም ፡ አል
፬፤ ተቻለውም ። መጽሐፉንም ፡ ሊዘረጋ ፡ ወይም ፡
ሊመለከተው ፡ የሚገባው ፡ ማንም ፡ በላልተ
ገኘ ፡ አጅግ ፡ አለቀስሁ ። ከሽማግሌዎቹም ፡ ፭፤
አንዱ ፡— አታልቅስ ፤ እነሆ ÷ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡
የሆነው ፡ አንበሳ ፡ እርሱም ፡ የዳዊት ፡ ሥር ፡
መጽሐፉን ፡ ይዘረጋ ፡ ዘንድ ፡ ሰባቱንም ፡ ማኅ
ተም ፡ ይፈታ ፡ ዘንድ ፡ ድል ፡ ነሥቶአል ፡ አለኝ ።
በዙፋኑና ፡ በአራቱ ፡ እንስሶች ፡ መካከልም ፡ ፮፤
በሽማግሌዎችም ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ታረደ ፡ በግ ፡
ቆሞ ፡ አየሁ ÷ ሰባትም ፡ ቀንዶችና ፡ ሰባት ፡ ዓይ
ኖች ፡ ነበሩት ፡ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡
የተላኩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መናፍስት ፡ ናቸው ።
መጥቶም ፡ በዙፋን ፡ ላይ ፡ ከተቀመጠ ፡ ከዚያ ፡ ፯፤
ከቀኝ ፡ እጁ ፡ መጽሐፉን ፡ ወሰደው ። መጽሐ ፰፤
ፉንም ፡ በወሰደ ፡ ጊዜ ፡ አራቱ ፡ እንስሶችና ፡ ሀያ ፡
አራቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ በበጉ ፡ ፊት ፡ ወደቁ ÷
እያንዳንዳቸውም ፡ በገናንና ፡ የቅዱሳን ፡ ጸሎት ፡
የሆነ ፡ ዕጣን ፡ የሞላበትን ፡ የወርቅ ፡ ዕታ ፡ ያዙ ።

መጽሐፉን ፡ ትወስድ ፡ ዘንድ ፡ ማኅተሞቹ ፱፤
ንም ፡ ትፈታ ፡ ዘንድ ፡ ይገባሃል ÷ ታርደሃ
ልና ÷ በደምህም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከነ
ገድ ፡ ሁሉ ፡ ከቋንቋም ፡ ሁሉ ፡ ከወገንም ፡
ሁሉ ፡ ከሕዝብም ፡ ሁሉ ፡ ሰዎችን ፡ ዋጅ
ተህ ፡ ለአምላካችን ፡ መንግሥትና ፡ ከህናት ፡
ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ አደረግሃቸው ÷ በምድርም ፡
ላይ ፡ ይነግሣሉ ፡

እያሉ ፡ አዲስን ፡ ቅኔ ፡ ይዘምራሉ ። አየሁም ÷ ፲፩፤
በዙፋኑም ፡ በእንስሶቹም ፡ በሽማግሌዎቹም ፡
ዙሪያ ፡ የብዙ ፡ መላእክትን ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ ፤
ቍጥራቸውም ፡ እእላፋት ፡ ጊዜ ፡ እእላፋትና ፡
ሺህ ፡ ጊዜ ፡ ሺህ ፡ ነበረ ÷ በታላቅም ፡ ድምፅ ፡— ፲፪፤

የታረደው ፡ በግ ፡ ኃይልና ፡ ባለ ፡ ጠግነት ፡
ጥበብም ፡ ብርታትም ፡ ክብርም ፡ ምስጋ
ናም ፡ በረከትም ፡ ሊቀበል ፡ ይገባዋል ፡

አሉ ። በሰማይና ፡ በምድርም ፡ ከምድርም ፡ ፲፫፤
በታች ፡ በባሕርም ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡
በእነርሱም ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሁሉ ፡—

በረከትና ፡ ክብር ፡ ምስጋናም ፡ ኃይልም ፡
ከዘላለም ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡
ለተቀመጠው ÷ ለበጉም ፡ ይሁን ፡

ሲሉ ፡ሰማሁ ። አራቱም ፡ እንስሶች ፡— አሜን ፡ ፲፬፤
አሉ ÷ ሽማግሌዎቹም ፡ ወድቀው ፡ ሰገዱ ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

በጉም ፡ ከሰባቱ ፡ ማኅተም ፡ አንዱን ፡ በፈታ ፡ ፩፤
ጊዜ ፡ አየሁ ÷ ከአራቱም ፡ እንስሶች ፡ አንዱ ፡ ነጐ
ድጓድ ፡ በሚመስል ፡ ድምፅ ፡— መጥተህ ፡ እይ ፡
ሲል ፡ ሰማሁ ። አየሁም ÷ እነሆም ÷ አምባላይ ፡ ፪፤
ፈረስ ፡ ወጣ ÷ በእርሱም ፡ ላይ ፡ የተቀመጠው ፡
ቀስት ፡ ነበረው ÷ አክሊልም ፡ ተሰጠው ÷ ድልም ፡

፬። ፭፤ ም. ፩ ÷ ፲፱ ፤ ዘፀአ. ፲፱ ÷ ፲፯ ፤ ዘካ. ፬ ÷ ፪ ። ፮፤ ሕዝ. ፩ ÷ ፭ ፤ ፲ ÷ ፲፬ ። ፯፤ ሕዝ. ፩ ÷ ፲ ። ፰፤ ኢሳ. ፮ ÷ ፪ ፤ ፫ ።
፱፤ ዳን. ፬ ÷ ፴፬ ። ፲፩፤ ም. ፩ ÷ ፱ ፤ ፲ ፤ ፲፱ ፤ ፲፫ ፤ ፯ ÷ ፲ ፤ ፲፱ ፤ ፲፱ ÷ ፳፯ ፤ ፲፮ ÷ ፫ ፤ ፱ ፤ ዘፍጥ. ፩ ።
፭። ፩፤ ሕዝ. ፪ ÷ ፱ ፤ ኢሳ. ፳፱ ÷ ፲፩ ። ፭፤ ዘፍጥ. ፵፱ ÷ ፱ ፤ ኢሳ. ፲፩ ÷ ፲ ። ፮፤ ኢሳ. ፶፫ ÷ ፯ ፤ ዮሐ. ፩ ÷ ፳፱ ፤ ፩ ጴጥ. ፩ ÷ ፲፱ ፤
ዘካ. ፬ ÷ ፲ ። ፯፤ መዝ. ፻፵ ÷ ፪ ። ፱፤ ም. ፬ ÷ ፲፩ ፤ መዝ. ፵፱ ÷ ፫ ። ፲፤ ም. ፩ ÷ ፮ ። ፲፩፤ ዳን. ፯ ÷ ፲ ። ፲፪፤
ም. ፬ ÷ ፲፱ ። ፲፫፤ መዝ. ፻፵፰ ÷ ፮ ።
፮። ፪፤ ዘካ. ፮ ÷ ፫ ።

አየነሣ ፡ ወጣ ፡ ድል ፡ ለመንሣት ።
፫ ሁለተኛውንም ፡ ማኅተም ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፡
ሁለተኛው ፡ እንስሳ ፡— መጥተህ ፡ እይ ፡ ሲል ፡
፬ ሰማሁ ። ሌላም ፡ ዳማ ፡ ፈረስ ፡ ወጣ ÷ በእር
ሱም ፡ ላይ ፡ ለተቀመጠው ፡ ሰላምን ፡ ከምድር ፡
ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ ሰዎችም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡
እንዲተራረዱ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጠው ÷ ታላቅም ፡
ሰይፍ ፡ ተሰጠው ።
፭ ሦስተኛውንም ፡ ማኅተም ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፡
ሦስተኛው ፡ እንስሳ ፡— መጥተህ ፡ እይ ፡ ሲል ፡
ሰማሁ ። አየሁም ÷ እነሆም ÷ ጥቁር ፡ ፈረስ ፡
ወጣ ÷ በእርሱም ፡ ላይ ፡ የተቀመጠው ፡ በእጁ ፡
፮ ሚዛን ፡ ያዘ ። በአራቱም ፡ እንስሶች ፡ መካከል ፡
ድምፅ ፡— አንድ ፡ እርቦ ፡ስንዴ ፡ በዲናር ፡ ሦስት ፡
እርቦ ፡ ገብስም ፡ በዲናር ÷ ዘይትንና ፡ ወይንንም ፡
አትጕዳ ፡ ሲል ፡ ሰማሁ ።
፯ አራተኛውንም ፡ ማኅተም ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፡ የአ
ራተኛው ፡ እንስሳ ፡ ድምፅ ፡— መጥተህ ፡ እይ ፡
፰ ሲል ፡ ሰማሁ ። አየሁም ÷ እነሆም ÷ ሐመር ፡
ፈረስ ፡ ወጣ ÷ በእርሱም ፡ ላይ ፡ የተቀመጠው ፡
ስሙ ፡ ሞት ፡ ነበረ ። ሲኦልም ፡ ተከተለው ፤
በሰይፍና ፡ በራብም ፡ በሞትም ፡ በምድርም ፡
አራዊት ፡ ይገድሉ ፡ ዘንድ ፡ ከምድር ፡ በአራተ
ኛው ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጣቸው ።
፱ አምስተኛውንም ፡ ማኅተም ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ÷
ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃልና ፡ ስለ ፡ ጠበቁት ፡
ምስክር ፡ የታረዱትን ፡ የሰዎች ፡ ነፍሳት ፡ ከመ
፲ ሠዊያ ፡ በታች ፡ አየሁ ። በታላቅ ፡ ድምፅም ፡
እየጮኹ ፡— ቅዱስና ፡ እውነተኛ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ÷
እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ አትፈርድም ፡ ደማችን
ንስ ፡ በምድር ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡
፲፩ አትበቀልም ? አሉ ። ለእያንዳንዳቸውም ፡
ነጭ ፡ ልብስ ፡ ተሰጣቸው ÷ እንደ ፡ እነርሱም ፡
ደግሞ ፡ ይገደሉ ፡ ዘንድ ፡ ያላቸው ፡ የባሪያ
ዎች ፡ ባልንጀራዎቻቸውና ፡ የወንድሞቻቸው ፡
ቍጥር ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ÷ ገና ፡ ጥቂት ፡
ዘመን ፡ እንዲያርፉ ፡ ተባለላቸው ።
፲፪ ስድስተኛውንም ፡ ማኅተም ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፡
አየሁ ÷ ታላቅም ፡ የምድር ፡ መናወጥ ፡ ሆነ ÷ ፀሐ
ይም ፡ እንደ ፡ ማቅ ፡ ጠጕር ፡ ጥቁር ፡ ሆነ ÷ ጨረ
፲፫ ቃም ፡ በሞላው ፡ እንደ ፡ ደም ፡ ሆነ ÷ በለስም ፡
በብርቱ ፡ ነፋስ ፡ ተናውጣ ፡ ቃርያዋን ፡ ፍሬ ፡ እን
ደምትጥል ፡ የሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ ወደ ፡ ምድር ፡
፲፬ ወደቁ ÷ ሰማይም ፡ እንደ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጠቅልሎ ፡
አለፈ ÷ ተራራዎችና ፡ ደሴቶችም ፡ ሁሉ ፡ ከስፍ
፲፭ ራቸው ፡ ተወሰዱ ። የምድርም ፡ ነገሥታትና ፡
መኳንንት ፡ ሻለቃዎችም ፡ ባለ ፡ ጠጋዎችም ፡ ኃይ
ለኛዎችም ፡ ባሪያዎችም ፡ ጌቶችም ፡ ሁሉ ፡ በዋ
፲፮ ሻችና ፡ በተራራዎች ፡ ዓለቶች ፡ ተሰወሩ ÷ ተራ
ራዎችንና ፡ ዓለቶችንም ፡— በላያችን ፡ ውደቁ ፡
በዙፋንም ፡ ከተቀመጠው ፡ ፊት ፡ ከበጉም ፡
ቍጣ ፡ ሰውሩን ፤ ታላቁ ፡ የቍጣው ፡ ቀን ፡ መጥ ፲፯
ቶአልና ÷ ማንስ ፡ ሊቆም ፡ ይችላል ? አሉአ
ቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በአራቱ ፡ በምድር ፡ ማዕዘን ፡ ፩
ቆመው ፡ አራት ፡ መላእክት ፡ አየሁ ÷ እነርሱም ፡
ነፋስ ፡ በምድር ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በባሕር ፡
ወይም ፡ በማንም ፡ ዛፍ ፡ እንዳይነፍስ ፡ አራቱን ፡
የምድር ፡ ነፋሳት ፡ ያዙ ። የሕያው ፡ እምላክ ፡ ፪
ማኅተም ፡ ያለውም ፡ ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከፀሐይ ፡
መውጫ ፡ ሲወጣ ፡ አየሁ ÷ ምድርንና ፡ ባሕር
ንም ፡ ሊጐዱ ፡ ስተሰጣቸው ፡ ለአራቱ ፡ መላእ
ክት ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ እየጮኸ ፡— የአምላክ ፫
ችንን ፡ ባሪያዎች ፡ ግምባራቸውን ፡ እስክናትማ
ቸው ፡ ድረስ ፡ ምድርን ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ባሕርን ፡
ወይም ፡ ዛፎችን ፡ አትጕዱ ፡ አላቸው ። የታ ፬
ተሙትንም ፡ ቍጥር ፡ ሰማሁ ፤ ከእስራኤል ፡
ልጆች ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡ የታተሙት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡
አራት ፡ ሺህ ፡ ነበሩ ። ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ አሥራ ፡ ፭
ሁለት ፡ ሺህ ፡ ታተሙ ÷ ከሮቤል ፡ ነገድ ፡ አሥራ ፡
ሁለት ፡ ሺህ ÷ ከጋድ ፡ ነገድ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡
ሺህ ÷ ከአሴር ፡ ነገድ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ÷ ፮
ከንፍታሌም ፡ ነገድ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ÷
ከምናሴ ፡ ነገድ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ÷ ከስም ፯
ዖን ፡ ነገድ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ÷ ከሌዊ ፡ ነገድ ፡
አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ÷ ከይሳኮር ፡ ነገድ ፡ አሥራ ፡
ሁለት ፡ ሺህ ÷ ከዛብሎን ፡ ነገድ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ፰
ሺህ ÷ ከዮሴፍ ፡ ነገድ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ÷
ከብንያም ፡ ነገድ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡
ታተሙ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አየሁ ÷ እነሆም ÷ አንድ ፡ እንኳ ፡ ፱
ሊቈጥራቸው ፡ የማይችል ፡ ከሕዝብና ፡ ከነገድ ፡
ከወገንም ፡ ከቋንቋም ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡
ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ ነጭ ፡ ልብስም ፡ ለብሰው ፡ የዘ
ንባባንም ፡ ዝንጣፊዎች ፡ በእጆቻቸው ፡ ይዘው ፡
በዙፋኑና ፡ በበጉ ፡ ፊት ፡ ቆሙ ፤ በታላቅም ፡ ፲
ድምፅ ፡ እየጮኹ ፡—
በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ለተቀመጠው ፡ ለአምላክ
ችንና ፡ ለበጉ ፡ ማዳን ፡ ነው ፡
አሉ ። መላእክቱም ፡ ሁሉ ፡ በዙፋኑና ፡ በሽማ ፲፩
ግሌዎቹ ፡ በአራቱም ፡ እንስሶቹ ፡ ዙሪያ ፡ ቆመው ፡
ነበር ፤ በዙፋኑም ፡ ፊት ፡ በግምባራቸው ፡
ተደፉ ÷ ለእግዚአብሔርም ፡ እየሰገዱ ፡—
አሜን ÷ በረከትና ፡ ክብር ፡ ጥበብም ፡ ምስ ፲፪
ጋናም ፡ ውዳሴም ፡ ኃይልም ፡ ብርታትም ፡
ከዘላለም ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ ለአም
ላካችን ፡ ይሁን ፤ አሜን ፡
አሉ ።

፮ ። ፬ ፡ ዘካ. ፮ ÷ ፪ ፤ ማቴ. ፳፬ ÷ ፮ ፡ ፯ ። ፭ ፡ ዘካ. ፮ ÷ ፪ ። ፰ ፡ ሕዝ. ፲፬ ÷ ፳፩ ። ፲ ፡ መዝ. ፸፱ ÷ ፲ ፤ ዘካ. ፩ ÷ ፲፪ ። ፲፪ ፡ ኢዩ. ፪ ÷ ፴፩ ። ፲፫ ፡ ፲፬ ፡ ማቴ. ፳፬ ÷ ፳፱ ። ፲፬ ፡ ፲፭ ፡ ኢሳ. ፴፬ ÷ ፬ ። ፲፭ ፡ ኢሳ. ፪ ÷ ፲ ፡ ፲፱ ። ፲፮ ፡ ሆሴ. ፲ ÷ ፰ ፤ ሉቃ. ፳፫ ÷ ፴ ። ፲፯ ፡ ኢዩ. ፪ ÷ ፲፩ ።
፯ ። ፩ ፡ ዘካ. ፮ ÷ ፭ ። ፫ ፡ ሕዝ. ፱ ÷ ፬ ። ፱ ፡ ዮሐ. ፲፬ ÷ ፲፫ ። ፲ ፡ ም. ፬ ÷ ፲፩ ፤ መዝ. ፫ ÷ ፰ ። ፲፪ ፡ ም. ፬ ÷ ፲፩ ።

፲፫፤ ከሽማግሌዎቹም ፡ አንዱ ፡ ተመልሶ ፡— እነ
ዚህ ፡ ነጩን ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡ እነማን ፡ ናቸው ?
፲፬፤ ከወዴትስ ፡ መጡ ? አለኝ ። እኔም ፡— ጌታ ፡
ሆይ ፥ አንተ ፡ ታውቃለህ ፡ አልሁት ። አለ
ኝም ፡— እነዚህ ፡ ከታላቁ ፡ መከራ ፡ የመጡ ፡
ናቸው ፥ ልብሳቸውንም ፡ አጥበው ፡ በበጉ ፡
፲፭፤ ደም ፡ አነጹ ። ስለዚህ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ዙፋን ፡ ፊት ፡ አሉ ፥ ሌሊትና ፡ ቀንም ፡ በመቅ
ደሱ ፡ ያመልኩታል ፥ በዙፋኑም ፡ ላይ ፡ የተቀ
፲፮፤ መጠው ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ያድርባቸዋል ። ከእ
ንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይራቡም ፥ ከእንግዲህም ፡
ወዲህ ፡ አይጠሙም ፥ ፀሐይም ፡ ትኵሳትም ፡
፲፯፤ ሁሉ ፡ ከቶ ፡ አይወርድባቸውም ፤ በዙፋኑ ፡
መካከል ፡ ያለው ፡ በጉ ፡ እረኛቸው ፡ ይሆናልና ፥
ወደ ፡ ሕይወትም ፡ ውኃ ፡ ምንጭ ፡ ይመራቸዋ
ልና ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንባዎችን ፡ ሁሉ ፡
ከዓይናቸው ፡ ያብሳል ።

## ምዕራፍ ፡ ፰ ።

፩፤ ሰባተኛውንም ፡ ማኅተም ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፡
እኵል ፡ ሰዓት ፡ የሚያህል ፡ ዝምታ ፡ በሰማይ ፡
፪፤ ሆነ ። በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ የሚቆሙትን ፡
ሰባቱን ፡ መላእክት ፡ አየሁ ፥ ሰባትም ፡ መለከት ፡
፫፤ ተሰጣቸው ። ሌላም ፡ መልአክ ፡ መጣና ፡ የወ
ርቅ ፡ ጥና ፡ ይዞ ፡ በመሠዊያው ፡ አጠገብ ፡ ቆመ ፤
በዙፋኑም ፡ ፊት ፡ ባለው ፡ በወርቅ ፡ መሠዊያ ፡
ላይ ፡ ለቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡ ጸሎት ፡ እንዲጨምረው ፡
፬፤ ብዙ ፡ ዕጣን ፡ ተሰጠው ። የዕጣኑም ፡ ጢስ ፡ ከቅ
ዱሳን ፡ ጸሎት ፡ ጋር ፡ ከመልአኩ ፡ እጅ ፡ በእግዚ
፭፤ አብሔር ፡ ፊት ፡ ወጣ ። መልአኩም ፡ ጥናውን ፡
ይዞ ፡ የመሠዊያውን ፡ እሳት ፡ ሞላበት ፡ ወደ ፡
ምድርም ፡ ጣለው ፤ ነጐድጓድና ፡ ድምፅም ፡
መብረቅም ፡ መናወጥም ፡ ሆነ ።
፮፤ ሰባቱንም ፡ መለከት ፡ የያዙ ፡ ሰባቱ ፡ መላእ
ክት ፡ ሊነፉ ፡ ተዘጋጁ ።
፯፤ ፊተኛውም ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፤ ደምም ፡ የተ
ቀላቀለበት ፡ በረዶና ፡ እሳት ፡ ሆነ ፥ ወደ ፡ ምድ
ርም ፡ ተጣለ ፤ የምድርም ፡ ሲሶው ፡ ተቃጠለ ፡
የዛፎችም ፡ ሲሶው ፡ ተቃጠለ ፡ የለመለመም ፡
ሣር ፡ ሁሉ ፡ ተቃጠለ ።
፰፤ ሁለተኛውም ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፤ በእሳት ፡ የሚ
ቃጠል ፡ ታላቅ ፡ ተራራን ፡ የሚመስል ፡ ነገር ፡
በባሕር ፡ ተጣለ ፤ የባሕርም ፡ ሲሶው ፡ ደም ፡
፱፤ ሆነ ፡ በባሕርም ፡ ከሚኖሩ ፡ ሕይወት ፡ ካላቸው ፡
ፍጥረቶች ፡ ሲሶው ፡ ሞተ ፡ የመርከቦችም ፡
ሲሶው ፡ ጠፋ ።
፲፤ ሦስተኛውም ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፤ እንደ ፡ ችቦም ፡
የሚቃጠል ፡ ታላቅ ፡ ኮከብ ፡ ከሰማይ ፡ ወደቀ ፥
ዐወንዞችና ፡ በውኃም ፡ ምንጮች ፡ ሲሶ ፡ ላይ ፡
ወደቀ ። የኮከቡም ፡ ስም ፡ እሬቶ ፡ ይባላል ። ፲፩፤
የውኃውም ፡ ሲሶ ፡ መራራ ፡ ሆነ ፡ መራራም ፡
ስለ ፡ ተደረገ ፡ በውኃው ፡ ጠንቅ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡
ሞቱ ።
አራተኛውም ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፤ የፀሐይ ፡ ፲፪፤
ሲሶና ፡ የጨረቃ ፡ ሲሶ ፡ የከዋክብትም ፡ ሲሶ ፡
ተመታ ፥ የእነዚህ ፡ ሲሶ ፡ ይጨልም ፡ ዘንድ ፥
የቀንም ፡ ሲሶው ፡ እንዳያበራ ፥ እንዲሁም ፡ የሌ
ሊት ።
እየሁም ፥ አንድም ፡ ንስር ፡ በሰማይ ፡ መካ ፲፫፤
ከል ፡ እየበረረ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡— ሊነፉ ፡ ያላ
ቸው ፡ የሦስቱ ፡ መላእክት ፡ መለከት ፡ ስለሚቀ
ረው ፡ ድምፅ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ለሚኖሩት ፡ ወዮላ
ቸው ፤ ወዮላቸው ፥ ወዮላቸው ፡ ሲል ፡ ሰማሁ ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

አምስተኛውም ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፤ ከሰማይም ፡ ፩፤
ወደ ፡ ምድር ፡ ወድቆ ፡ የነበረ ፡ ኮከብ ፡ አየሁ ፥
የጥልቁም ፡ ጕድጓድ ፡ መክፈቻ ፡ ተሰጠው ።
የጥልቁንም ፡ ጕድጓድ ፡ ከፈተው ፤ ጢስም ፡ ፪፤
ከታላቅ ፡ እቶን ፡ እንደሚወጣ ፡ ጢስ ፡ ሆኖ ፡
ከጕድጓዱ ፡ ወጣ ፡ ፀሐይና ፡ አየርም ፡ በጕድ
ጓዱ ፡ ጢስ ፡ ጨለሙ ። ከጢሱም ፡ አንበጣዎች ፡ ፫፤
ወደ ፡ ምድር ፡ ወጡ ፥ የምድርም ፡ ጊንጦች ፡
ሥልጣን ፡ እንዳላቸው ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጣቸው ።
የእግዚአብሔርም ፡ ማኅተም ፡ በግምባራቸው ፡ ፬፤
ከሌለባቸው ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ በምድር ፡ ያለውን ፡
ሣር ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ የለመለመ ፡
ነገር ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ዛፍ ፡ እንዳይጐዱ ፡
ተበለላቸው ። አምስትም ፡ ወር ፡ ሊሣቅዩአ ፭፤
ቸው ፡ ተሰጣቸው ፡ እንጂ ፡ ሊገድሉአቸው ፡ አይ
ደለም ፤ እነርሱም ፡ የሚሣቅዩት ፡ ሥቃይ ፡
ጊንጥ ፡ ሰውን ፡ ነድፎ ፡ እንደሚሣቅይ ፡ ነው ።
በዚያም ፡ ወራት ፡ ሰዎች ፡ ሞትን ፡ ይፈልጋሉ ፡ ፮፤
አያገኙትምም ፥ ሊሞቱም ፡ ይመኛሉ ፡ ሞትም ፡
ከእነርሱ ፡ ይሸሻል ።
የአንበጣዎቹም ፡ መልክ ፡ ስጦርነት ፡ እንደ ፡ ፯፤
ተዘጋጁ ፡ ፈረሶች ፡ ነው ፥ በራሳቸውም ፡ ላይ ፡
ወርቅ ፡ እንደሚመስሉ ፡ አክሊሎች ፡ ነበሩአ
ቸው ፥ ፊታቸውም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ነበረ ፤
የሴቶችን ፡ ጠጕር ፡ የሚመስል ፡ ጠጕር ፡ ነበራ ፰፤
ቸው ፥ ጥርሳቸውም ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ጥርስ ፡
ነበረ ፥ የብረት ፡ ጥሩር ፡ የሚመስልም ፡ ጥሩር ፡ ፱፤
ነበራቸው ፥ የክንፋቸውም ፡ ድምፅ ፡ ወደ ፡ ጦር
ነት ፡ እንደሚጋልቡ ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ፈረሶች ፡
ሰረገላዎች ፡ ድምፅ ፡ ነበረ ። እንደ ፡ ጊንጥም ፡ ፲፤
ጅራት ፡ ያለ ፡ ጅራት ፡ አላቸው ፡ በጅራታቸ
ውም ፡ መውጊያ ፡ አለ ፥ ሰዎችንም ፡ አምስት ፡
ወር ፡ እንዲጐዱ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ። በእነ ፲፩፤

፯። ፲፬፤ ማቴ ፳፰፡፳፰። ፲፭፤ ዮሐ ፩፡፲፬። ፲፯፤ ኢሳ ፵፱፡፲። ፲፯፤ መዝ ፳፫፡፩፤ ዮሐ ፲፡፲፤ ኢሳ ፳፭፡፰።
፰። [illegible]
፱። [illegible]

ርሱም ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ አላቸው ፡ እርሱም ፡ የጥ
ልቅ ፡ መልአክ ፡ ነው ፤ ስሙም ፡ በዕብራይስጥ ፡
አብዶን ፡ በግሪክም ፡ አጶልዮን ፡ ይባላል ።
፲፪ ፊተኛው ፡ ወዮ ፡ አልፎአል ፤ እነሆ ፤ ከዚህ ፡
በኋላ ፡ ገና ፡ ሁለት ፡ ወዮ ፡ ይመጣል ።
፲፫ ስድስተኛውም ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፤ በእግዚአ
ብሔርም ፡ ፊት ፡ ካለ ፡ በወርቅ ፡ ከተሠራ ፡ መሠ
፲፬ ዊያ ፡ ቀንዶች ፡ አንድ ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ ፤ መለከ
ትም ፡ ያለውን ፡ ስድስተኛውን ፡ መልአክ ፡—
በታላቁ ፡ ወንዝ ፡ በኤፍራጥስ ፡ የታሰሩትን ፡ አራ
፲፭ ቱን ፡ መላእክት ፡ ፍታቸው ፡ አለው ። የሰዎች
ንም ፡ ሢሶ ፡ እንዲገድሉ ፡ ለሰዓቱና ፡ ለቀኑ ፡ ለወ
ሩም ፡ ለዓመቱም ፡ ተዘጋጅተው ፡ የነበሩ ፡
፲፮ አራቱ ፡ መላእክት ፡ ተፈቱ ። የፈረሰኞችም ፡
ጭፍራ ፡ ቍጥር ፡ እልፍ ፡ ጊዜ ፡ እልፍ ፤ እልፍ ፡
ጊዜ ፡ እልፍ ፡ ነበረ ፤ ቍጥራቸውን ፡ ሰማሁ ።
፲፯ ፈረሶቹንና ፡ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ የተቀመጡትን ፡
እንዲሁ ፡ በራእይ ፡ አየሁ ፤ እሳትና ፡ ያክንት ፡
ዲንም ፡ የሚመስል ፡ ጥሩር ፡ ነበራቸው ፤ የፈ
ረሶቹም ፡ ራስ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ራስ ፡ ነበረ ፤ ከአ
፲፰ ፋቸውም ፡ እሳትና ፡ ጢስ ፡ ዲንም ፡ ወጣ ። ከአ
ፋቸውም ፡ በወጡት ፡ በእሳቱና ፡ በጢሱ ፡ በዲ
ኑም ፡ በእነዚህ ፡ ሦስት ፡ መቅሠፍቶች ፡ የሰዎቹ ፡
፲፱ ሢሶ ፡ ተገደለ ። የፈረሶቹ ፡ ሥልጣን ፡ በአፋቸ
ውና ፡ በጅራታቸው ፡ ነውና ፤ ጅራታቸው ፡ እባ
ብን ፡ ይመስላልና ፤ ራስም ፡ አላቸው ፡ በእርሱም ፡
ይጐዳሉ ።
፳ በእነዚህም ፡ መቅሠፍቶች ፡ ያልተገደሉት ፡
የቀሩቱ ፡ ሰዎች ፡ ለአጋንንትና ፡ ያዩ ፡ ወይም ፡
ይሰሙ ፡ ወይም ፡ ይሄዱ ፡ ዘንድ ፡ ለማይችሉ ፡
ከወርቅና ፡ ከብር ፡ ከናስም ፡ ከድንጋይም ፡ ከእ
ንጨትም ፡ ለተሠሩ ፡ ስጣዖቶች ፡ እንዳይሰግዱ ፡
፳፩ ስለ ፡ እጃቸው ፡ ሥራ ፡ ንስሐ ፡ አልገቡም ፤ ስለ ፡
መግደላቸውም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አስማ
ታቸው ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ዝሙታቸው ፡ ወይም ፡
ስለ ፡ ስርቆታቸው ፡ ንስሐ ፡ አልገቡም ።

## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

፩ ሌላም ፡ ብርቱ ፡ መልአክ ፡ ደመና ፡ ተጐናጽፎ ፡
ከሰማይ ፡ ሲወርድ ፡ አየሁ ፤ በራሱም ፡ ላይ ፡
ቀስተ ፡ ደመና ፡ ነበረ ፤ ፊቱም ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡
እግሮቹም ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ዓምዶች ፡ ነበሩ ፤
፪ የተከፈተችንም ፡ ታናሽ ፡ መጽሐፍ ፡ በእጁ ፡
ያዘ ። ቀኝ ፡ እግሩንም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ግራው
፫ ንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አኖረ ፤ እንደሚያገሣም ፡
አንበሳ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ። በጮኸም ፡
ጊዜ ፡ ሰባቱ ፡ ነጐድጓድ ፡ በየድምፃቸው ፡ ተና
፬ ገሩ ። ሰባቱ ፡ ነጐድጓድ ፡ በተናገሩ ፡ ጊዜ ፡ ልጽፍ ፡
አሰብሁ ፤ ከሰማይም ፡— ሰባቱ ፡ ነጐድጓድ ፡
የተናገሩትን ፡ ነገር ፡ በማኅተም ፡ ዝጋው ፡ አት
ጻፈውም ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ ። በባሕርና ፡ ፭
በምድርም ፡ ላይ ፡ ሲቆም ፡ ያየሁት ፡ መልአክ ፡
ቀኝ ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አሻቅቦ ፡ ዘረጋ ፤
ሰማይንና ፡ በእርሱም ፡ ያሉትን ፤ ምድርንና ፡ ፮
በእርስዋም ፡ ያሉትን ፤ ባሕርንና ፡ በእርሱም ፡
ያሉትን ፡ በፈጠረው ፤ ከዘላለምም ፡ እስከ ፡ ዘላ
ለም ፡ ድረስ ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ በሚኖረው ፡ ምሎ ፡—
ወደ ፡ ፊት ፡ አይዘገይም ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ሰባተኛው ፡ ፯
መልአክ ፡ ሊነፋ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ድምፁም ፡
በሚሰማበት ፡ ዘመን ፤ ለባሪያዎቹ ፡ ለነቢያት ፡
የምሥራች ፡ እንደ ፡ ሰበከላቸው ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ ምሥጢር ፡ ይፈጸማል ፡ አለ ።
ከሰማይም ፡ የሰማሁት ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ፰
ሲናገረኝና ፡— ሂድና ፡ በባሕርና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
ከሚቆመው ፡ መልአክ ፡ በእጁ ፡ ያለችውን ፡
የተከፈተችውን ፡ መጽሐፍ ፡ ውሰድ ፡ ሲል ፡
ሰማሁ ። ወደ ፡ መልአኩም ፡ ሄጄ ፡— ታናሺቱን ፡ ፱
መጽሐፍ ፡ ስጠኝ ፡ አልሁት ። እርሱም ፡—
ውሰድና ፡ ብላት ፤ ሆድህንም ፡ መራራ ፡ ታደር
ገዋለች ፡ በአፍህ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ማር ፡ ትጣፍጣ
ለች ፡ አለኝ ። ከመልአኩም ፡ እጅ ፡ ታናሺቱን ፡ ፲
መጽሐፍ ፡ ወስጄ ፡ በላኋት ፡ በአፌም ፡ እንደ ፡
ማር ፡ ጣፋጭ ፡ ሆነች ፤ ከበላኋት ፡ በኋላም ፡
ሆዴ ፡ መራራ ፡ ሆነ ። በብዙ ፡ ወገኖችና ፡ በአ ፲፩
ሕዛብም ፡ በቋንቋዎችም ፡ በነገሥታትም ፡ ላይ ፡
እንደ ፡ ገና ፡ ትንቢት ፡ ትናገር ፡ ዘንድ ፡ ይገባሃል ፡
ተባለልኝ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

በትር ፡ የሚመስል ፡ መስፈሪያ ፡ ለእኔ ፡ ተሰ ፩
ጠኝ ፡ እንዲህም ፡ ተባለልኝ ፡— ተነሥተህ ፡ የእ
ግዚአብሔርን ፡ መቅደስና ፡ መሠዊያውን ፡ በዚ
ያም ፡ የሚሰግዱትን ፡ ለካ ። በመቅደሱም ፡ ፪
ውጭ ፡ ያለው ፡ አደባባ ፡ ለአሕዛብ ፡ ተሰጥቶአ
ልና ፡ ተወው ፡ አትለከውም ፤ እነርሱም ፡ አርባ ፡
ሁለት ፡ ወር ፡ የተቀደሰችውን ፡ ከተማ ፡ ይረግ
ጡአታል ። ለሁለቱም ፡ ምስክሮቼ ፡ ማቅ ፡ ለብ ፫
ሰው ፡ ሺህ ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ቀን ፡ ትን
ቢት ፡ ሊናገሩ ፡ እሰጣለሁ ።
እነዚህ ፡ በምድር ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ የሚቆሙ ፡ ፬
ሁለቱ ፡ ወይራዎችና ፡ ሁለቱ ፡ መቅረዞች ፡
ናቸው ። ማንምም ፡ ሊጐዳቸው ፡ ቢወድ ፡ ፭
እሳት ፡ ከአፋቸው ፡ ይወጣል ፡ ጠላቶቻቸውንም ፡
ይበላል ፤ ማንም ፡ ሊጐዳቸው ፡ ቢወድም ፡ እን
ዲሁ ፡ ሊገደል ፡ ይገባዋል ። እነዚህ ፡ ትንቢት ፡ ፮
በሚናገሩበት ፡ ወራት ፡ ዝናብ ፡ እንዳይዘንብ ፡
ሰማይን ፡ ሊዘጉ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ፤ ውኆች
ንም ፡ ወደ ፡ ደም ፡ ሊለውጡ ፡ በሚፈልጉበትም ፡
ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በመቅሠፍት ፡ ሁሉ ፡ ምድርን ፡
ሊመቱ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ። ምስክራቸውን ፡ ፯

፱። ፲፫፤ ምዕ. ፰፥፫። ፳፤ መዝ. ፻፲፭፥፬—፲፭፤ ፩ ቆሮ. ፲፥፳።
፲። ፩፤ ... ፲፬፥፳፱። ፯፤ ዳን. ፲፪፥፯፤ መዝ. ... ፥ ፩፤ ... ፱፥ ፯። ፱፡ ፲፤ ሕዝ. ፫፥፩—፫። ፲፩፤ ኤር. ፩፥፲።
፲፩። ፩፤ ሕዝ. ፵፥፫። ፪፤ ሕዝ. ፵፥፲፯፤ ሉቃ. ፳፩፥፳፬። ፫፤ ... ፥፫፤ ፲፫፥፲፬። ፬፤ ፩ ነገሥ. ፩፥፲። ፭፤ ፩ ነገሥ. ፲፯፥፩፤ ዘፀ. ፯፥፲፱። ፮፤ ዳን. ፯፥፳፩።

ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ከጥልቁ ፡ የሚወጣው ፡ አውሬ ፡
ይዋጋቸዋል ፡ ያሸንፋቸውማል ፡ ይገድላቸው
፰፡ ማል ። በድናቸውም ፡ ለታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ አደባ
ባይ ፡ ይተኛል ፡ እርስዋም ፡ በመንፈሳዊ ፡ ምሳሌ ፡
ሰዶምና ፡ ግብጽ ፡ የተባለች ፡ ደግሞ ፡ ጌታቸው ፡
፱፡ የተሰቀሰበት ፡ ናት ። ከወገኖችና ፡ ከነገዶችም ፡
ከቋንቋዎችም ፡ ከአሕዛብም ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡
ሦስት ፡ ቀን ፡ ተኩል ፡ በድናቸውን ፡ ይመለከ
ታሉ ፥ በድናቸውም ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ሊገባ ፡
፲፡ አይፈቅዱም ። እነዚህም ፡ ሁለት ፡ ነቢያት ፡ በም
ድር ፡ የሚኖሩትን ፡ ስለ ፡ ሣቀዩ ፡ በምድር ፡ የሚ
ኖሩት ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ በደስ
ታም ፡ ይኖራሉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ስጦታ ፡
፲፩ ይሰጣጣሉ ። ከሦስቱ ፡ ቀን ፡ ተኩልም ፡ በኋላ ፡
ከእግዚአብሔር ፡ የወጣ ፡ የሕይወት ፡ መንፈስ ፡
ገባባቸው ፡ በእግሮቻቸውም ፡ ቆሙ ፥ ታላቅም ፡
ፍርሃት ፡ በሚመለከቱት ፡ ላይ ፡ ወደቀባቸው ።
፲፪፡ በሰማይም ፡— ወደዚህ ፡ ውጡ ፡ የሚላቸውን ፡
ታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ሰሙ ፤ ጠላቶቻቸውም ፡ እየተ
መለከቱአቸው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በደመና ፡ ወጡ ።
፲፫፡ በዚያም ፡ በዓት ፡ ታላቅ ፡ የምድር ፡ መናወጥ ፡
ሆነ ፥ ከከተማይቱም ፡ አሥረኛው ፡ እጅ ፡ ወደቀ ፥
በመናወጥም ፡ ሰባት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ተገደሉ ፥
የቀሩትንም ፡ ፍርሃት ፡ ያዛቸው ፥ ለሰማዩም ፡
አምላክ ፡ ክብር ፡ ሰጡ ።
፲፬፡ ሁለተኛው ፡ ወዮ ፡ አልፎአል ፤ እነሆ ፥ ሦስተ
ኛው ፡ ወዮ ፡ በቶሎ ፡ ይመጣል ።
፲፭፡ ሰባተኛውም ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፤ በሰማይም ፡—
የዓለም ፡ መንግሥት ፡ ለጌታችንና ፡ ለእ
ርሱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ሆነች ፥ ለዘላለምም ፡
እስከ ፡ ዘላለም ፡ ይነግሣል ፡
፲፮፡ የሚሉ ፡ ታላላቅ ፡ ድምፆች ፡ ሆኑ ። በእግዚአ
ብሔርም ፡ ፊት ፡ በዙፋኖቻቸው ፡ የተቀመጡ ፡
ሀያ ፡ አራቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ በግምባራቸው ፡ ተደ
፲፯፡ ፍተው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እየሰገዱ ፡ እንዲህ ፡
አሉ ፡—
ያለህና ፡ የነበርህ ፡ ሁሉን ፡ የምትገዛ ፡ ጌታ ፡
እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ትልቁን ፡ ኃይልህን ፡
ስለ ፡ ያዝህ ፡ ስለ ፡ ነግሥህም ፡ እናመሰግን
፲፰፡ ሃለን ፤ አሕዛብም ፡ ተቈጡ ፥ ቍጣህም ፡
መጣ ፥ በሙታንም ፡ ትፈርድ ፡ ዘንድ ፡
ዘመን ፡ መጣ ፥ ስባሪያዎችህም ፡ ለነቢያትና ፡
ለቅዱሳን ፡ ስምህንም ፡ ለሚፈሩት ፡ ለታ
ናናሾችና ፡ ለታላላቆችም ፡ ዋጋቸውን ፡
ትሰጥ ፡ ዘንድ ፥ ምድርንም ፡ የሚያጠፉትን ፡
ታጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ዘመን ፡ መጣ ።
፲፱፡ በሰማይም ፡ ያለው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅ
ደስ ፡ ተከፈተ ፥ የኪዳኑም ፡ ታቦት ፡ በመቅደሱ ፡
ታየ ፥ መብረቅና ፡ ድምፅም ፡ ነጐድጓድም ፡ የም
ድርም ፡ መናወጥ ፡ ታላቅም ፡ በረዶ ፡ ሆነ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

ታላቅ ፡ ምልክትም ፡ በሰማይ ፡ ታየ ፤ ፀሐይን ፡ ፩፡
ተጐናጽፋ ፡ ጨረቃ ፡ ከእግሮችዋ ፡ በታች ፡ ያላት ፡
በራስዋም ፡ ላይ ፡ የአሥራ ፡ ሁለት ፡ ከዋክብት ፡
አክሊል ፡ የሆነላት ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ነበረች ።
እርስዋም ፡ ፀንሳ ፡ ነበር ፥ ምጥም ፡ ተይዛ ፡ ልትወ ፪፡
ልድ ፡ ተጨንቃ ፡ ጮኸች ። ሌላም ፡ ምልክት ፡ ፫፡
በሰማይ ፡ ታየ ፤ እነሆም ፡ ታላቅ ፡ ቀይ ፡ ዘንዶ ፤
ሰባት ፡ራሶችና ፡ አሥር ፡ ቀንዶችም ፡ ነበሩት ፡
በራሶቹም ፡ ላይ ፡ ሰባት ፡ ዘውዶች ፡ ነበሩ ፥ ጅራ ፬፡
ቱም ፡ የሰማይን ፡ ከዋክብት ፡ ሲሶ ፡ እየሳበ ፡
ወደ ፡ ምድር ፡ ጣላቸው ። ዘንዶውም ፡ ሴቲቱ ፡
በወለደች ፡ ጊዜ ፡ ሕፃንዋን ፡ እንዲበላ ፡ ልትወ
ልድ ፡ ባላት ፡ ሴት ፡ ፊት ፡ ቆመ ። አሕዛብንም ፡ ፭፡
ሁሉ ፡ በብረት ፡ በትር ፡ ይገዛቸው ፡ ዘንድ ፡ ያለ
ውን ፡ ልጅ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ፤ ልጅዋም ፡
ወደ ፡ እግዚአብሔርና ፡ ወደ ፡ ዙፋኑ ፡ ተነጠቀ ።
ሴቲቱም ፡ ሺህ ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ቀን ፡ ፮፡
በዚያ ፡ እንዲመግቡአት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተዘ
ጋጅቶላት ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ በረሀ ፡
ሸሸች ።
በሰማይም ፡ ሰልፍ ፡ ሆነ ፤ ሚካኤልና ፡ መላ ፯፡
እክቱ ፡ ዘንዶውን ፡ ተዋጉ ። ዘንዶውም ፡ ከመ
ላእክቱ ፡ ጋር ፡ ተዋጋ ፥ አልቻላቸውምም ፥ ከዚ ፰፡
ያም ፡ወዲያ ፡ በሰማይ ፡ ስፍራ ፡ አልተገኘላቸ
ውም ። ዓለሙንም ፡ ሁሉ ፡ የሚያስተው ፥ ዲያ ፱፡
ብሎስና ፡ ሰይጣን ፡ የሚባለው ፡ ታላቁ ፡ ዘንዶ ፡
እርሱም ፡ የቀደመው ፡ እባብ ፡ ተጣለ ፤ ወደ ፡
ምድር ፡ ተጣለ ፡ መላእክቱም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
ተጣሉ ። ታላቅም ፡ ድምፅ ፡ በሰማይ ፡ ሰማሁ ፡ ፲፡
እንዲህ ፡ ሲል ፡—
አሁን ፡ የአምላካችን ፡ ማዳንና ፡ ኃይል ፡
መንግሥትም ፡ የክርስቶስም ፡ ሥልጣን ፡
ሆነ ፥ ቀንና ፡ ሌሊትም ፡ በአምላካችን ፡ ፊት ፡
የሚከሳቸው ፡ የወንድሞቻችን ፡ ከሳሽ ፡
ተጥሎአልና ። እነርሱም ፡ ከበጉ ፡ ደም ፡ ፲፩
የተነሣ ፡ ከምስክራቸውም ፡ ቃል ፡ የተነሣ ፡
ድል ፡ነሡት ፥ ነፍሳቸውንም ፡ እስከ ፡ ሞት ፡
ድረስ ፡ አልወደዱም ። ስለዚህ ፥ ሰማይና ፡ ፲፪
በውስጡ ፡ የምታድሩ ፡ ሆይ ፥ ደስ ፡ ይበላ
ችሁ ፤ ለምድርና ፡ ለባሕር ፡ ወዮላቸው ፥
ዲያብሎስ ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ እንዳለው ፡
አውቆ ፡ በታላቅ ፡ ቍጣ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡
ወርዶአልና ።
ዘንዶውም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ተጣለ ፡ ፲፫
ባየ ፡ ጊዜ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ የወለደችውን ፡ ሴት ፡
አሳደዳት ። ከእባቡም ፡ ፊት ፡ ርቃ ፡ አንድ ፡ ፲፬

፲፩ ። ፰ ፤ ኢሳ. ፩ ፥ ፲ ፤ ሉቃ. ፲፫ ፥ ፴፬ ። ፲፩ ፤ ሕዝ. ፴፯ ፥ ፭ ፡ ፲ ። ፲፭ ፤ ዳን. ፯ ፥ ፲፬ ። ፲፯ ፤ ም. ፬ ፥ ፲፭ ። ፲፰ ፤ ም. ፱ ፥ ፩ ፤ መዝ. ፪ ፥ ፩ ፡ ፭ ። ፲፱ ፤ ፩ ነገሥ. ፰ ፥ ፩ ፡ ፮ ።
፲፪ ። ፪ ፤ ሚክ. ፬ ፥ ፲ ። ፫ ፤ ዳን. ፯ ፥ ፯ ። ፬ ፤ ዳን. ፰ ፥ ፲ ። ፭ ፤ መዝ. ፪ ፥ ፱ ። ፯ ፤ ዳን. ፲ ፥ ፲፫ ፤ ይሁዳ ፱ ። ፱ ፤ ዘፍጥ. ፫ ፥ ፩ ፤ ሉቃ. ፲ ፥ ፲፰ ። ፲ ፤ ኢዮብ ፩ ፥ ፱—፲፩ ። ፲፩ ፤ ሮሜ ፰ ፥ ፴፯ ። ፲፪ ፤ ኢሳ. ፵፱ ፥ ፲፫ ። ፲፬ ፤ ዘፀአ. ፲፱ ፥ ፬ ፤ ዳን. ፯ ፥ ፳፭ ።

ዘመን ፥ ዘመናትም ፥ የዘመንም ፡ እኩሌታ ፡ ወደ
ምትመገብበት ፡ ወደ ፡ ስፍራዋ ፡ ወደ ፡ በረሀ ፡ እን
ድትበር ፡ ለሴቲቱ ፡ ሁለት ፡ የታላቁ ፡ ንሥር ፡
፲፭ ክንፎች ፡ ተሰጣት ። እባቡም ፡ ሴቲቱ ፡ በወንዝ ፡
እንድትወሰድ ፡ ሊያደርግ ፡ ወንዝ ፡ የሚያህልን ፡
፲፮ ውኃ ፡ ከአፉ ፡ በስተ ፡ ኋላዋ ፡ አፈሰሰ ። ምድሪ
ቱም ፡ ሴቲቱን ፡ ረዳቻት ፥ ምድሪቱም ፡ አፍዋን ፡
ከፍታ ፡ ዘንዶው ፡ ከአፉ ፡ ያፈሰሰውን ፡ ወንዝ ፡
፲፯ ዋጠችው ። ዘንዶውም ፡ በሴቲቱ ፡ ላይ ፡ ተቈ
ጥቶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዛት ፡ የሚጠብ
ቁትን ፡ የኢየሱስም ፡ ምስክር ፡ ያላቸውን ፡ ከዘ
ርዋ ፡ የቀሩትን ፡ ሊዋጋ ፡ ሄደ ፤ በባሕርም ፡
አሸዋ ፡ ላይ ፡ ቆመ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

፩ አንድም ፡ አውሬ ፡ ከባሕር ፡ ሲወጣ ፡ አየሁ ፤
አሥር ፡ ቀንዶችና ፡ ሰባት ፡ ራሶች ፡ ነበሩት ፥ በቀ
ንዶቹም ፡ ላይ ፡ አሥር ፡ ዘውዶች ፡ በራሶቹም ፡
፪ ላይ ፡ የስድብ ፡ ስም ፡ ነበረ ። ያየሁትም ፡ አውሬ ፡
ነብር ፡ ይመስል ፡ ነበር ፥ እግሮቹም ፡ እንደ ፡ ድብ ፡
እግሮች ፥ አፉም ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ አፍ ፡ ነበሩ ።
ዘንዶውም ፡ ኃይሉንና ፡ ዙፋኑን ፡ ትልቅም ፡
፫ ሥልጣን ፡ ሰጠው ። ከራሶቹም ፡ ለሞት ፡ እንደ ፡
ታረደ ፡ ሆኖ ፡ አንዱን ፡ አየሁ ፥ ለሞቱ ፡ የሆነ
ውም ፡ ቍስል ፡ ተፈወሰ ። ምድርም ፡ ሁሉ ፡
፬ አውሬውን ፡ እየተከተለ ፡ ተደነቀ ፥ ለዘንዶውም ፡
ሰገዱለት ፥ ለአውሬው ፡ ሥልጣንን ፡ ሰጥቶታ
ልና ፤ ለአውሬውም ፡— አውሬውን ፡ ማን ፡ ይመ
ስለዋል ፥ እርሱንስ ፡ ሊዋጋ ፡ ማን ፡ ይችላል ?
እያሉ ፡ ሰገዱለት ።
፭ ታላቅንም ፡ ነገርና ፡ ስድብን ፡ የሚናገርበት ፡
አፍ ፡ ተሰጠው ፥ በአርባ ፡ ሁለት ፡ ወርም ፡ እንዲ
፮ ሠራ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጠው ። እግዚአብሔር
ንም ፡ ለመሳደብ ፡ ስሙንና ፡ ማደሪያውንም ፡
በሰማይም ፡ የሚያድሩትን ፡ ሊሳደብ ፡ አፉን ፡
፯ ከፈተ ። ቅዱሳንንም ፡ ይዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ድልም ፡
ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ተሰጠው ፥ በነገድና ፡ በወ
ገንም ፡ በቋንቋም ፡ በሕዝብም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሥል
፰ ጣን ፡ ተሰጠው ። ከዓለምም ፡ ፍጥረት ፡ ጀምሮ ፡
በታረደው ፡ በግ ፡ ሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ስሞቻ
ቸው ፡ ያልተጻፉ ፡ በምድር ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ይሰ
፱ ግዱለታል ። ጆሮ ፡ ያለው ፡ ቢኖር ፡ ይስማ ።
፲ ይማረክ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ማንም ፡ ቢኖር ፡ ወደ ፡
ምርኮነት ፡ ይሄዳል ፤ በሰይፍ ፡ የሚገድል ፡
ማንም ፡ ቢኖር ፡ ራሱ ፡ በሰይፍ ፡ እንዲገደል ፡ ይገ
ባዋል ። የቅዱሳን ፡ ትዕግሥትና ፡ እምነት ፡
በዚህ ፡ ነው ።
፲፩ ሌላም ፡ አውሬ ፡ ከምድር ፡ ሲወጣ ፡ አየሁ ፥
የበግ ፡ ቀንዶችን ፡ የሚመስሉ ፡ ሁለት ፡ ቀን
ዶችም ፡ ነበሩት ፡ እንደ ፡ ዘንዶም ፡ ይናገር ፡
፲፪ ነበር ። በፊተኛውም ፡ አውሬ ፡ ሥልጣን ፡ በእ
ርሱ ፡ ፊት ፡ ሁሉን ፡ ያደርጋል ። ለሞቱ ፡ የሆ
ነውም ፡ ቍስል ፡ ተፈወሰለት ፡ ለፊተኛው ፡
አውሬ ፡ ምድርና ፡ በእርሱ ፡ የሚኖሩት ፡ እንዲ
ሰግዱለት ፡ ያደርጋል ። እሳትንም ፡ እንኳ ፡ ከሰ ፲፫
ማይ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ እስኪያወ
ርድ ፡ ድረስ ፡ታላላቆችን ፡ ምልክቶች ፡ ያደር
ጋል ። በአውሬውም ፡ ፊት ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ፲፬
ከተሰጡት ፡ ምልክቶች ፡ የተነሣ ፡ በምድር ፡
የሚኖሩትን ፡ ያስታል ፤ የሰይፍም ፡ ቍስል ፡
ለነበረውና ፡ በሕይወት ፡ ለኖረው ፡ ለአውሬው ፡
ምስልን ፡ እንዲያደርጉ ፡ በምድር ፡ የሚኖሩትን ፡
ይናገራል ። የአውሬው ፡ ምስል ፡ ሊናገር ፡ ፲፭
እንኳ ፡ ለአውሬውም ፡ ምስል ፡ የማይሰግዱለትን ፡
ሁሉ ፡ ሊያስገድላቸው ፥ ለአውሬው ፡ ምስል ፡
ትንፋሽ ፡ እንዲሰጠው ፡ ተሰጠው ። ታናናሾ ፲፮
ችና ፡ ታላላቆችም ፡ ባለ ፡ ጠጋዎችና ፡ ድሆችም ፡
ጌታዎችና ፡ ባሪያዎችም ፡ ሁሉ ፡ በቀኝ ፡ እጃ
ቸው ፡ ወይም ፡ በግምባራቸው ፡ ምልክትን ፡
እንዲቀበሉ ፥ የአውሬውም ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ፲፯
የስሙ ፡ ቍጥር ፡ ያለው ፡ ምልክት ፡ የሌለበት ፡
ማንም ፡ ሊገዛ ፡ ወይም ፡ ሊሸጥ ፡ እንዳይችል ፡
ያደርጋል ። ጥበብ ፡ በዚህ ፡ አለ ። አእምሮ ፡ ፲፰
ያለው ፡ የአውሬውን ፡ ቍጥር ፡ ይቍጠረው ፤
ቍጥሩ ፡ የሰው ፡ ቍጥር ፡ ነውና ፥ ቍጥሩም ፡
ስድስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ስድስት ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

አየሁም ፥ እነሆም ፥ በጉ ፡ በጽዮን ፡ ተራራ ፡ ፩
ቆሞ ፡ ነበር ፥ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ስሙና ፡ የአባቱ ፡
ስም ፡ በግምባራቸው ፡ የተጻፈላቸው ፡ መቶ ፡
አርባ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ ነበሩ ። እንደ ፡ ብዙ ፡ ፪
ውኃም ፡ ድምፅና ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ነጐድጓድ ፡
ድምፅ ፡ ያለ ፡ ከሰማይ ፡ ድምፅን ፡ ሰማሁ ፥ ደርዳ
ሪዎችም ፡ በገና ፡ እንደሚደረድሩ ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡
ሰማሁ ። በዙፋኑም ፡ ፊት ፡ በአራቱም ፡ እንስሶ ፫
ችና ፡ በሽማግሌዎቹ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ ቅኔ ፡ ዘመሩ ፤
ከምድርም ፡ ከተዋጁት ፡ ከመቶ ፡ አርባ ፡ አራት ፡
ሺህ ፡ በቀር ፡ ያን ፡ ቅኔ ፡ ሊማር ፡ ለማንም ፡ አል
ተቻለውም ። ከሴቶች ፡ ጋር ፡ ያልረከሱ ፡ እን ፬
ዚህ ፡ ናቸው ፥ ድንግሎች ፡ ናቸውና ። በጉ ፡
ወደሚሄድበት ፡ የሚከተሉት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።
ለእግዚአብሔርና ፡ ለበጉ ፡ በኵራት ፡ እንዲሆኑ ፡
ከሰዎች ፡ የተዋጁ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። በአፋቸ ፭
ውም ፡ ውሸት ፡ አልተገኘም ፤ ነውር ፡ የለባቸ
ውም ።
በምድርም ፡ ለሚኖሩ ፡ ለሕዝብም ፡ ለነገድም ፡ ፮
ለቋንቋም ፡ ለወገንም ፡ ሁሉ ፡ ይሰብክ ፡ ዘንድ ፡
የዘላለም ፡ ወንጌል ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከሰ
ማይ ፡ መካከል ፡ ሲበር ፡ አየሁ ፤ በታላቅ ፡ ድም ፯
ፅም ፡— የፍርዱ ፡ ሰዓት ፡ ደርሶአልና ፡ እግዚአ
ብሔርን ፡ ፍሩ ፡ ክብርንም ፡ ስጡት ፤ ሰማይንና ፡

፲፫። ፩ ፡ ፪ ፤ ዳን ፡ ፯ ፡ ፫—፯ ። ፭ ፤ ዳን ፡ ፯ ፡ ፰ ። ፯ ፤ ዳን ፡ ፯ ፡ ፳፩ ። ፰ ፤ ም ፡ ፫ ፡ ፭ ፤ ፩ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።
፲ ፤ ኤር ፡ ፲፭ ፡ ፪ ፤ ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፶፪ ። ፲፩ ፤ ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፭ ። ፲፫ ፤ ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፳፬ ፤ ፪ ተሰ ፡ ፩ ፡ ፲ ። ፲፬ ፤ ዘዳግ ፡ ፲፫ ፡ ፩ ፡ ፪ ።
፲፬። ፩ ፤ ም ፡ ፭ ፡ ፮ ፤ ፯ ፡ ፬ ፤ ፫ ፡ ፲፪ ፤ መዝ ፡ ፪ ፡ ፮ ። ፪ ፤ ም ፡ ፩ ፡ ፲፭ ። ፭ ፤ ሶፎ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ። ፯ ፤ ም ፡ ፲ ፡ ፯ ።

ምድርንም ፡ ባሕርንም ፡ የውኃንም ፡ ምንጮች ፡
ለሠራው ፡ ስገዱለት ፡ አለ ።
፰፤ ሌላም ፡ ሁለተኛ ፡ መልአክ ፡— አሕዛብን ፡
ሁሉ ፡ የዝሙትዋን ፡ ቍጣ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ያጠ
ጣች ፡ ታላቂቱ ፡ ባቢሎን ፡ ወደቀች ÷ ወደቀች ፡
እያለ ፡ ተከተለው ።
፱፤ ሦስተኛም ፡ መልአክ ፡ ተከተላቸው ÷ በታላቅ ፡
ድምፅ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡— ለአውሬውና ፡ ለም
ስሉ ፡ የሚሰግድ ፡ በግምባሩም ፡ ወይም ፡ በእጁ ፡
፲፤ ምልክቱን ፡ የሚቀበል ፡ ማንም ፡ ቢኖር ÷ እርሱ ፡
ደግሞ ፡ በቍጣው ፡ ጽዋ ፡ ሳይቀላቅል ፡ ከተዘጋ
ጀው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡
ይጠጣል ÷ በቅዱሳንም ፡ መላእክትና ፡ በበጉ ፡
፲፩፤ ፊት ፡ በእሳትና ፡ በዲን ፡ ይሣቀያል ። የሥቃያ
ቸውም ፡ ጢስ ፡ ለዘላለም ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡
ይወጣል ÷ ለአውሬውና ፡ ለምስሉም ፡ የሚሰ
ግዱ ፡ የስሙንም ፡ ምልክት ፡ የሚቀበል ፡ ሁሉ ፡
ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ዕረፍት ፡ የላቸውም ።
፲፪፤ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዛት ፡ የሚጠብቁት ፡
ኢየሱስንም ፡ በማመን ፡ የሚጸኑት ፡ ቅዱሳን ፡
ትዕግሥታቸው ፡ በዚህ ፡ ነው ።
፲፫፤ ከሰማይም ፡— አሁንጋዲህ ፡ ወዲህ ፡ በጌታ ፡
የሚሞቱ ፡ ሙታን ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። መን
ፈስ ፡— አዎን ÷ ከድካማቸው ፡ ያርፉ ፡ ዘንድ ÷
ሥራቸውም ፡ ይከተላቸዋል ፡ ይላል ፡ ብለህ ፡
ጻፍ ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ ።
፲፬፤ እየሁም ÷ እነሆም ፡ ነጭ ፡ ደመና ÷ በደመና
ውም ፡ ላይ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ የሚመስል ፡ ተቀ
ምጦአል ÷ በራሱም ፡ ላይ ፡ የወርቅ ፡ አክሊል ፡
፲፭፤ በእጁም ፡ ስለታም ፡ ማጭድ ፡ ነበረው ። ሌላ ፡
መልአክም ፡ ከመቅደሱ ፡ ወጥቶ ፡ በደመናው ፡
ላይ ፡ ለተቀመጠው ፡— የማጨድ ፡ ሰዓት ፡ ስለ ፡
ደረሰ ፡ ማጭድህን ፡ ስደድና ፡ እጨድ ÷ የም
ድሪቱ ፡ መከር ፡ ጠውልጓልና ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡
፲፮፤ ድምፅ ፡ ጮኸ ። በደመናውም ፡ ላይ ፡ የተቀ
መጠው ፡ ማጭዱን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ጣለው ፡
ምድርም ፡ ታጨደች ።
፲፯፤ ሌላ ፡ መልአክም ፡ በሰማይ ፡ ካለው ፡ መቅደስ ፡
ወጣ ÷ እርሱም ፡ ደግሞ ፡ ስለታም ፡ ማጭድ ፡
፲፰፤ ነበረው ። በእሳትም ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡
ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከመሠዊያው ፡ ወጥቶ ፡ ስለታም ፡
ማጭድ ፡ ያለውን ፡— ዘለላዎቹ ፡ ፈጽመው ፡
በስለዋልና ፡ ስለታሙን ፡ ማጭድህን ፡ ስደድና ፡
በምድር ፡ ያለውን ፡ የወይን ፡ ዛፍ ፡ ዘለላዎች ፡
፲፱፤ ቍረጥ ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጠራ ። መል
አኩም ፡ ማጭዱን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ጣለው ÷
በምድርም ፡ ካለው ፡ ከወይን ፡ ዛፍ ፡ ቈረጠ ፡ ወደ ፡
ታላቁ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ መጥመ
፳፤ ቂያ ፡ ጣለ ። የወይኑም ፡ መጥመቂያ ፡ ከከተማ ፡
ውጭ ፡ ተረገጠ ÷ እስከ ፡ ፈረሶች ፡ ልጓምም ፡
የሚደርስ ፡ ደም ፡ ርቀቱ ፡ ሺህ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡
ምዕራፍ ፡ ሆኖ ፡ ከመጥመቂያው ፡ ወጣ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

ሌላም ፡ ታላቅና ፡ ድንቅ ፡ ምልክት ፡ በሰማይ ፡ ፩፤
እየሁ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በእነርሱ ፡ ስለ
ሚፈጸም ፡ ኋለኞቹን ፡ ሰባት ፡ መቅሠፍቶች ፡
የያዙ ፡ ሰባት ፡ መላእክት ፡ ታዩ ።
በእሳትም ፡ የተቀላቀለውን ፡ የብርጭቆ ፡ ፪፤
ባሕር ፡ የሚመስለውን ፡ እየሁ ÷ በአውሬውና ፡
በምስሉም ፡ በስሙም ፡ ቍጥር ፡ ላይ ፡ ድል ፡ ነሥ
ተው ፡ የነበሩት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ በገና ፡
ይዘው ፡ በብርጭቆ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ሲቆሙ ፡
እየሁ ።

ሁሉን ፡ የምትገዛ ፡ ጌታ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ÷ ፫ ፡ ፬
ሥራህ ፡ ታላቅና ፡ ድንቅ ፡ ነው ፤ የአሕዛብ ፡
ንጉሥ ፡ ሆይ ÷ መንገድህ ፡ ጻድቅና ፡ እው
ነተኛ ፡ ነው ፤ ጌታ ፡ ሆይ ÷ የማይፈራህና ፡
ስምህን ፡ የማያከብር ፡ ማን ፡ ነው ? አንተ ፡
ብቻ ፡ ቅዱስ ፡ ነህና ÷ የጽድቅም ፡ ሥራህ ፡
ስለ ፡ ተገለጠ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ይመጣሉ ፡
በፊትህም ፡ ይሰግዳሉ ፡

እያሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ባሪያ ፡ የሙሴን ፡
ቅኔና ፡ የበጉን ፡ ቅኔ ፡ ይዘምራሉ ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እየሁ ÷ የምስክርም ፡ ድን ፭፤
ኳን ፡ መቅደስ ፡ በሰማይ ፡ ተከፈተ ÷ ሰባቱንም ፡ ፮፤
መቅሠፍት ፡ የያዙ ፡ ሰባቱ ፡ መላእክት ፡ ከመቅ
ደሱ ፡ ወጡ ፤ ከተልባ ፡ እግርም ፡ የተሠራ ፡ ጥሩ ፡
የጌጥ ፡ ልብስ ፡ ለበሱ ፡ ደረታቸውንም ፡ በወርቅ ፡
መታጠቂያ ፡ ታጠቁ ። ከአራቱም ፡ እንስሶች ፡ ፯፤
አንዱ ፡ ከዘላለም ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ የሚ
ኖር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ የሞላባቸውን ፡
ሰባት ፡ የወርቅ ፡ ጽዋዎች ፡ ለሰባቱ ፡ መላእክት ፡
ሰጣቸው ። ከእግዚአብሔርም ፡ ክብርና ፡ ከኃ ፰፤
ይሉ ፡ ጢስ ፡ በመቅደሱ ፡ ሞላበት ÷ የሰባቱም ፡
መላእክት ፡ ሰባቱ ፡ መቅሠፍት ፡ እስኪፈጸሙ ፡
ድረስ ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ ወደ ፡ መቅደሱ ፡ ይገባ ፡
ዘንድ ፡ አልቻለም ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

ሰባቱም ፡ መላእክት ፡— ሂዱችሁ ፡ የእግዚ ፩፤
አብሔርን ፡ ቍጣ ፡ ጽዋዎች ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡
አፍስሱ ፡ የሚል ፡ ታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ከመቅደሱ ፡
ሰማሁ ።
ፊተኛውም ፡ ሄዶ ፡ ጽዋውን ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ፪፤
አፈሰሰ ፤ የአውሬውም ፡ ምልክት ፡ ባለባቸው ፡
ለምስሉም ፡ በሚሰግዱ ፡ ሰዎች ፡ ክፉኛ ፡ የሚን
ዘንዝ ፡ ቍስል ፡ ሆነባቸው ።

፲፬፤ ፰፤ ኢሳ. ፳፩ ÷ ፱ ፤ ኤር. ፶፩ ÷ ፯ ። ፱፤ ም. ፲፫ ÷ ፲፭ ፡ ፲፯ ። ፲፤ ኤር. ፳፭ ÷ ፲፭ ። ፲፩፤ ኢሳ. ፴፬ ÷ ፲ ። ፲፬፤ ም. ፩ ÷ ፲፫ ። ፲፭፤ ኢዩ. ፫ ÷ ፲፫ ፤ ማር. ፬ ÷ ፳፱ ። ፲፱ ፡ ፳፤ ኢሳ. ፷፫ ÷ ፫ ።
፲፭ ። ፫፤ ም. ፬ ÷ ፲፩ ፤ ዘፀአ. ፲፭ ÷ ፩ ፤ መዝ. ፻፵፩ ÷ ፲፯ ። ፬፤ መዝ. ፹፮ ÷ ፱ ፤ ፲ ፤ ኤር. ፲ ÷ ፯ ። ፭፤ ዘፀአ. ፴፰ ÷ ፳፩ ። ፰፤ ዘፀአ. ፵ ÷ ፴፬ ፤ ፩ኛ ነገሥ. ፰ ÷ ፲ ፡ ፲፩ ፤ ኢሳ. ፮ ÷ ፬ ።
፲፮ ። ፩፤ ኢሳ. ፷፮ ÷ ፮ ፤ መዝ. ፸፱ ÷ ፮ ። ፪፤ ዘፀአ. ፱ ÷ ፲ ።

፫፤ ሁለተኛውም፡ጽዋውን፡በባሕር፡ውስጥ፡
አፈሰሰ ፤ እንደ፡ሞተም፡ሰው፡ደም፡ሆነ ፥
በባሕርም፡ከሚኖሩት፡ሕይወት፡ያለበት፡ነፍስ፡
ሁሉ፡ሞተ ።
፬፤ ሦስተኛውም፡ጽዋውን፡በወንዞችና፡በውኃ፡
ምንጮች፡ውስጥ፡አፈሰሰ ፤ እነርሱም፡ደም፡
፭፤ ሆኑ ። የውኃውም፡መልአክ፡— ያለህና፡የነበ
ርህ፡ጌታ፡ሆይ ፥ ቅዱስ፡ሆይ ፥ እንዲህ፡ስለ፡
፮፤ ፈረድህ፡ጻድቅ፡ነህ ፤ የቅዱሳንንና፡የነቢያ
ትን፡ደም፡ስላፈሰሱ፡ደምን፡ደግሞ፡አጠጣ
ተሃቸዋል ፥ የሚገባቸው፡ነውና፡ብሎ፡ሲናገር፡
፯፤ ሰማሁ ። ከመሠዊያውም፡— አዎን ፤ ሁሉን፡
የምትገዛ፡ጌታ፡አምላክ፡ሆይ ፥ ፍርዶችህ፡
እውነትና፡ጽድቅ፡ናቸው፡ብሎ፡ሲናገር፡
ሰማሁ ።
፰፤ አራተኛውም፡ጽዋውን፡በፀሐይ፡ላይ፡አፈ
ሰሰ ፤ ሰዎችንም፡በእሳት፡ልታቃጥል፡ተሰ
፱፤ ጣት ። ሰዎችም፡በታላቅ፡ትኵሳት፡ተቃጠሉ ፥
በእነዚህም፡መቅሠፍቶች፡ላይ፡ሥልጣን፡ያለ
ውን፡የእግዚአብሔርን፡ስም፡ተሳደቡ ፥ ክብ
ርንም፡እንዲሰጡት፡ንስሐ፡አልገቡም ።
፲፤ አምስተኛውም፡ጽዋውን፡በአውሬው፡
ዙፋን፡ላይ፡አፈሰሰ ፤ መንግሥቱም፡ጨለማ፡
ሆነች፡ከሥቃይም፡የተነሣ፡መላሶቻቸውን፡
፲፩፤ ያኝኩ፡ነበር ፥ ከሥቃያቸውና፡ከቍስላቸውም፡
የተነሣ፡የሰማይን፡አምላክ፡ተሳደቡ ፥ ከሥራ
ቸውም፡ንስሐ፡አልገቡም ።
፲፪፤ ስድስተኛውም፡ጽዋውን፡በታላቁ፡ወንዝ፡
በኤፍራጥስ፡ላይ፡አፈሰሰ ፤ ከፀሐይም፡መውጫ፡
ለሚመጡ፡ነገሥታት፡መንገድ፡እንዲሰናዳላ
፲፫፤ ቸው፡ውኃው፡ደረቀ ። ከዘንዶውም፡አፍና፡
ከአውሬው፡አፍ፡ከሐሰተኛውም፡ነቢይ፡አፍ፡
ጓጕንቸሮች፡የሚመስሉ፡ሦስት፡ርኵሳን፡መና
፲፬፤ ፍስት፡ሲወጡ፡አየሁ ፤ ምልክት፡እያደረጉ፡
የአጋንንት፡መናፍስት፡ናቸውና ፥ በታላቁም፡
ሁሉን፡በሚገዛ፡በእግዚአብሔር፡ቀን፡ወደ
ሚሆነው፡ጦር፡እንዲያስከትቱአቸው፡ወደ፡
፲፭፤ ዓለም፡ሁሉ፡ነገሥታት፡ይወጣሉ ። እነሆ ፥
እንደ፡ሌባ፡ሆኜ፡እመጣለሁ ፤ ራቁቱን፡እንዳ
ይሄድ፡እፍረቱንም፡እንዳያዩ፡ነቅቶ፡ልብሱን፡
፲፮፤ የሚጠብቅ፡ብፁዕ፡ነው ። በዕብራይስጥም፡
አርማጌዶን፡ወደሚባል፡ስፍራ፡አስከተቱአ
ቸው ።
፲፯፤ ሰባተኛውም፡ጽዋውን፡በአየር፡ውስጥ፡
አፈሰሰ ፤ ከመቅደሱም፡ውስጥ፡— ተፈጸመ
አል፡የሚል፡ታላቅ፡ድምፅ፡ከዙፋኑ፡ወጣ ።
፲፰፤ መብረቅና፡ድምፅም፡ነጐድጓድም፡ሆኑ ፥ ትል
ቅም፡የምድር፡መናወጥ፡ሆነ ፤ ሰው፡በም
ድር፡ከተፈጠረ፡ጀምሮ፡እንዲህ፡ያለ፡ታላቅ፡
መናወጥ፡ከቶ፡አልነበረም ፤ ከሁሉ፡በለጠ ።
፲፱፤ ታላቂቱም፡ከተማ፡በሦስት፡ተከፋፈለች ፥ የአ
ሕዛብም፡ከተማዎች፡ወደቁ ። ታላቂቱም፡በቢ
ሎን፡የብርቱ፡ቍጣው፡ወይን፡ጠጅ፡የሞላ
በትን፡ጽዋ፡እንዲሰጣት፡በእግዚአብሔር፡
ፊት፡ታሰበች ። ደሴቶችም፡ሁሉ፡ሸሹ፡ተራ ፳፤
ራዎችም፡አልተገኙም ። በሚዘንም፡አንድ፡ ፳፩፤
ታላንት፡የሚያህል፡ታላቅ፡በረዶ፡በሰዎች፡
ላይ፡ከሰማይ፡ወረደባቸው ፤ ሰዎቹም፡ከበ
ረዶው፡መቅሠፍት፡የተነሣ፡እግዚአብሔርን፡
ተሳደቡ ፥ መቅሠፍቱ፡እጅግ፡ታላቅ፡ነውና ።

፳፩፤ አንድ፡ታላንት፡ሦስት፡ፈረሱላ፡የሚያህል፡ነው ።

## ምዕራፍ፡፲፯ ።

ሰባቱንም፡ጽዋዎች፡ከያዙ፡ከሰባቱ፡መላእ ፩፤
ክት፡አንዱ፡መጥቶ፡— ና፡በብዙም፡ውኃዎች፡
ላይ፡የተቀመጠችውን፡የታላቂቱን፡ጋለሞታ፡
ፍርድ፡አሳይሃለሁ ፤ የምድርም፡ነገሥታት፡ ፪፤
ከእርስዋ፡ጋር፡ሴሰኑ፡በምድርም፡የሚኖሩ፡
ከዝሙትዋ፡ወይን፡ጠጅ፡ሰከሩ፡ብሎ፡ተና
ገረኝ ። በመንፈስም፡ወደ፡በረሀ፡ወሰደኝ ፤ ፫፤
የስድብም፡ስሞች፡በሞሉበት ፥ ሰባት፡ራስ
ችና፡አሥር፡ቀንዶችም፡ባሉበት፡በቀይ፡
አውሬ፡ላይ፡አንዲት፡ሴት፡ተቀምጣ፡አየሁ ።
ሴቲቱም፡በቀይና፡በሐምራዊ፡ልብስ፡ተጐ ፬፤
ናጽፋ፡በወርቅና፡በከበሩ፡ድንጋዮች፡በዕን
ቍችም፡ተሸልማ፡ነበር ፥ በእጅዋም፡የሚያስ
ጸይፍ፡ነገር፡የዝሙትዋም፡ርኵሰት፡የሞላ
በትን፡የወርቅ፡ጽዋ፡ያዘች ፤ በግምባርዋም፡ ፭፤
ምሥጢር፡የሆነ፡ስም፡— ታላቂቱ፡ባቢሎን ፤
የጋለሞታዎችና፡የምድር፡ርኵሰት፡እናት፡
ተብሎ፡ተጻፈ ። ሴቲቱም፡በቅዱሳን፡ደምና፡ ፮፤
በኢየሱስ፡ምስክሮች፡ደም፡ሰክራ፡አየኋት ።
ባየኋትም፡ጊዜ፡እጅግ፡ታላቅ፡ድንቅ፡
አደነቅሁ ። መልአኩም፡አለኝ፡— የምትደ ፯፤
ነቅ፡ስለ፡ምንድር፡ነው ? የሴቲቱን፡ምሥ
ጢርና፡የሚሸከማትን ፥ ሰባት፡ራሶችና፡አሥር፡
ቀንዶች፡ያሉትን፡የአውሬውን፡ምሥጢር፡
እኔ፡እነግርሃለሁ ። ያየኸው፡አውሬ፡አስቀ ፰፤
ድሞ፡ነበረ ፥ አሁንም፡የለም ፥ ከጥልቁም፡
ይወጣ፡ዘንድ፡አለው ፥ ወደ፡ጥፋትም፡ይሄ
ዳል ፤ ስሞቻቸውም፡ከዓለም፡ፍጥረት፡ጀምሮ፡
በሕይወት፡መጽሐፍ፡ያልተጻፉ፡በምድር፡
የሚኖሩ፡አውሬው፡አስቀድሞ፡እንደ፡ነበረ፡
አሁንም፡እንደሌለ ፥ ነገር፡ግን፡እንዳለ፡ሲያዩ፡
ያደንቃሉ ። ጥበብ፡ያለው፡አእምሮ፡በዚህ፡ ፱፤
ነው ። ሰባቱ፡ራሶች፡ሴቲቱ፡የተቀመጠችባ
ቸው፡ሰባት፡ተራራዎች፡ናቸው ፤ ሰባት፡ ፲፤
ነገሥታት፡ደግሞ፡ናቸው ፤ አምስቱ፡ወድቀ
ዋል፡አንዱም፡አለ ፥ የቀረውም፡ገና፡አል
መጣም ፤ ሲመጣም ፥ ጥቂት፡ጊዜ፡ሊቆይ፡
ይገባዋል ። የነበረውና፡የሌለውም፡አውሬ፡ ፲፩፤
ራሱ፡ደግሞ፡ስምንተኛው፡ነው፡ከሰባቱም፡

፲፮ ። ፫፡፬፤ ምዕ. ፰ ÷ ፰—፲ ። ፭፤ ኢሳ. ፵፱ ÷ ፳፮ ። ፯፤ መዝ. ፻፲፰ ÷ ፻፴፯ ። ፲፤ ዘፀአ. ፲ ÷ ፳፩ ። ፲፪፤ ኢሳ. ፲፩ ÷ ፲፭ ።
፲፬፤ ፩ ነገሥ. ፳፪ ÷ ፳—፳፪ ። ፲፭፤ ምዕ. ፫ ÷ ፫ ። ፲፮፤ መሳ. ፭ ÷ ፲፱ ። ፲፰፤ ምዕ. ፱ ÷ ፭ ። ፳፩፤ ዘፀአ. ፱ ÷ ፳፫—፳፭ ።
፲፯ ። ፩፤ ኤር. ፶፩ ÷ ፲፫ ። ፪፤ ምዕ. ፲፬ ÷ ፰፤ ኢሳ. ፳፫ ÷ ፲፯ ። ፫፤ ምዕ. ፲፫ ÷ ፩ ። ፬፤ ኤር. ፶፩ ÷ ፯ ። ፰፤ ምዕ. ፲ ÷ ፩ ።

፲፪ አንዱ ፡ ነው ፥ ወደ ፡ ጥፋትም ፡ ይሄዳል ። ያየ
ሃቸውም ፡ አሥሩ ፡ ቀንዶች ፡ ገና ፡ መንግሥትን ፡
ያልተቀበሉ ፡ አሥር ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ፥ ዳሩ ፡
ግን ፡ ከአውሬው ፡ ጋር ፡ ለአንድ ፡ ሰዓት ፡ እንደ ፡
፲፫ ነገሥታት ፡ ሥልጣንን ፡ ይቀበላሉ ። እነዚህ ፡
አንድ ፡ አሳብ ፡ አላቸው ፥ ኃይላቸውንና ፡ ሥል
፲፬ ጣናቸውንም ፡ ለአውሬው ፡ ይሰጣሉ ። እነዚህ ፡
በጉን ፡ ይወጋሉ ፤ በጉም ፡ የጌቶች ፡ ጌታና ፡
የነገሥታት ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እነርሱን ፡ ድል ፡
ይነሣል ፥ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ያሉ ፡ የተጠሩና ፡
የተመረጡ ፡ የታመኑም ፡ ደግሞ ፡ ድል ፡ ይነ
ሣሉ ።
፲፭ አለኝም ፡— ጋለሞታይቱ ፡ የተቀመጠችባ
ቸው ፡ ያየሃቸው ፡ ውኆዎች ፥ ወገኖችና ፡ ብዙ ፡
፲፮ ሰዎች ፡ አሕዛብም ፡ ቋንቋዎችም ፡ ናቸው ። ያየሃ
ቸውም ፡ አሥር ፡ ቀንዶችና ፡ አውሬው ፡ ጋለሞ
ታይቱን ፡ ይጣላሉ ፤ ባዶዋንና ፡ ራቁትዋንም ፡
ያደርጓታል ፥ ሥጋዋንም ፡ ይበላሉ ፥ በእሳትም ፡
፲፯ ያቃጥሉአታል ። እግዚአብሔር ፡ አሳቡን ፡ እን
ዲያደርጉ ፡ አንድንም ፡ አሳብ ፡ እንዲያደርጉ ፡
የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡
መንግሥታቸውን ፡ ለአውሬው ፡ እንዲሰጡ ፡
፲፰ በልባቸው ፡ አግብቶአልና ። ያየሃትም ፡ ሴት ፡
በምድር ፡ ነገሥታት ፡ ላይ ፡ የምትነግሥ ፡ ታላ
ቂቱ ፡ ከተማ ፡ ናት ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

፩ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ታላቅ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡
መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ ሲወርድ ፡ አየሁ ፥ ከክብ
፪ ሩም ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ በራች ። በብርቱም ፡
ድምፅ ፡— ታላቂቱ ፡ ባቢሎን ፡ ወደቀች ፥ ወደ
ቀች ፥ የአጋንንትም ፡ ማደሪያ ፡ ሆነች ፥ የርኵሰ
ንም ፡ መናፍስት ፡ ሁሉ ፡ መጠጊያ ፡ የርኵሳንና ፡
የተጠሉም ፡ ወፎች ፡ ሁሉ ፡ መጠጊያ ፡ ሆነች ፤
፫ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ከዝሙትዋ ፡ ቍጣ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡
የተነሣ ፡ ወድቀዋልና ፥ የምድርም ፡ ነገሥታት ፡
ከእርስዋ ፡ ጋር ፡ ሴሰኑ ፡ የምድርም ፡ ነጋዴዎች ፡
ከቅምጥልነትዋ ፡ ኃይል ፡ የተነሣ ፡ ባለ ፡ ጠጎች ፡
፬ ሆኑ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ። ከሰማይም ፡ ሌላ ፡ ድምፅ ፡
ሰማሁ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡— ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ በኃ
ጢአትዋ ፡ እንዳትተባበሩ ፡ ከመቅሠፍትዋም ፡
፭ እንዳትቀበሉ ፡ ከእርስዋ ፡ ዘንድ ፡ ውጡ ፤ ኃጢ
አትዋ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ድረስ ፡ ደርሶአልና ፥ እግ
፮ ዚአብሔርም ፡ ዓመፃዋን ፡ አሰበ ። እርስዋ ፡
እንደ ፡ ሰጠች ፡ መጠን ፡ ብድራት ፡ መልሱላት ፥
እንደ ፡ ሥራዋም ፡ ሁለት ፡ እጥፍ ፡ ደርቡባት ፤
በቀላቀለችው ፡ ጽዋ ፡ ሁለት ፡ እጥፍ ፡ አድርጋ
፯ ችሁ ፡ ቀላቅሉባት ፤ ራስዋን ፡ እንደ ፡ አከበረ
ችና ፡ እንደ ፡ ተቀማጠለች ፡ ልክ ፡ ሥቃይና ፡
ኀዘን ፡ ስጡአት ። በልብዋ ፡— ንግሥት ፡ ሆኜ ፡
እቀመጣለሁ ፡ በልቴትም ፡ አልሆንም ፡ ኀዘን
ንም ፡ ከቶ ፡ አላይም ፡ ስላለች ፥ ስለዚህ ፡ በአ ፰
ንድ ፡ ቀን ፡ ሞትና ፡ ኀዘን ፡ ራብም ፡ የሆኑ ፡ መቅ
ሠፍቶችዋ ፡ ይመጣሉ ፥ በእሳትም ፡ ትቃጠላ
ለች ፤ የሚፈርድባት ፡ እግዚአብሔር ፡ ብርቱ ፡
ነውና ።
ከእርስዋም ፡ ጋር ፡ የሴሰኑና ፡ የተቀማጠሉ ፡ ፱
የምድር ፡ ነገሥታት ፡ የመቃጠልዋን ፡ ጢስ ፡
ሲያዩ ፡ ስለ ፡ እርስዋ ፡ ዋይ ፡ ዋይ ፡ እያሉ ፡ ያለ
ቅሳሉ ፤ ሥቃይዋንም ፡ ከመፍራት ፡ የተነሣ ፡ ፲
በሩቅ ፡ ቆመው ፡— እንቺ ፡ ታላቂቱ ፡ ከተማ ፥
ብርቱይቱ ፡ ከተማ ፡ ባቢሎን ፥ ወዮልሽ ፥ ወዮ
ልሽ ፥ በአንድ ፡ ሰዓት ፡ ፍርድሽ ፡ ደርሶአልና ፡
እያሉ ፡ ይናገራሉ ።
የመርከባቸውንም ፡ ጭነት ፡ ከእንግዲህ ፡ ፲፩
ወዲህ ፡ የሚገዛ ፡ የለምና ፡ የምድር ፡ ነጋዴዎች ፡
ያለቅሱላታል ፡ ያዝኑላትማል ፤ ጭነትም ፡ ወር ፲፪
ቅና ፡ ብር ፡ የከበረም ፡ ድንጋይ ፡ ዕንቍም ፥
ቀጭንም ፡ ተልባ ፡ እግር ፡ ቀይም ፡ ሐርም ፡ ሐም
ራዊም ፡ ልብስ ፡ የሚሸትም ፡ እንጨት ፡ ሁሉ ፥
ከዝሆን ፡ ጥርስም ፡ የተሠራ ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፥ እጅ
ግም ፡ ከከበረ ፡ እንጨት ፡ ከናስም ፡ ከብረትም ፡ ከዕ
ብነ ፡ በረድም ፡ የተሠራ ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፥ ቀረፋም ፡ ፲፫
ቅመምም ፡ የሚቃጠልም ፡ ሽቱ ፡ ቅባትም ፡ ዕጣ
ንም ፡ የወይን ፡ ጠጅም ፡ ዘይትም ፡ የተሰለቀ ፡
ዱቄትም ፡ ስንዴም ፡ ከብትም ፡ በግም ፡ ፈረስም ፡
ሰረገላም ፡ ባሪያዎችም ፡ የሰዎችም ፡ ነፍሳት ፡
ነው ። ነፍስሽም ፡ የጐመጀችው ፡ ፍሬ ፡ ከእ ፲፬
ንቺ ፡ ዘንድ ፡ አልፎአል ፥ የሚቀማጠልና ፡ የሚ
ያጌጥም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጠፍቶብሻል ፥ ሰዎችም ፡
ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከቶ ፡ አያገኙአቸውም ።
እነዚህን ፡ የነገዱ ፡ በእርስዋም ፡ ባለ ፡ ጠጎች ፡ ፲፭
የሆኑት ፡ እያለቀሱና ፡ እያዘኑ ፡— በቀጭን ፡ ፲፮
ተልባ ፡ እግርና ፡ በቀይ ፡ ሐምራዊም ፡ ልብስ ፡
ለተጐናጸፈች ፡ በወርቅና ፡ በከበረ ፡ ድንጋይም ፡
በዕንቍም ፡ ለተሸለመች ፡ ለታላቂቱ ፡ ከተማ ፡
ወዮላት ፥ ወዮላት ፥ ይህን ፡ የሚያህል ፡ ታላቅ ፡
ባለ ፡ ጠግነት ፤ በአንድ ፡ ሰዓት ፡ ጠፍቶአልና ፡
እያሉ ፡ ሥቃይዋን ፡ ከመፍራት ፡ የተነሣ ፡ በሩቅ ፡
ይቆማሉ ። የመርከብም ፡ መሪ ፡ ሁሉ ፡ በመር
ከብም ፡ ወደ ፡ ማናቸውም ፡ ስፍራ ፡ የሚሄድ ፡
ሁሉ ፡ መርከበኞችም ፡ ከባሕርም ፡ የሚጠቀሙ ፡
ሁሉ ፡ በሩቅ ፡ ቆሙ ፥ የመቃጠልዋንም ፡ ጢስ ፡ ፲፰
በዩ ፡ ጊዜ ፡— ታላቂቱን ፡ ከተማ ፡ የምትመስላት ፡
ምን ፡ ከተማ ፡ ነበረች ? እያሉ ፡ ጮኹ ። በራሳ ፲፱
ቸውም ፡ ላይ ፡ ትቢያ ፡ ነስንሰው ፡ እያለቀሱና ፡
እያዘኑ ፡— በባሕር ፡ መርከቦች ፡ ያሉአቸውን ፡
ሁሉ ፡ ከባለ ፡ ጠግነትዋ ፡ የተነሣ ፡ ባለ ፡ ጠጎች ፡
ላደረገች ፡ ለታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ ወዮላት ፥ ወዮ
ላት ፥ በአንድ ፡ ሰዓት ፡ ጠፍታለችና ፡ እያሉ ፡

፲፯ ። ፲፪ ፡ ዳን. ፯ ፥ ፳፬ ። ፲፬ ፡ ዘዳግ. ፲ ፥ ፲፯ ። ፲፭ ፡ ኢሳ. ፰ ፥ ፯ ።
፲፰ ። ፪ ፡ ሕዝ. ፵፫ ፥ ፪ ። ፪ ፡ ምዕ. ፲፬ ፥ ፰ ፤ ኢሳ. ፲፫ ፥ ፳፩ ። ፫ ፡ ምዕ. ፲፬ ፥ ፰ ፤ ሕዝ. ፳፯ ፥ ፴፫ ። ፬ ፡ ኢሳ. ፵፰ ፥ ፳ ፤ ፪ ቆሮ.
፮ ፥ ፲፯ ። ፭ ፡ ኤር. ፶፩ ፥ ፱ ። ፮ ፡ መዝ. ፻፴፯ ፥ ፰ ፤ ኤር. ፶ ፥ ፳፱ ። ፯ ፡ ኢሳ. ፵፯ ፥ ፯ ፡ ፰ ። ፱ ፡ ሕዝ. ፳፮ ፥ ፲፮ ።
፲፩—፲፱ ፡ ሕዝ. ፳፯ ፥ ፳፯—፴፮ ።

፳ ጮኹ ። ሰማይ ፡ ሆይ ፥ ቅዱሳን ፡ ሐዋርያት ፡
ነቢያትም ፡ ሆይ ፥ በእርስዋ ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ ይበላ
ችሁ ፥ እግዚአብሔር ፡ ፈርዶላችኋልና ።
፳፩ አንድም ፡ ብርቱ ፡ መልአክ ፡ ትልቅን ፡ ወፍጮ ፡
የሚመስልን ፡ ድንጋይ ፡ አንሥቶ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡
ወረወረው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡— ታላቂቱ ፡ ከተማ ፡
ባቢሎን ፡ እንዲህ ፡ ተገፍታ ፡ ትወድቃለች ፡ ከእ
፳፪ ንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ከቶ ፡ አትገኝም ። በገና ፡
የሚመቱና ፡ የሚዘምሩም ፡ ድምፅ ፡ እምቢልታ
ንና ፡ መለከትንም ፡ የሚነፉ ፡ ድምፅ ፡ ከእንግዲህ ፡
ወዲህ ፡ በአንቺ ፡ ውስጥ ፡ ከቶ ፡ አይሰማም ፥
የእጅ ፡ ጥበብም ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ብልሃተኛ ፡
እንኳ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በአንቺ ፡ ውስጥ ፡
ከቶ ፡ አይገኝም ፥ የወፍጮ ፡ ድምፅም ፡ ከእንግ
ዲህ ፡ ወዲህ ፡ በአንቺ ፡ ውስጥ ፡ ከቶ ፡ አይሰማም ፥
፳፫ የመብራትም ፡ ብርሃን ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡
በአንቺ ፡ ውስጥ ፡ ከቶ ፡ አይበራም ፥ የሙሽራና ፡
የሙሽራይቱም ፡ ድምፅ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡
በአንቺ ፡ ውስጥ ፡ ከቶ ፡ አይሰማም ፤ ነጋዴዎ
ችሽ ፡ የምድር ፡ መኳንንት ፡ ነበሩና ፥ በአስማት
፳፬ ሽም ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ስተዋልና ። በእርስ
ዋም ፡ ውስጥ ፡ የነቢያትና ፡ የቅዱሳን ፡ ደም ፡
በምድርም ፡ የታረዱ ፡ ሁሉ ፡ ደም ፡ ተገኘበት ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

፩ ፡ ፪ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሰማይ ፡—
ሃሌ ፡ ሉያ ፤ በዝሙትዋ ፡ ምድርን ፡ ያጠፋ
ችይቱን ፡ ታላቂቱን ፡ ጋለሞታ ፡ ስለ ፡ ፈረደ
ባት ፥ የባሪያዎቹንም ፡ ደም ፡ ከእጅዋ ፡ ስለ ፡
ተበቀለ ፥ ፍርዶቹ ፡ እውነትና ፡ ጽድቅ ፡
ናቸውና ፡ ማዳንና ፡ ክብር ፡ ኃይልም ፡ የእ
ምላካችን ፡ ነው ፡
ብሎ ፡ ሲናገር ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ታላቅ ፡
፫ ድምፅ ፡ ያለ ፡ ድምፅን ፡ ሰማሁ ። ደግመውም ፡—
ሃሌ ፡ ሉያ ፡ አሉ ፤ ጢስዋም ፡ ለዘላለም ፡ እስከ ፡
፬ ዘላለም ፡ ይወጣል ። ሀያ ፡ አራቱም ፡ ሽማግሌ
ዎችና ፡ አራቱ ፡ እንስሶች ፡ በፊታቸው ፡ ተደፍ
ተው ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ለተቀመጠው ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡— አሜን ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ እያሉ ፡ ሰገዱ
፭ ለት ። ድምፅም ፡—
በሪያዎቹ ፡ ሁሉ ፡ እርሱንም ፡ የምትፈሩት ፡
ታናናሾችና ፡ ታላላቆች ፡ ሆይ ፥ አምላካች
ንን ፡ አመስግኑ ፡
፮ ሲል ፡ ከዙፋኑ ፡ ወጣ ። እንደ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብም ፡
ድምፅ ፥ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውኆዎችም ፡ ድምፅ ፥
እንደ ፡ ብርቱም ፡ ነጐድጓድ ፡ ድምፅ ፡ ያለ ፡
ድምፅ ፡ ሰማሁ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡—
ሃሌ ፡ ሉያ ፤ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ ጌታ ፡ አም
፯ ላካችን ፡ ነግሦአልና ። የበጉ ፡ ሰርግ ፡ ስለ ፡
ደረሰ ፡ ሚስቱም ፡ ራስዋን ፡ ስላዘጋጀች ፡
ደስ ፡ ይበለን ፡ ሐሤትም ፡ እናድርግ ፡ ክብ
ርንም ፡ ለእርሱ ፡ እናቅርብ ። ያጌጠና ፡ ፰
የተጣራ ፡ ቀጭን ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ ልብስ ፡
እንድትጐናጸፍ ፡ ተሰጥቶአታል ። ቀጭኑ ፡
የተልባ ፡ እግር ፡ የቅዱሳን ፡ ጽድቅ ፡ ሥራ ፡
ነውና ።
እርሱም ፡— ወደ ፡ በጉ ፡ ሰርግ ፡ እራት ፡ የተ ፱
ጠሩ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፡ አለኝ ።
ደግሞም ፡— ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እውነተኛ ፡
ቃል ፡ ነው ፡ አለኝ ። ልሰግድለትም ፡ በእግሩ ፡ ፲
ፊት ፡ ተደፋሁ ። እርሱም ፡— እንዳታደርገው ፡
ተጠንቀቅ ፤ ከአንተ ፡ ጋር ፡ የኢየሱስም ፡ ምስ
ክር ፡ ካላቸው ፡ ከወንድሞችህ ፡ ጋር ፡ አብሬ ፡
ባሪያ ፡ ነኝ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ስገድ ፤ የኢየ
ሱስ ፡ ምስክር ፡ የትንቢት ፡ መንፈስ ፡ ነውና ፡
አለኝ ።
ሰማይም ፡ ተከፍቶ ፡ አየሁ ፥ እነሆም ፡ አምባ ፲፩
ላይ ፡ ፈረስ ፥ የተቀመጠበትም ፡ የታመነና ፡ እው
ነተኛ ፡ ይባላል ፥ በጽድቅም ፡ ይፈርዳል ፡ ይዋ
ጋልም ። ዓይኖቹም ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ነበልባል ፡ ፲፪
ናቸው ፥ በራሱ ፡ ላይም ፡ ብዙ ፡ ዘውዶች ፡ አሉ ፥
ከእርሱም ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ የማያውቀው ፡
የተጻፈ ፡ ስም ፡ አለው ፤ በደምም ፡ የተረጨ ፡ ፲፫
ልብስ ፡ ተጐናጽፎአል ፥ ስሙም ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ ቃል ፡ ተብሎአል ። በሰማይም ፡ ያሉት ፡ ፲፬
ጭፍራዎች ፡ ነጭና ፡ ጥሩ ፡ ቀጭን ፡ የተልባ ፡
እግር ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ በአምባላዮች ፡ ፈረሶች ፡
ተቀምጠው ፡ ይከተሉት ፡ ነበር ። አሕዛብንም ፡ ፲፭
ይመታበት ፡ ዘንድ ፡ ስለታም ፡ ሰይፍ ፡ ከአፉ ፡
ይወጣል ፤ እርሱም ፡ በብረት ፡ በትር ፡ ይገዛቸ
ዋል ፤ እርሱም ፡ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ የእግዚአብ
ሔርን ፡ የብርቱ ፡ ቍጣውን ፡ ወይን ፡ መጥመ
ቂያ ፡ ይረግጣል ። በልብሱና ፡ በጭኑም ፡ የተ ፲፮
ጻፈበት ፡— የነገሥታት ፡ ንጉሥና ፡ የጌታዎች ፡
ጌታ ፡ የሚል ፡ ስም ፡ አለው ።
እንድም ፡ መልአክ ፡ በፀሐይ ፡ ውስጥ ፡ ቆሞ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰
አየሁ ፥ በሰማይም ፡ መካከል ፡ ለሚበሩ ፡ ወፎች ፡
ሁሉ ፡— መጥታችሁ ፡ የነገሥታትን ፡ ሥጋና ፡ የሻ
ለቃዎችን ፡ ሥጋ ፡ የብርቱዎችንም ፡ ሥጋ ፡ የፈ
ረሶችንም ፡ በእነርሱም ፡ የተቀመጡትን ፡ ሥጋ ፡
የጌታዎችንና ፡ የባሪያዎችንም ፡ የታናናሾችንና ፡
የታላላቆችንም ፡ ሁሉ ፡ ሥጋ ፡ እንድትበሉ ፡
ወደ ፡ ታላቁ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እራት ፡ ተከ
ማቹ ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ። በፈረ ፲፱
ሱም ፡ የተቀመጠውን ፡ ጭፍራዎቹንም ፡ ይወጉ ፡
ዘንድ ፡ አውሬውና ፡ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ ጭፍ
ራዎቻቸውም ፡ ተከማችተው ፡ አየሁ ። አውሬ ፳
ውም ፡ ተያዘ ፡ በእርሱም ፡ ፊት ፡ ተአምራትን ፡

፲፰ ። ፳ ፡ ኤር ፶፩ ፥ ፵፰ ። ፳፩ ፡ ኤር ፶፩ ፥ ፷፫ ፡ ፷፬ ። ፳፪ ፡ ኢሳ ፳፬ ፥ ፰ ፡ ኤር ፳፭ ፥ ፲ ። ፳፫ ፡ ኤር ፳፭ ፥ ፲ ፡ ኢሳ ፳፫ ፥ ፰ ። ፳፬ ፡ ማቴ ፳፫ ፥ ፴፭ ፡ ፴፯ ።

፲፱ ። ፩ ፡ መዝ ፻፬ ፥ ፴፭ ። ፪ ፡ ዘዳግ ፴፪ ፥ ፵፫ ። ፫ ፡ ም ፲፬ ፥ ፲፩ ። ፭ ፡ መዝ ፻፲፭ ፥ ፲፫ ፡ ፻፴፭ ፥ ፳፩ ። ፮ ፡ መዝ ፺፯ ፥ ፩ ። ፯ ፡ መዝ ፻፲፰ ፥ ፳፬ ። ፲፩ ፡ ኢሳ ፲፩ ፥ ፬ ። ፲፪ ፡ ዳን ፲ ፥ ፮ ። ፲፫ ፡ ኢሳ ፷፫ ፥ ፩ ፡ ፫ ፡ ዮሐ ፩ ፥ ፩ ። ፲፭ ፡ መዝ ፪ ፥ ፱ ። ፲፮ ፡ ም ፲፯ ፥ ፲፬ ። ፲፯ ፡ ፲፰ ፡ ሕዝ ፴፱ ፥ ፲፯—፳ ። ፳ ፡ ዳን ፯ ፥ ፲፩ ።

እያደረገ ፡ የአውሬውን ፡ ምልክት ፡ የተቀበሉ
ትን ፡ ስምስሉም ፡ የሰገዱትን ፡ ያሳተ ፡ ሐሰተ
ኛው ፡ ነቢይ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ተያዘ ፤ ሁለቱም ፡
በሕይወት ፡ ሳሉ ፡ በዲን ፡ ወደሚቃጠል ፡ ወደ ፡
፳፩፡ እሳት ፡ ባሕር ፡ ተጣሉ ። የቀሩትም ፡ በፈረስ ፡
ላይ ፡ ከተቀመጠው ፡ ከአፉ ፡ በሚወጣው ፡ ሰይፍ ፡
ተገደሉ ፤ ወፎችም ፡ ሁሉ ፡ ከሥጋቸው ፡ ጠገቡ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳ ።

፩፡ የጥልቁንም ፡ መክፈቻና ፡ ታላቁን ፡ ሰንሰለት ፡
በእጁ ፡ የያዘ ፡ መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ ሲወርድ ፡
፪፡ አየሁ ። የቀደመውንም ፡ እባብ ፡ ዘንዶውን ፡
እርሱም ፡ ዲያብሎስና ፡ ሰይጣን ፡ የተባለውን ፡
፫፡ ያዘው ÷ ሺህ ፡ ዓመትም ፡ አሰረው ÷ ወደ ፡ ጥል
ቅም ፡ ጣለው ፡ አሕዛብንም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንዳ
ያስት ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ በእ
ርሱ ፡ ላይ ፡ ዘግቶ ፡ ማኅተም ፡ አደረገበት ፤ ከዚ
ያም ፡ በኋላ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ይፈታ ፡ ዘንድ ፡
ይገባዋል ።
፬፡ ዙፋኖችንም ፡ አየሁ ÷ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ ለተ
ቀመጡት ፡ ዳኝነት ፡ ተሰጣቸው ፤ ስለ ፡ ኢየሱ
ስም ፡ ምስክርና ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
ራሶቻቸው ፡ የተቈረጡባቸውን ፡ ሰዎች ፡ ነፍ
ሳት ÷ ለአውሬውና ፡ ለምስሉም ፡ ያልሰገዱትን ፡
ምልክቱንም ፡ በግምባራቸው ፡ በእጆቻቸውም ፡
ላይ ፡ ያልተቀበሉትን ፡ አየሁ ፤ ከክርስቶስም ፡
፭፡ ጋር ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ኖሩና ፡ ነገሡ ። የቀሩቱ ፡
ሙታን ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ እስኪፈ
ጸም ፡ ድረስ ፡ በሕይወት ፡ አልኖሩም ። ይህ ፡
፮፡ የፊተኛው ፡ ትንሣኤ ፡ ነው ። በፊተኛው ፡ ትን
ሣኤ ፡ ዕድል ፡ ያለው ፡ ብፁዕና ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፤
ሁለተኛው ፡ ሞት ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡
የለውም ÷ ዳሩ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርና ፡ የክር
ስቶስ ፡ ካህናት ፡ ይሆናሉ ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡
ይህን ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ይነግሣሉ ።
፯፡ ሺሁም ፡ ዓመት ፡ ሲፈጸም ፡ ሰይጣን ፡ ከእስ
፰፡ ራቱ ፡ ይፈታል ÷ በአራቱም ፡ በምድር ፡ ማዕ
ዘን ፡ ያሉትን ፡ አሕዛብ ፡ ጎግንና ፡ ማጎግን ÷ እን
ዲያስታቸው ፡ ለሰልፍም ፡ እንዲያስከትታቸው ፡
ይወጣል ፤ ቍጥራቸውም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡
፱፡ የሚያህል ፡ ነው ። ወደ ፡ ምድርም ፡ ስፋት ፡
ወጡ ፡ የቅዱሳንንም ፡ ሰፈርና ፡ የተወደደችውን ፡
ከተማ ፡ ከበቡ ፤ እሳትም ፡ ከሰማይ ፡ ከእግዚአ
፲፡ ብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወርዳ ፡ በላቻቸው ። ያሳታቸ
ውም ፡ ዲያብሎስ ፡ አውሬውና ፡ ሐሰተኛው ፡
ነቢይ ፡ ወዳሉበት ፡ ወደ ፡ እሳቱና ፡ ወደ ፡ ዲኑ ፡
ባሕር ፡ ተጣለ ÷ ለዘላለምም ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡
ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ይሣቀያሉ ።

ታላቅና ፡ ነጭ ፡ ዙፋንን ፡ በእርሱም ፡ ላይ ፡ ፲፩፡
የተቀመጠውን ፡ አየሁ ÷ ምድርና ፡ ሰማይም ፡
ከፊቱ ፡ ሸሹ ፡ ለፍራም ፡ አልተገኘላቸውም ።
ሙታንንም ፡ ታናናሾችንና ፡ ታላላቆችን ፡ በዙ ፲፪፡
ፋኑ ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ አየሁ ÷ መጻሕፍትም ፡ ተከ
ፈቱ ፤ ሌላ ፡ መጽሐፍም ፡ ተከፈተ ፡ እርሱም ፡
የሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፤ ሙታንም ፡ በመ
ጻሕፍት ፡ ተጽፎ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንደ ፡ ሥራ
ቸው ፡ መጠን ፡ ተከፈሉ ። ባሕርም ፡ በእርሱ ፡ ፲፫፡
ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ሙታን ፡ ሰጠ ÷ ሞትና ፡ ሲኦ
ልም ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ያሉትን ፡ ሙታን ፡
ሰጡ ÷ እያንዳንዱም ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ መጠን ፡
ተከፈለ ። ሞትና ፡ ሲኦልም ፡ በእሳት ፡ ባሕር ፡ ፲፬፡
ውስጥ ፡ ተጣሉ ። ይህም ፡ የእሳት ፡ ባሕር ፡ ሁለ
ተኛው ፡ ሞት ፡ ነው ። በሕይወትም ፡ መጽ ፲፭፡
ሐፍ ፡ ተጽፎ ፡ ያልተገኘው ፡ ማንኛውም ፡ በእ
ሳት ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ተጣለ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

አዲስ ፡ ሰማይንና ፡ አዲስ ፡ ምድርንም ፡ አየሁ ÷ ፩፡
ፊተኛው ፡ ሰማይና ፡ ፊተኛይቱ ፡ ምድር ፡ አል
ፈዋልና ÷ ባሕርም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የለም ። ቅድ ፪፡
ስቲቱም ፡ ከተማ ፡ አዲሲቱ ፡ ኢየሩሳሌም ÷ ለባ
ልዋ ፡ እንደ ፡ ተሸለመች ፡ ሙሽራ ፡ ተዘጋጅታ ÷
ከሰማይ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ስትወርድ ፡
አየሁ ። ታላቅም ፡ ድምፅ ፡ ከሰማይ ፦ እነሆ ÷ ፫፡
የእግዚአብሔር ፡ ድንኳን ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡
ነው ፡ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ ያድራል ÷ እነርሱም ፡
ሕዝቡ ፡ ይሆናሉ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እርሱ ፡
ራሱ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ አምላካቸው ፡ ይሆ
ናል ፤ እንባዎችንም ፡ ሁሉ ፡ ከዓይኖቻቸው ፡ ያብ ፬፡
ሳል ÷ ሞትም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይሆንም ÷
ኀዘንም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ጩኸት ፡ ወይም ፡
ሥቃይ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይሆንም ÷ የቀ
ደመው ፡ ሥርዓት ፡ አልፎአልና ፡ ብሎ ፡ ሲና
ገር ፡ ሰማሁ ።
በዙፋንም ፡ የተቀመጠው ፦ እነሆ ÷ ሁሉን ፡ ፭፡
አዲስ ፡ አደርጋለሁ ፡ አለ ። ለእኔም ፦ እነዚህ ፡
ቃሎች ፡ የታመኑና ፡ እውነተኛዎች ፡ ናቸውና ፡
ጻፍ ፡ አለኝ ። አለኝም ፦ ተፈጽሞአል ። አል ፮፡
ፋና ፡ ዖሜጋ ÷ መጀመሪያውና ፡ መጨረሻው ፡
እኔ ፡ ነኝ ። ለተጠማ ፡ ከሕይወት ፡ ውኃ ፡ ምንጭ ፡
እንዲያው ፡ እኔ ፡ እሰጣለሁ ። ድል ፡ የሚነሣ ፡ ፯፡
ይህን ፡ ይወርሳል ፡ አምላክም ፡ እሆንለታለሁ ፡ እር
ሱም ፡ ልጅ ፡ ይሆነኛል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የሚፈ ፰፡
ሩና ፡ የማያምኑ ፡ የርኩሳንም ፡ የነፍሰ ፡ ገዳዮ
ችም ፡ የሴሰኞችም ፡ የአስማተኞችም ፡ ጣዖ
ትንም ፡ የሚያመልኩ ፡ የሐሰተኞችም ፡ ሁሉ ፡

፳። ፪፡ ይሁዳ ፮። ፫፡ ፪ ተሰ. ፪÷፱ ፡ ፲። ፬፡ ዳን. ፯÷፱ ፡ ፳፪ ፡ ፳፯። ፮፡ ምዕ. ፳፩÷፰ ፡ ኢሳ. ፳፭÷፰። ፰፡ ሕዝ.
፴፰÷፪ ፡ ፲፭። ፱፡ ሕዝ. ፴፰÷፱ ፡ ፩ ነገሥ. ፲፰÷፴፰። ፲፩፡ መዝ. ፻፬÷፳፱። ፲፪፡ ምዕ. ፫÷፩ ፡ ዳን. ፯÷፲ ፡ ማቴ.
፲፮÷፳፯። ፲፫፡ ዮሐ. ፩÷፳፰ ፡ ፳፱። ፲፭፡ ማቴ. ፳፭÷፵፩።
፳፩። ፩፡ ምዕ. ፰÷፲፩ ፡ ኢሳ. ፷፭÷፲፯። ፪፡ ዕብ. ፲፪÷፳፪። ፫፡ ዘሌዋ. ፳፮÷፲፩ ፡ ፲፪ ፡ ዮሐ. ፩÷፲፬። ፬፡ ምዕ. ፯÷፲፯ ፡
ኢሳ. ፳፭÷፲። ፭፡ ፪ ቆሮ. ፭÷፲፯። ፮፡ ኢሳ. ፶፭÷፩ ፡ ዮሐ. ፬÷፲ ፡ ፯÷፴፯። ፯፡ ፪ ቆሮ. ፮÷፲፰። ፰፡ ምዕ.
፳÷፲፬።

ዕድላቸው ፡ በዲንና ፡ በእሳት ፡ በሚቃጠል ፡
ባሕር ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ሁለተኛ ፡ ሞት ፡ ነው ።
፱ ሰባቱም ፡ ኋለኞዎች ፡ መቅሠፍቶች ፡ የሞሉበ
ቸውን ፡ ሰባቱን ፡ ጽዋዎች ፡ ከያዙት ፡ ከሰባቱ ፡
መላእክት ፡ አንዱ ፡ መጥቶ ፡— ወደዚህ ፡ ና ÷ የበ
ጉንም ፡ ሚስት ፡ ሙሽራይቱን ፡ አሳይሃለሁ ፡
፲ ብሎ ፡ ተናገረኝ ። በመንፈስም ፡ ወደ ፡ ታላቅና ፡
ወደ ፡ ረጅም ፡ ተራራ ፡ ወሰደኝ ÷ የእግዚአብ
ሔርም ፡ ክብር ፡ ያለበትን ፡ ቅድስቲቱን ፡ ከተማ ፡
ኢየሩሳሌምን ፡ ከሰማይ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
በትወርድ ፡ አሳየኝ ፤ ብርሃንዋም ፡ እጅግ ፡ እንደ ፡
ከበረ ፡ ድንጋይ ፡ እንደ ፡ ኢያሰጲድ ፡ ድንጋይ ፡
፲፪ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ብርሌ ፡ የጠራ ፡ ነበረ ፤ ታላቅና ፡
ረጅም ፡ ቅጥር ፡ ነበራት ÷ አሥራ ፡ ሁለትም ፡
ደጆች ፡ ነበሩአት ፡ በደጆቹም ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡
መላእክት ፡ ቆሙ ÷ የአሥራ ፡ ሁለቱም ፡ የእስ
ራኤል ፡ ልጆች ፡ ነገዶች ፡ ስሞች ፡ ተጽፈውባ
፲፫ ቸው ፡ ነበር ። በምሥራቅ ፡ ሦስት ፡ ደጆች ÷
በሰሜንም ፡ ሦስት ፡ ደጆች ÷ በደቡብም ፡ ሦስት ፡
ደጆች ÷ በምዕራብም ፡ ሦስት ፡ ደጆች ፡ ነበሩ ።
፲፬ ለከተማይቱም ፡ ቅጥር ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ መሠ
ረቶች ፡ ነበሩአት ÷ በእነርሱም ፡ ውስጥ ፡ የአ
ሥራ ፡ ሁለቱ ፡ የበጉ ፡ ሐዋርያት ፡ ስሞች ፡ ተጽ
ፈው ፡ ነበር ።
፲፭ የተናገረኝም ፡ ከተማይቱንና ፡ ደጆችዋን ፡
ቅጥርዋንም ፡ ይለካ ፡ ዘንድ ፡ የወርቅ ፡ ዘንግ ፡ ነበ
፲፮ ረው ። ከተማይቱም ፡ አራት ፡ ማዕዘን ፡ ነበራት ÷
ርዝመትዋም ፡ እንደ ፡ ስፋትዋ ፡ ልክ ፡ ነበረ ።
ከተማይቱንም ፡ በዘንግ ፡ ለካት ፡ አሥራ ፡ ሁለ
ትም ፡ ሺህ ፡ ምዕራፍ ፡ ሆነች ፤ ርዝመትዋና ፡
፲፯ ስፋትዋ ፡ ከፍታዋም ፡ ትክክል ፡ ነው ። ቅጥር
ዋንም ፡ ለካ ÷ መቶ ፡ አርባ ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ በሰው ፡
፲፰ ልክ ÷ እርሱም ፡ በመልአክ ፡ ልክ ። ቅጥርዋም ፡
ከኢያሰጲድ ፡ የተሠራ ፡ ነበረ ÷ ከተማይቱም ፡
ጥሩ ፡ ብርጭቆ ፡ የሚመስል ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ነበ
፲፱ ረች ። የከተማይቱም ፡ ቅጥር ፡ መሠረት ፡ በከ
በረ ፡ ድንጋይ ፡ ሁሉ ፡ ተጌጦ ፡ ነበር ፤ ፊተኛው ፡
መሠረት ፡ ኢያሰጲድ ÷ ሁለተኛው ፡ ሰንፔር ÷
ሦስተኛው ፡ ኬልቄዶን ÷ አራተኛው ፡ መረግድ ÷
፳ አምስተኛው ፡ ሰርዶንክስ ÷ ስድስተኛው ፡ ሰር
ድዮን ÷ ሰባተኛው ፡ ክርስቲሎቤ ÷ ስምንተ
ኛው ፡ ቢረሌ ÷ ዘጠነኛው ፡ ወራውሬ ÷ አሥረ
ኛው ፡ ክርስጵራስስ ÷ አሥራ ፡ አንደኛው ፡ ያክ
ንት ÷ አሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ አሜቴስጢኖስ ፡
፳፩ ነበረ ። አሥራ ፡ ሁለቱም ፡ ደጆች ፡ አሥራ ፡
ሁለት ፡ ዕንቁች ፡ ነበሩ ፤ እየአንዳንዱ ፡ ደጅ ፡
ከአንድ ፡ ዕንቍ ፡ የተሠራ ፡ ነበረ ። የከተማይ
ቱም ፡ አደባባይ ፡ ጥሩ ፡ ብርጭቆ ፡ የሚመስል ፡
ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ።

ሁሉንም ፡ የሚገዛ ፡ ጌታ ፡ አምላክና ፡ በጉ ፡ ፳፪
መቅደስዋ ፡ ናቸውና ፡ መቅደስ ፡ በእርስዋ ፡
ዘንድ ፡ አላየሁም ። ለከተማይቱም ፡ የእግዚአ ፳፫
ብሔር ፡ ክብር ፡ ስለሚያበራላት ፡ መብራትዋም ፡
በጉ ፡ ስለ ፡ ሆነ ÷ ፀሐይ ፡ ወይም ፡ ጨረቃ ፡ እን
ዲያበሩላት ፡ አያስፈልጓትም ፡ ነበር ። አሕዛ ፳፬
ብም ፡ በብርሃንዋ ፡ ይመላለሳሉ ÷ የምድርም ፡
ነገሥታት ፡ ክብራቸውን ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ ያመ
ጣሉ ፤ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ ስለሌለ ፡ ደጆችዋ ፡ ፳፭
በቀን ፡ ከቶ ፡ አይዘጉም ÷ የአሕዛብንም ፡ ግር ፳፮
ማና ፡ ክብር ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ ያመጣሉ ። ለበ ፳፯
ጉም ፡ በሆነው ፡ በሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ከተጻ
ፉት ፡ በቀር ÷ ጸያፍ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ርኵሰትና ፡
ውሸትም ፡ የሚያደርግ ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ ከቶ ፡
አይገባም ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

በአደባባይዋም ፡ መካከል ፡ ከእግዚአብሔ ፩
ርና ፡ ከበጉ ፡ ዙፋን ፡ የሚወጣውን ፡ እንደ ፡
ብርሌ ፡ የሚያንጸባርቀውን ፡ የሕይወትን ፡ ውኃ ፡
ወንዝ ፡ አሳየኝ ። በወንዙም ፡ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ፪
በየወሩ ፡ እያፈራ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ፍሬ ፡ የሚ
ሰጥ ፡ የሕይወት ፡ ዛፍ ፡ ነበረ ÷ የዛፉም ፡ ቅጠ
ሎች ፡ ለሕዝብ ፡ መፈወሻ ፡ ነበሩ ። ከእንግዲ ፫
ህም ፡ ወዲህ ፡ መርገም ፡ ከቶ ፡ አይሆንም ። የእ
ግዚአብሔርና ፡ የበጉም ፡ ዙፋን ፡ በእርስዋ ፡
ውስጥ ፡ ይሆናል ÷ ባሪያዎቹም ፡ ያመልኩታል ÷
ፊቱንም ፡ ያያሉ ÷ ስሙም ፡ በግምባሮቻቸው ፡ ፬
ይሆናል ። ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ሌሊት ፡ አይ ፭
ሆንም ÷ ጌታ ፡ አምላክም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ያበራ
ላቸዋልና ፡ የመብራት ፡ ብርሃንና ፡ የፀሐይ ፡ ብር
ሃን ፡ አያስፈልጋቸውም ፤ ለዘላለምም ፡ እስከ ፡
ዘላለም ፡ ይነግሣሉ ።
እርሱም ፡— እነዚህ ፡ ቃሎች ፡ የታመኑና ፡ ፮
እውነተኛዎች ፡ ናቸው ÷ የነቢያትም ፡ መናፍ
ስት ፡ ጌታ ፡ አምላክ ፡ በቶሎ ፡ ሊሆን ፡ የሚገባ
ውን ፡ ነገር ፡ ለባሪያዎቹ ፡ እንዲያሳይ ፡ መልአ
ኩን ፡ ሰደደ ። እነሆም ÷ በቶሎ ፡ እመጣለሁ ። ፯
የዚህን ፡ መጽሐፍ ፡ ትንቢት ፡ ቃል ፡ የሚጠ
ብቅ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ፡ አለኝ ።
ይህንም ፡ ያየሁትና ፡ የሰማሁት ፡ እኔ ፡ ዮሐንስ ፡ ፰
ነኝ ። በሰማሁትና ፡ ባየሁትም ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡
በሳየኝ ፡ በመልአኩ ፡ እግር ፡ ፊት ፡ እሰግድ ፡
ዘንድ ፡ ተደፋሁ ። እርሱም ፡— እንዳታደርገው ፡ ፱
ተጠንቀቅ ፤ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ከወንድሞችህም ፡
ከነቢያት ፡ ጋር ፡ የዚህንም ፡ መጽሐፍ ፡ ቃል ፡
ከሚጠብቁ ፡ ጋር ፡ አብሬ ፡ ባሪያ ፡ ነኝ ፤ ለእግ
ዚአብሔር ፡ ስገድ ፡ አለኝ ።
ለእኔም ፡— ዘመኑ ፡ ቀርቦአልና ፡ የዚህን ፡ ፲

፳፩። ፲ ፤ ሕዝ. ፵ ፥ ፪ ። ፲፩ ፤ ሕዝ. ፵፫ ፥ ፪ ፥ ፭ ። ፲፪ ፡ ፲፫ ፤ ሕዝ. ፵፰ ፥ ፴፩—፴፬ ። ፲፬ ፤ ኤፌ. ፪ ፥ ፳ ። ፲፭ ፤ [illegible]
፲፫ ፥ ፭ ። ፲፱ ፡ ፳ ፤ ኢሳ. ፶፬ ፥ ፲፩ ፡ ፲፪ ። ፳፪ ፤ [illegible] ። ፳፫ ፤ ኢሳ. ፷ ፥ ፲፱ ። ፳፬ ፤ ኢሳ. ፷ ፥ ፫ ። ፳፭ ፤
ኢሳ. ፷ ፥ ፲፩ ። ፳፯ ፤ ኢሳ. ፶፪ ፥ ፩ ።
፳፪። ፩ ፤ ሕዝ. ፵፯ ፥ ፩ ። ፪ ፤ ዘፍጥ. ፪ ፥ ፱ ፤ ሕዝ. ፵፯ ፥ ፲፪ ። ፫ ፤ ዘካ. ፲፬ ፥ ፲፩ ። ፬ ፤ ማቴ. ፭ ፥ ፰ ፤ ፩ ዮሐ. ፫ ፥ ፪ ።
፭ ፤ ዳን. ፯ ፥ ፲፰ ።

መጽሐፍ ፡ ትንቢት ፡ ቃል ፡ በማኅተም ፡ አትዝ
፲፩ ጋው ። ዓመፀኛው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ያምፅ ፥ ርኩ
ሱም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይርከስ ፥ ጻድቁም ፡ ወደ ፡
ፊት ፡ ጽድቅ ፡ ያድርግ ፥ ቅዱሱም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡
ይቀደስ ፡ አለ ።
፲፪ እነሆ ፥ በቶሎ ፡ እመጣለሁ ፥ ለእያንዳንዱም ፡
እንደ ፡ ሥራው ፡ መጠን ፡ እከፍል ፡ ዘንድ ፡
፲፫ ዋጋዬ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ አለ ። አልፋና ፡ ዖሜጋ ፥
ፊተኛውና ፡ ኋለኛው ፥ መጀመሪያውና ፡ መጨ
ረሻው ፡ እኔ ፡ ነኝ ።
፲፬ ወደ ፡ ሕይወት ፡ ዛፍ ፡ ስመድረስ ፡ ሥልጣን ፡
እንዲኖራቸው ፡ በደጆችዋም ፡ ወደ ፡ ከተማ
ይቱ ፡ እንዲገቡ ፡ ልብሳቸውን ፡ የሚያጥቡ ፡ ብፁ
፲፭ ዓን ፡ ናቸው ። ውሻዎችና ፡ አስማተኛዎች ፡ ሴሰ
ኛዎችም ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዮችም ፡ ጣዖትንም ፡ የሚ
ያመልኩት ፡ ውሸትንም ፡ የሚወዱና ፡ የሚያ
ደርጉ ፡ ሁሉ ፡ በውጭ ፡ አሉ ።
፲፮ እኔ ፡ ኢየሱስ ፡ በአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡
ዘንድ ፡ ይህን ፡ እንዲመሰክርላችሁ ፡ መልአኬን ፡
ላክሁ ። እኔ ፡ የዳዊት ፡ ሥርና ፡ ዘር ፡ ነኝ ፥ የሚ
ያበራም ፡ የንጋት ፡ ኮከብ ፡ ነኝ ።
መንፈሱና ፡ ሙሽራይቱም ፡ — ና ፡ ይላሉ ። ፲፯
የሚሰማም ፡ — ና ፡ ይበል ። የተጠማም ፡ ይምጣ ፥
የወደደም ፡ የሕይወትን ፡ ውኃ ፡ እንዲያው ፡
ይውሰድ ።
በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ የትንቢት ፡ ፲፰
ቃል ፡ ለሚሰማ ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ እመሰክራለሁ ፤
ማንም ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ አንዳች ፡ ቢጨምር ፡ እግዚ
አብሔር ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፉትን ፡ መቅ
ሠፍቶች ፡ ይጨምርበታል ፤ ማንምም ፡ በዚህ ፡ ፲፱
በትንቢት ፡ መጽሐፍ ፡ ከተጻፉት ፡ ቃሎች ፡
አንዳች ፡ ቢያጐድል ፥ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከተጻ
ፉት ፡ ከሕይወት ፡ ዛፍና ፡ ከቅድስቲቱ ፡ ከተማ ፡
እግዚአብሔር ፡ ዕድሉን ፡ ያጐድልበታል ።
ይህን ፡ የሚመሰክር ፡ — አዎን ፥ በቶሎ ፡ እመ ፳
ጣለሁ ፡ ይላል ። አሜን ፥ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ሆይ ፥
ና ።
የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ከሁ ፳፩
ላችሁ ፡ ጋር ፡ ይሁን ፤ አሜን ።

፳፪ ። ፲፩ ፤ ዳን ፲፪ ፥ ፲ ። ፲፪ ፤ ኢሳ ፵ ፥ ፲ ። ፲፫ ፤ ም ፩ ፥ ፲፯ ። ፲፬ ፤ መዝ ፻፲፱ ፥ ፩ ። ፲፭ ፤ ፩ ቆሮ ፮ ፥ ፱ ፡ ፲ ።
፲፮ ፤ ም ፩ ፥ ፩ ፤ ማቴ ፩ ፥ ፩ ። ፲፯ ፤ ም ፳፩ ፥ ፯ ። ፲፰ ፡ ፲፱ ፤ ዘዳግ ፬ ፥ ፪ ።

Printed in Great Britain by
Lowe and Brydone (Printers) Limited, London, N.W.10